መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 2 ቁጥር 64 ሐምሌ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99

እስከመቼ ነው ክልሎችን "ሉዓላዊ ናችሁ" እያልን የምንሸነግላቸው?

መታሰቢያ መልአከ

አዲሱ መንግሥት "በፕሬስ ላይ ባለው አቋም" ወቀሳና ትችት እየቀረበበት ነው!

ከሰሞነኛው ዕስርና ካልተሻሻለው፣ "የሽብርተኞች ሕግ" ጀርባ ምን አለ?

የማንነት' ፖለቲካ፤ የኢትዮጵያ ፍፃሜ

ተሾመ ሽፈራው

"ልዑል አስወደደኝ!" የአፄ ኃይለስላሴ የልጅ ልጅ

ብሩክ መኮንን

"እስከ ዛሬ ለማንም ያላወጋኋቸው የቴዲ አፍሮ እውነቶች"

በአለምፀሐይ ወዳጆ

"በሕዝብና መንግስት ገንዘብ የለማችውን ሃዋሳ ለመጠቅለል ማሰብ ስህተት ነው"

ስዩም ተሾመ (አክቲቪስትና መምህር)

"በኢሕአዴግ ድርጅቶች ገመድ ጉተታ ብዙ ችግር እየተፈጠረ ነው"

ፕ/ር መረራ ጉዲና



# `እስር`

## የህግ የበላይነትን ጥያቄ ይመልስ ይሆን ?



**3**



“በኢሕአዲግ ድርጅቶች ገመድ ጉተታ ብዙ ችግር እየተፈጠረ ነው”

*ፕ/ር መረራ ጉዲና*

“በሕዝብና መንግስት ገንዘብ የለማችውን ሃዋሳ ለመጠቅለል ማሰብ ስህተት ነው”

*ስዩም ተሾመ (አክቲቪስትና መምህር)*

“ኢትዮጵያ ዛሬ የሕሊና እስረኞች ያሉባት ሃገር ሆናለች”

*እስክንድር ነጋ*

.................... 2

”እስር” የህግ የበላይነትን ጥያቄ ይመልስ ይሆን?

መሳክ ቢ.

.................... 5

ከሰሞነኛው እስርና ካልተሻሻለው፣ “የሽብርተኞች ሕግ” ጀርባ ምን አለ?

....................8

እስከመቼ ነው ክልሎችን “ሉዓላዊ ናችሁ” እያልን የምንሸነግላቸው?

መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

....................9

አዲሱ መንግሥት “በፕሬስ ላይ ባለው አቋም” ወቀሳና ትችት እየቀረበበት ነው!

.................... 10

የማንነት’ ፖለቲካ፤ የኢትዮጵያ ፍፃሜ

ተሾመ ሽፈራው

.................... 11

ለዛ

....................13


**ቀጣይ ዕትም**

**ቅዳሜ**

**ሐምሌ 13**

**ይጠብቁን!**




**ቁጥር 63 ዕትም**


“በአፍሪካ ደረጃ በጥራትና በፍጥነት አገልግሎት መስጠት ተቀዳሚ ግባችን ነው”

*ሳምራዊት ሽፈራው*

....................14

“ከኢንተርኔት አምጥተን የምንሰጣቸው የሚመስላቸው ሰዎች አሉ”

*አቶ ቸርነት ተካ*

....................15

መረባ ሌላኛዋ መፃኢ ኮከብ

....................16

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በደቡብ አፍሪካ ከትናንትና እስከ ዛሬ

ተረፈ ወርቁ

....................17

ሀገር አሳሹ ዋልተር ሚትልሆዘር በኢትዮጵያ

ብሩክ መኮንን

....................19

“ልዑል አስወደደኝ!”

የአፄ ኃይለስላሴ የልጅ ልጅ

ብሩክ መኮንን

....................21

የ“ሚዛን” ድራማ ወላጅ እናት ዛብሽ እስጢፋኖስ

....................23

“እስከ ዛሬ ለማንም ያላወጋኋቸው የቴዲ አፍሮ እውነቶች”

በአስምፀሐይ ወዳጆ

27

ማህበራዊ ሚዲያ

28

**ዜና**

# "ኢትዮጵያ ዛሬ የሕሊና እስረኞች ያሉባት ሃገር ሆናለች" እስክንድር ነጋ



የአዲስ አበባ ህዝብ ሰላማዊ ሰልፎችን ለማድረግም ሆነ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን እንዳያደርግ ማዕቀብ ተጥሎበታል ሲል የአዲስ አበባ ባላደራ ምክር ቤት ባልደራ ሰብሳቢ እስክንድር ነጋ ገለጸ፡፡

"የሕሊና እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ" በሚል ባልደራስ ባወጣው መግለጫውና በትናትናው ዕለት ሲሰጥ በነበረው ጋዜጣዊ መግለጫው፤ የአዲስ አበባ ሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍም ሆነ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን እንዳያደርግ ማዕቀብ ተጥሎበታልብሏል፡፡

"ኢትዮጵያ ዛሬ የሕሊና እስረኞች ያሉባት ሃገር ሆናለች ያለው የሰብአዊ መብት ተሚጋቹ እስክንድር ነጋ የሕወሓት አገዛዝ ከተገረሰሰ ከአንድ አመት በኋላ በርካቶች በሕሊና እስረኝነት ወደ እስር እንዲጋዙ ተደርጓል፡፡

የባላደራው ምክር ቤት ዋና ጸሃፊ ኤልያስ ገብሩና የሕዝብ ግንኙነት ሓላፊው ስንታየሁ ቸኮልን ጨምሮ በርካቶች ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ከእነዚህ እስረኞች በአብዛኞቹ ላይ ፖሊስ በባህርዳር ከተፈጸመው ችግር ጋር ንክኪ አላቸው በሚል በኢትዮጵያ ሕዝብ፣በአዲሱ አመራርም ሆነ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በተወገዘው የሽብር ህግ ክስ መስርቶባቸው በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡" ሲል እውነታውን በግልጽ አስቀምጧል፡፡

"በባህር ዳርም ሆነ በአዲስ አበባ የተከሰቱት ችግሮች መጀመሪያቸውም ሆነ መጨረሻቸው ኢሕአዴግ ውስጥ የተፈጠረ ልዩነት መሆኑ እየታወቀ በባላደራው አባላት ላይም ሆነ በሌሎች ላይ እየተወሰደ ያለው የእስር ርምጃ አሳዛኝ ነው፣አንቀበለውምም" ያለው ባላደራው ም/ቤት በዕለቱ የነበረው ጋዜጣዊ መግለጫ ባልታወቁ ቡድኖች አማካይነት እንዲቋረጥ መደረጉ ይታወቃል፡፡

# ነፃ የት/ቤት ዩኒፎርም ለ600 ሺህ የአዲስ አበባ ተማሪዎች

በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ት/ቤቶች ውስጥ ለሚማሩ ከ600.000 (ከስድስት መቶ ሺህ) በላይ ተማሪዎች የት/ቤት ደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) በራሱ ወጪ አሰፍቶ ለማደል በዝግጅት ላይ መሆኑን የከተማው አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የከተማ አስተዳደሩ በከተማዋ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ለማምጣት ከያዛቸው ታላላቅ እቅዶቹ መካከል አንዱ እንደሆነ የተነገረለትን ያህል ለተማሪዎች የት/ቤት ዩኒፎርም አሰፍቶ በነፃ የማደል ዕቅድ እውን ለማድረግ ከወራት በፊት ጀምሮ በስፋት ሲንቀሳቀስበት እንደቆየ በገለፀበት መግለጫው እንደተመለከተው ለተማሪዎች ተስማሚ የሆኑትን የደንብ ልብሶች ለማቅረብ ፋሽን ዲዛይነሮችን ያሳተፈ ሰፊ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

"በፋሽን ዲዛይነሮቹ በቀረቡ የተማሪዎች ዩኒፎርም አይነቶችና ጥራት ላይ የተማሪ ወላጆች፣ መምህራን፣ የሥነ ልቦና ባለሙያዎችና ተማሪዎች ራሳቸው ሀሳብ እንዲሰጡበት ተደርጓል" ያለው የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ጽ/ቤት ቁጥራቸው 400 (አራት መቶ) በሚጠጉ በከተማዋ በሚገኙ ት/ቤቶች ለሚማሩት ከ600 ሺህ በላይ ለሚሆኑት የመንግሥት ት/ቤት ተማሪዎች ከደንብ ልብስ በተጨማሪ ደብተርና ሌሎች ለትምህርት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በነፃ የማደል ዕቅድ መያዙን አስታውቋል፡፧

‹‹ ይህ የተደረገው የተማሪ ቤተሰቦችን ሸክም ለመቀነስና ችግራቸውን ለመጋራት ›› በማሰብ እንደሆነ የገለፀው የከንቲባው ጽ/ቤት ‹‹ የተማሪዎችን ወጪ መሸፈን የትምህርት ሥርዓቱን እንደሚያግዝ፣ የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድን ለመገንባትና የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እንደሚረዳ ›› እምነት ማሳደሩን በሰጠው መግለጫ አመልክቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ም/ከንቲባ ኢንጂነር ታከለ ኡማ በይፋ ያስጀመሩት ይህ ፕሮግራም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሥራው ተጠናቆ ለመጪው የትምህርት ዝግጁ እንዲሆን የታሰበ ሲሆን ከዩኒፎርሙ በተጓዳኝ ለተማሪዎቹ በነፃ ለመስጠት ለታሰበው የ7 ሚሊዮን ደብተር ልገሳም በበጎ ፈቃደኞች ርብርብ እንዲሁም በባለሀብቶችና ድርጅቶች ልገሳ ግማሽ ያህሉ (3.5 ሚሊዮን ደብተር) ተገኝቷል፡፡ በቀጣይ ሳምንትም ቀሪዎቹን ደብተሮች በማሰባሰብ ለተማሪዎች የማዳረሱ ሥራ ይጀመራል ተብሏል፡፡

# ዓለም አቀፍ የሂሳብ አቀራረብ መርህ ሥልጠና ተካሄደ!!

"የኢትዮጵያ ሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማህበር" ሐምሌ 3 ቀን 2011ዓ.ም ‹‹ ዓለም አቀፍ የሂሳብ አቀራረብ መርህ ›› በሚል ትግበራ ሥልጠና የመዝጊያ ፕሮግራም በራስ ሆቴል አዲሱ አዳራሽ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሥልጠና ተሳታፊዎች በተገኙበት ‹‹ ትሬኒንግና (የግንዛቤ ማስጨበጫ አሰጣጥ) የልምድ ልውውጥ ተካሂዷል፡፡

ስልጠናው የሙያ ማህበራት የሂሳብ አያያዝና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥጋቶችን አስመልክቶ በስፋት ጥያቄዎች ተነስተው አስተያየትና ግንዛቤ የሚሰጥ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡

በዕለቱ የማህበሩ ፕሬዚዳንት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮሐንስ ንጋቱ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን፣ በጉዳዩ ዙሪያ ሰፋ ያለ ሙያዊ ትንታኔ የታከለበት የሂሳብ አቀራረብ መርህን ያማከለ ገለፃ አድርገዋል፡፡ አቶ አሉላ ሀይሉ መድረኩን የመሩ ሲሆን፣ አቶ ዮሀንስ ታንቱ ስለ ኢትዮጵያ ሂሳብ አዋቂዎች ውይይት ያደረጉ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ያለውን የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሂደቱ፣ ውጤቱና ልምዱን፣ አካውንታንቶች ምን እየሰሩ እንደሆነ፣ የኮንሰልታቶች ማነስን አስመልክቶ በርካታ ጉዳዮችን አንስተው ከመድረኩ ተወያይተውበታል፡፡ የኦዲተሮች ማህበራትና ተቋማት ከአገር ውስጥ ገቢ ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ ሥጋቶቹ እንዴት ሊወገዱ ይችላሉ? ወደ ዘመናዊነት ለማሳደግ የተካሄደበትና የንግድ ም/ቤቶችና የንግዱ ማህበረሰብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ምን መደረግ አለበት? የሚሉና በኤክስፖርቶች ዙሪያ ተቀራርቦ መስራት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ አቶ አወቀ አስፋውና አቶ ተንሴ ነብይ በዕለቱ ውይይት ያደረጉ ሲሆን ከመዝጊያው ፕሮግራም በፊት የሰርተፍኬት ፕሮግራም መሰጠቱን ለመርዳት ችለናል፡፡

# የኢትዮጵያና የአሜሪካ ወታደራዊ ልምምድ ሰኞ ይጀመራል!

ኢትዮጵያና ልዕለ ኃያሏ አሜሪካ የጋራ ወታደራዊ ልምምዳቸውን የፊታችን ሰኞ ሰኔ 8 ቀን 2011 ዓ.ም በይፋ እንደሚጀምሩ ተገለፀ፡፡አዲስ አበባ ከሚገኘው ከአሜሪካ ኤምባሲ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የአሜሪካ ጦር ሀይል ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጋር በጥምረት የሚያከናወኑት የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ለ17 ቀናት እንዲካሄድ ዕቅድ ተይዟል፡፡የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የአባላቱን ዝግጁነትና አቅም በማሳደግ የቀጠናውን ሰላም ለማስከበር ለሚደረገው ጥረት አጋዥ እንዲሆንና የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎችን በብቃት እንዲወጣ ለማስቻል ታስቦ በተዘጋጀው የጋራ ወታደራዊ ልምምድ 1 ሺኅ አንድ መቶ የሰራዊቱ አባላትና የመንግሥት ሃላፊዎች ተሳታፊ ይሆናሉ ተብሏል፡፡በሶማሊያ የተሰማራውን የአፍሪካ ሰላም አስከባሪ ሀይል (አሚሶም) አባላትን አቅም ማሳደግ ላይ ባተኮረው በዚሁ የሁለቱ ሀገራት የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ከብራዚል፣ ካናዳ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ኔዘርላንድስ፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ጅቡቲ፣ ኬኒያ፣ ብሩንዲ፣ ሶማሊያ፣ ሩዋንዳ እና ኡጋንዳ የተውጣጡ ወታደሮችም ተሳታፊ እንደሚሆኑበት ያገኘበው መረጃ አመልክቷል፡፡

# “በኢሕአዲግ ድርጅቶች ገመድ ጉተታ ብዙ ችግር እየተፈጠረ ነው”

ሰሞኑን የአማራ ክልል “መፈንቅለ መንግስት”፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል እየተካሄደ ያለውን የጅምላ አፈሳ፣ ዳግም ያገረሸውን የቤኒሻንጉል ግጭት፣የሲዳማ ክልልነት ጥያቄን እንዲሁም ቀጣዩን ምርጫ 2012ን አስመልክቶ ከወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መልኩ በቂ ምላሽ ይሰጡን ዘንድ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሰፊ ልምድ ያላቸውን ፕ/ር መረራ ጉዲና እና ስዩም ተሾመን የግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡ መልካም ቆይታ፡፡

**ግዮን፡- ሰሞኑን በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ በርካታ ዜጎች ላይ የጅምላ እስር እየተካሄደባቸው ይገኛል፡፡ ይህ ሂደት ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወደ አምባገነንነት እየተጓዘ መሆኑን ያመላክታል?**

ፕ/ር መረራ፡- አፍ ሞልቶ ወደ ኋላ እየተመለሰ ነው ለማለት ትንሽ ያስቸግራል፡፡ በእኛ በኩል የምንችለውን ያህል መንግስትን ለማነጋገር እየሞከርን ነው፡፡ ግን በስፋት እየተካሄደ ያለው ዕስር ያስደነግጣል፤ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ማድረግ የምንችለውን እየጣርን ነው፤ በሚዲያዎችም መልዕክት



እያስተላለፍን ነው፡፡

በአንድ በኩል አገሪቷና ሕዝቦቿን ወደ ብሔራዊ መግባባት መምራቱ የተሻለ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ለዚህ ችግር መፍትሔ መፈለግ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ ጎን ለጎን ደግሞ ሕዝብ አላፈላጊ በሆነ ነገር እንዳይጋጭ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ደህንነቱ፣ ፖሊስና መከላከያ ሠራዊቱ መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ አሁን በኦሮሞ ተወላጆች ላይ እየተወሰደ ያለው እስራት ግን

## ፕ/ር መረራ ጉዲና

አስደንጋጭ ነው፡፡

**ግዮን፡- በኦሮሚያ ክልል የተያዙት ግለሰቦች “ከኦነግ ሸኔ” ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ነው፡፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ቀደም ሲል በፓርላማ ቃል እንደገቡት ተጠርጣሪዎቹ ጉዳያቸው ተጣርቶ ነው የተያዙት? “ሳናጣራ አናስርም” ብለዋልና፡፡**

ፕ/ር መረራ፡- በየቦታው ያልተጣሩ የጅምላ ዕስረኞች እንዳሉ እየነገሩናቸው ነው፡፡ ማንም ዜጋ ሕጋዊ ባልሆነ፣ ባልተጠራና “ትጠረጠራለህ” በሚል ደረጃ ብቻ መታሰሩ መንግስትንም ጭምር እንደማይጠቅም ለሚመለከተው አካል አስረድተናል፡፡ እነሱም “ይሄን እናሻሽለን” ዓይነት ነገር ነግረውናል፤ እሱ እንግዲህ የት ደርሶ እንደሚቆም ውሎ አድሮ ይታያል፡፡

ግን ዋናው ጉዳይ ቀደም ሲል እንደገለፅሁት በአንድ በኩል ፖለቲካዊ መፍትሄ እየፈለጉ፣ በሌላ በኩል የሕዝቦችን ደህንነት ለመጠበቅ መጣር፡፡ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ እስካልተካሄደ ድረስ በቀር ለብዙ ነገሮች ክፍት ይሆንና ሁኔታውን ወደ ኋላ መመለስ ውስጥ መግባት ይመጣል፡፡ ስለዚህ ጥንቃቄ ▶

# “በሕዝብና መንግስት ገንዘብ የለማችውን ሃዋሳ ለመጠቅለል ማሰብ ስህተት ነው”



**ግዮን፡- ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በአማራ ክልል ከተካሄደው “መፈንቅለ መንግስት” እና እሱን ተከትለው ከተፈጠሩት ክስተቶች ውይይታችን እንጀምር፡፡**

ስዩም፡- መልካም፡፡ ያለነው የለውጥ ጊዜ ላይ ነው፡፡ ለውጥ ሲካሄድ ደግሞ በመሀሉ ብዙ ውጣ ውረዶች ይኖራሉ፤ ከዛ ውስጥ አንዱ ቀድሞ ስልጣን ላይ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ ጀነራሎችና ሌሎች ኃላፊዎች ሁሉም ለውጡ እንዲመጣ የራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡ ለምሳሌ ጀነራል ከማል ገመቹ ሀገር ጥሎ እስከ መሰደድ ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ ጀነራል አሳምነው ጽጌና ጀነራል ተፈራ ማሞም እንዲሁ የራሳቸውን ትግል አድርገዋል፡፡ በዛ ምክንያትም ለዕስር ተዳርገዋል፡፡

ለውጡ ሲገኝ እነዚህን ዋጋ የከፈሉ ሰዎች ወደ ኃላፊነት ማውጣት የለውጡ አንድ ግብዓት ተደርጎ የታሰበ ይመስለኛል፡፡ ሆኖም ግን ይሄ አካሄድ በደንብ የተጠናናና በጥንቃቄ የተወሰደ አልነበረም፡፡ ለጦርነት የሰለጠነ ጀነራልን የፖለቲካ ሹመት ላይ ስታስቀምጥ እንዲህ ዓይነት ሊከሰት እንደሚችል መጠርጠር ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም እየታዩ የነበሩ ምልክቶችና በኃላፊነት የተሾሙት ጀነራሎች ሲወስዷቸው የነበሩት ዕርምጃዎች፣ ሲሰጧቸው የነበሩት መግለጫዎች አመላካች በመሆናቸው ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግና የእርምት ዕርምጃ መወሰድ ነበረበት፡፡ የትክክለኛውን የፖለቲካ መስመር እንዲከተሉ፣ አልያም እንደ ጀነራል ከማል ገመቹ ፈጥኖ ከኃላፊነት ማንሳት

## ስዩም ተሾመ (አክቲቪስትና መምህር)

ሲቻል ያ ባለመደረጉ ምክንያት ነው በባህርዳር አሳዛኙና ችግር የተፈጠረው፡፡

**ግዮን፡- በኦሮሚያ ክልል የጸጥታ ሓላፊ የነበሩት ጀነራል ከማል ገመቹ፤ በአቶ ለማ መገርሳ ትዕዛዝ በፍጥነት ከሓላፊነት ባይነሱ ኖሮ እንደ ባህርዳሩ ዓይነት ችግር ይፈጥሩ ነበር ብሎ መገመት ይቻላል?**

ስዩም፡- ምናልባት ከሓላፊነት ከተነሱ በኋላ እኚህ ጀነራል የሰጧቸውን አስተያየት ከተመለከትን እጅግ በጣም ኃላፊነት የጎዳላቸው ናቸው፡፡ ከአንድ ትልቅ አመራር የማይጠበቅም ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ጀነራል አሳምነው ፅጌ ከሓላፊነት ሊነሱ ሙከራ ቢደረግ፣ እንዲህ ዓይነት ዕርምጃዎችን እንደማይቀበሉ ሲናገሩ ነበር፡፡ ከዛም አልፎ ተርፎ የክልሉ ሕዝብ የጦር መሳሪያ እንዲታጠቅ፣ በሱዳን በኩል የሚገባው የጦር መሳሪያ ሊታገድ ▶

ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- በየትኞቹ የኦሮሚያ ከተሞች ውስጥ ነው የጅምላ እስሩ እየተካሄደ ያለው?**

ፐ/ር መረራ፡- እኔ ከማውቀው ነቀምት ላይ የድርጅታችን የዞኑ ኃላፊና ደጋፊዎቻችን ታስረውብናል፡፡ ጉጂ አካባቢም በብዛት የድርጅታችን አባሎችና ደጋፊዎች ታስረዋል፡፡ ጅማ፣ ሐረር፣ ሆለታ መስመር አካባቢም በርካታ ደጋፊዎቻችን ለእስር ተዳርገዋል፡፡ በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች የተካሄደውን የዕሥር ዓይነት በዝርዝር በድርጅታችን የቢሮ ሊስት ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ እኔ አንዲሁ ለ መረጃ ያህል ነው የተወሰኑትን የጠቀስኩልህ፡፡

**ግዮን፡- ዕስረኞቹ ያሉበትን ሁኔታ፣ የሚደር ስባቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ካለ ያንን ለማጣራት ሙከራ አድርጋችኋል? የተገኘስ መረጃ ይኖራል?**

ፐ/ር መረራ፡- በአብዛኛው ይህንን ለማድረግ የሚያስችል አመቺ ሁኔታ የለም፡፡ ነቀምት አካባቢ የታሰሩ ዕስረኞችን በተመለከተ ቤተሰብ እንኳን ሊያነጋግራቸውና ሊያያቸው አልቻለም፡፡

ለምሳሌ ብዛት ያላቸው የኦሮሞ ተወላጆች ተይዘው፣ ተጭነው የተወሰዱትና የታሰሩት "ሰንቀሌ" አምቦ አካባቢ ያለው ወታደራዊ ካምፐ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ለቤተሰብ ጥየቃ፣ ለፍለጋም ሆነ ለማጣራት አመቺ ቦታ አይደለም ያሉት፡፡

**ግዮን፡- ጠ/ሚኒስትሩ ስልጣን በያዙ ማግስት እንደሚሻሻል ቃል በገቡት "የሽብር ሕጉ" ዛሬም ዜጎች ተጠርጥረው እየታሰሩ ነው፡፡ ዳግም ወደ ኋላ ተመልሶ በዚህ ሕግ መቅጣት ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ?**

ፐ/ር መረራ፡- ዋናው ጉዳይ ለውጥ የምንለው ራሱ መሰረታዊ የሆኑ ችግሮች እየገጠሙት ነው፤ ከዛ ነው እንዲህ ዓይነቱ ነገር የሚመነጨው፡፡ ለምሳሌ የኢህአዴግ ድርጅቶች ራሳቸው በዚህ ለውጥ ላይ የጋራ ስምምነት ያላቸው አይመስልም፡፡ ከዛም አልፎ ድርጅቶቹ ገመድ ጉተታ ላይ ናቸው፤ አንዱ ከአንዱ ለመብለጥ እየተጓተቱ ያሉና በዛ ውስጥ ሚዳክሩ ይመስላሉ፡፡ ሕዝብም ደግሞ "ለውጡ እኔን አልደረሰኝም" ብሎ በየአካባቢው የሚያሰማው ነገር ራሱ ቦታ አለው፡፡

መንግስትና ተፎካካሪ የፖለቲካ ኃይሎች የሚባሉት፤ የቀረፁት የጋራ አጀንዳ፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በሚያስፈልጉ ጉዳዮች ላይም የደረሱበት የጋራ ስምምነት የላቸውም፡፡ በዚህ መልክ የሚጠቀሱ ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ ለዚህም ነው ፈጥነን፣ በተደጋጋሚ አገሪቷ ወደ ብሔራዊ መግባባት፣ ወደ ብሔራዊ ስምምነት መሄድ አለባት የምንለው፡፡ አገሪቷ ምን ትሁን? እንዴት ትተዳደር? ወዴትና እንዴት ትሂድ? የሚሉት ጉዳዮች ግልጽ መሆን አለባቸው፡፡ ዝም ብሎ በኢህአዴግ ሳጥን ውስጥ ሆኖ ብዙ ነገሮችን መግፋቱ፤ ያ ሳጥን አሁን አሁን ደግሞ ራሱ ችግር ውስጥ እየገባ ስለሆነ፤ ከላይ የተባሉት ድርጊቶች ዛሬም ሳይፈቱ እንዲቆዩና እንዲተገበሩ አድርጓል፡፡

እነዚህ የችግር መንስኤ የሆኑት ጉዳዮች እስካልተፈቱ ድረስ እስሩም የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ነገሮችም ከመበላሸት ይድናሉ ብዬ አላምንም፡፡ የፖለቲካ ጥያቄዎች በፖለቲካዊ መልስ እንጂ፣ የኃይልና የጉልበት ዕርምጃ አይመልሳቸውም፡፡ መደራደር፣ መነጋገር አስፈላጊ ነው የምንለው ለዛ ነው፡፡

**ግዮን፡- በሽብር ሕጉ እርስዎም ተከሰው ለእስር ተዳርገውበታል፡፡ ብዙዎችም መስዋዕትነት ከፍለውበታል፡፡ ይህንን አላስፈላጊ ሕግ በተመለከተ ድርጅትዎ ኦ.ፌ.ኮ እስካሁን ለምን ቁርጥ ያለ አቋሙን የሚያሳይ ይፋዊ መግለጫ አላወጣም፡፡**

ፐ/ር መረራ፡- እሱ ላይ የቸገረን ነገር ምን መሰለህ፣ በዓለም ላይ ሰለጠኑ የሚባሉት አገራትም የፀረ ሽብር ሕግ አላቸው፡፡ ግን እነሱ የስልጣን ክፍፍሉን በአግባቡ ይተገበራሉ፡፡ ፍ/ቤቱ፣ ስራ አስፈፃሚው፣ ፓርላማው፣ ፖሊስና ደህንነቱ በአግባቡ ስቸራውን ስለሚያከናውኑና ተቆጣጣሪም ስላላቸው ሕጉ ለእንዲህ ዓይነቶቹ አገሮች ያስኬዳል፡፡

ዓለም ይህንን ሕግ በትጋትና በጥንቃቄ እየተጠቀመ ኢትዮጵያ ብቻ መጠቀም የለበትም የሚለው አስቸግሮናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት ይሄን ሕግ በተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ላይ መጠቀሙ

ቀሪውን በገጽ 25 ይመልከቱ

እንደማይገባው ሲናገሩም ሰምተናል፡፡ ከዛም አልፈው በተቃዋሚ ፓርቲው በአ.ብ.ንና በአዴፓ መኃል ምንም ዓይነት ልዩነት ሊኖር እንደማይገባ ሲናገሩ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ጀነራል ከማል ገመቹ ኦዴፓ ውስጥ ሆነው የራሳቸውን ተቃዋሚ ፓርቲ ሲመሩ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ተመሳሳይ ሓላፊነትና ውጤት ስለነበራቸው ተመሳሳይ ድርጊት ይፈፅማሉ ማለት አይቻልም፡፡ ግን በዋናነት እዚህ ላይ የፓርቲዎች አጀንዳ መቀላቀል ነገር ይታያል፡፡ ጀነራል አሳምነው ጽጌ የአ.ብ.ንን አጀንዳ እያራመዱ ብአዴን (አዴፓ) ውስጥ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የክልሉ የጸጥታ ዘርፍ ሓላፊነትን ይዘው የነበሩ ሰው ናቸው፡፡ ጀነራል ከማል ገመቹም የተቃዋሚ ፓርቲ አጀንዳ እያራመዱ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ይዘው የነበሩ ሰው ናቸው፡፡

እንደ ልዩነት የሚታየው የኦሮሞ ብሔርተኝነትን ሲያቀነቅኑ የነበሩት ከማል ገመቹ እየለዘበ የመጣውን፣ (ምክንያቱም ኦሮሞ ስልጣን ይዟል በሚል) እሳቤ፤ ያንን የኦሮሞ ብሔርተኝነት መሰረት አድርገው ሕዝባዊ ንቅናቄን ፈጥረው ወደዚህ ዓይነቱ የጥፋት እርምጃ የሚስኬድ ምቹ ሁኔታ አልነበራቸውም፡፡ ለጀነራል አሳምነው ጽጌ ግን ለእዛ የሚሆኑ በቂ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ አንደኛ በደልና ጭቆና ሲፈፅሙበት የነበሩት ሰዎች እዛው አጠገቡ ቁጭ ብለዋል፤ አጠገቡ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን በቅማንት ጉዳይ ላይ ጣልቃ እየገቡ በክልሉ ሕዝብ ላይ የሕልውና አደጋ እንደተጋረጠ አድርጎ እንዲያስብ ብሎም ያንን አጀንዳ እንዲያራምድ ጥሩ ዕድል ፈጥረውለታል፡፡

እስር ቤት በከፍተኛ ደረጃ ውርደትና መሰቃየት ሲደርስበት የኖረ ሰው የራሱ የሆነ ስነልቦናዊ ጫና ይኖረዋል፡፡ እንደህ ዓይነት ግፍ ሲፈፅሙበት የኖሩ ሰዎች በቅርብ ርቀት አጠገቡ ከመቀመጣቸው ባሻገር በሚመራው ክልል ደህንነትና ሰላም ላይ ጣልቃ እየገቡ በውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ስታይ፤ በአንፃሩ ከፍተኛ የሆነ ጦር የማዘዝ ስልጣን ሲኖርህ፣ ወደ እዚህ ዓይነት ነገር ልትገባ ትችላለህ፡፡ የአማራ ሕዝብ በመላ አገሪቱ የተበተነ እንደመሆኑ መጠን በተለያዩ አካባዎች በደልና ጭቆና ሲደርስበት፣ ከመኖሪያ ቤቱ ሲፈናቀል፣ ሲገደል ስታይ፣ ቀደም ሲል በአማራነታቸው ብዙ ሺኅ ወታደሮች አደራጅተህ ንቅናቄ ለመጀመር ስትንቀሳቀስ እንዲሁም በፊት በነበረው ስርዓት ተይዘህ ዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶብህ የነበርክ ሰው እንደነበርክ ስታስብ፣ በሌላ አከባቢ እነዛ አጠገብህ ያሉት ሰዎች በመሰል ግሩፖቻቸው ብዙ በደሎችን በየቦታው ሲፈፅሙ ስታይ ነገሮችን በሰከነ መልኩ የማየት አቅምህን ይቀንሰዋል፡ በዛ ላይ የፖለቲካ ልሂቃኖች፣ አክራሪ ብሔርተኞች የሚያራግቡት ነገር፣ ሌሎች ከእስር ቤት የወጡ ስነ ልቦናዊ ጫና የደረሰባቸው ነገሮችን ገፍተው መሄድ የሚፈልጉ ሰዎች (ስም መጥቀስ የማያስፈልጋቸው) ግፊትና በርታ ባይነትና ጀነራል አሳምነው ጽጌን ያልተፈለገ ዕርምጃ እንዲወስድ አድርጎታል፡፡

**ግዮን፡- በቤኒሻንጉል ዳግም ግጭቱ ተቀስቅሷል፡፡ ምክንያቱ ምን ይመስልሀል?**

እነዚህ ሰዎች እዛ ቦታ ላይ ለዘመናት የኖሩ ናቸው፤ መተከል የጎጃም አካልመሆኑ የሚታወስ ነው፡፡ ለ27 ዓመት በስርዓት በተቋማት ደረጃ ሲሰራ የነበረ ዘረኝነትና ጥላቻ፣ እንዲሁም በሌላ ክልል የሚኖር የአማራ ሕዝብ አንገቱን ደፍቶ፣ መብቱን እንዳይጠይቅ ሲደረግና እንደስደተኛ ሲቆጠር የነበረበት ሁኔታ ነበር፡፡

ለምሳሌ ቤኒሻንጉል ክልል በአሶሳ ከተማ 37% ነዋሪ አማራ ነው፡፡ በጥቅሉ በክልሉ ከሚኖሩ ሕዝቦች 21% አካባቢ አማራ ነው፡፡ ቤኒሻንጉል ውስጥ ከሺናሻ ቀጥሎ ሁለተኛ ሕዝብ አማራ ነው፡፡ በብዛት ይሄንን ያህል ብዛት ያለው ሕዝብ በክልሉ ውስጥ ምንም ዓይነት መብት እንደሌለው በሕገ-መንግስት ደረጃ ተወስኗል፡፡ በዛ አካባቢ በርካታ ግፍና በደል ሲፈፀም ነበር፤ ይሄ ለውጡ ከተከሰተ ጀምሮ ለውጡን ለማዳናቀፍ ሁከትን የመቀስቀስ ነገር ልክ ኢሉባቡርና ደቡብ አካባቢ ሲከሰትና ሲፈፀም እንደነበረው ቡኒሻንጉል ውስጥም ሲደረግ ነበር፡፡

የአማራ ሕዝብ ላይ ጥቃትና በደል ስትፈፅም የአማራ ብሔርተኝነትና አክራሪ የሆነ አመለካከት እንዲሰርፅ ታደርጋለህ፡፡ በዛ ደግሞ አሁን የታየው ለውጡን የማደናቀፍ ዓይነት

ቀሪውን በገጽ 26 ይመልከቱ

# “እስር” የህግ የበላይነትን ጥያቄ ይመልስ ይሆን?

**መላክ ቢ.**

በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ የሕግ የበላይነት (Rule of law) መከበር ጥያቄ በእያንዳንዱ ዘመነ መንግስት የሕዝብ ጥያቄ ሆኖ ሲነሳ ቢኖርም ምላሹ ግን “ላም አለኝ በሰማይ” ከመሆን አልዘለለም። በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን የህግ የበላይነት ከንጉሱ የበላይነት ቀድሞ እንዲመጣ ማሰብ ከንቱ ድካም ነበር። ምዕራባዊያን የሕግ ተመራማሪዎች የሕግ የበላይነት ከንጉስም በላይ ቀድሞ ሊከበር የሚገባው ነው ይላሉ። “ንጉስ ራሱም ቢሆን ከአምላክና ከሕግ በታች ነው። ምክንያቱም ንጉሱን ንጉስ ያደረገው ህጉ ነውና” “The king himself ought to be subject God and the law, because the law makes him King” እንዲሉ። በኢትዮጵያ ንጉሱ ከህግ በላይ ስለሆኑ “ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ” የሚል ብሂል እስከመነገር ደርሷል። አጼ ኃይለስላሴ “ስዩመ እግዚአብሄር” ተብለው በህግ የመገዛት ሳይሆን ህግን የመግዛት ስልጣን ለራሳቸው የሰጡ መሆናቸው በአገዛዝ ዘመናቸው ህግ የበላይ መሆኑ እንዳይረጋገጥ ምክንያት ሆኗል።

ደርግ ንጉሱን ጥሎ ወንበር ሲይዝ ደግሞ ህግ የበላይነቱ ቀርቶ መኖሩ እንኳን ጥያቄ ውስጥ ገባ። ሀገሪቱን ወታደራዊው ደርግ ከላይም ከታችም ብቸኛ ሆኖ አስተዳደራት። ሰው ያለ ሕግ ውሳኔ እንደከብት ታጎረ፣ እንደበግ ታረደ። ሰብዓዊነቱ ጥያቄ ውስጥ ገባ። ዘመነ ኢህአዴግ ዘመነ ደርግን ሲተካም በመጀመሪያው ሰሞን የዴሞክራሲ እና የህግ የበላይነት ጭላንጭል ቢታይም ሲውል ሲያድር ግን ማርክሲስቱ አስተዳደር ሕግን ከሃይል ኋላ ተከትሎ የሚመጣ ጋሪ አደረገው። አስተዳደሩ በዜጎች መብት አጠባበቅ ረገድ ካለፉት ሁለት መንግስታት የተሻለ ቢሆንም የህግ የበላይነትን አስከብሮ መቀጠል ላይ ግን ወገቤን አለ። አሳሪ ሕጎችን አውጥቶ በሕግ የበላይነት ሳይሆን በጨቋኝ ህጎች ረዳትነት ሀገር መግዛት ጀመረ። ነገር ግን ለዘመናት በኢትዮጵያ የጎደለው እና ሀገሪቱንና ህዝቧን ለከፋ ቀውስ የዳረጋት የህግ የበላይነት አለመከበር ጥያቄ ከቀደሙት ዘመናት ጠንከር ባለ መልኩ ተደጋግሞ መነሳት የጀመረው በዘመነ ኢህአዴግ ነው።

በዘመኑ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት ተቋማዊ ባህሪ የያዘ፣ በአብዛኛው በአሳሪ ሕጎች የተደገፈና በየትኛውም ስፍራ በየእለቱ የሚፈጸም ድርጊት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመደራጀት፣ መናገርና ተቃውሞን በሰላማዊ መንገድ መግለጽ እንዳይቻል ኢህአዴግ ጸረ-መብት ሕጎችን ደንግጓል። ይህንን የሚቃወሙ ወገኖች ፓርቲው ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ለሕዝቡ የገባውን ቃል አልጠበቀም ሲሉም ወቅሰዋል። ጎምቱው የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና ፖለቲከኛ ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ከዓመታት በፊት በዚሁ የሕግ የበላይነት ጉዳይ ላይ ተጠይቀው በሰጡት መልስ “በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት (rule of low) የለም። ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የለም። ከገዢው መደብ ውጭ ላሉ ማናቸውም አካላትም ይሁን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ሚዲያን በባለቤትነት ማስተዳደርና መጠቀም ተከልክሏል። እነዚህን ስንመለከት በሀገሪቱ ተቋማዊ በሆነ መልኩ መብቶች እየተጣሱ መሆኑን ያሳየናል” ነበር ያሉት።

## ጉዞ- ከወቀሳ ወደወቀሳ

ከአሮጌው ኢህአዴግ ውስጥ የወጣው አዲሱ ኢህአዴግ ሀገሪቱን በለውጥ መስመር ለማራመድ የጀመራቸው ጥረቶችና ቃሎች ገና ከሕዝብ ዓይንና ጆሮ ሳይርቁ በብሄራዊ ደረጃ ሊባል በሚችል መልኩ ሰላምና መረጋጋት ተጓደለ። ወጥቶ መግባት ፣ ተጉዞ መመለስ ጥያቄ ሆነ። የብሔር ግጭቶች እና ጠባብና ጥላቻ ወለድ ጥቃቶች በረከቱ። ዜጎች ተፈናቀሉ። መንገድ መዝጋት እና ዘረፋ እንደበጎ ተግባር ታየ። ክልሎች ማን አለብኝ አሉ። ወንጀል ፈጻሚዎች ሀገር ውስጥ ሆነው ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ቀሩ። የቡድኖች እና ግለሰቦች አምባገነንነት የሀገሪቱን መንግስት ደካማ መንግስት አስመስሎ አቀጨጨው። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ የህግ የበላይነት ቅድሚያ ይሰጠው እያለ መጮህ ጀመረ። መንግስት “ታጋሽና ሆደ ሰፊ ሆኜ ነው” አለ። “አምባገነን አታድርጉኝ” ብሎ የህግን የበላይነት አረጋግጥ ለሚለው የህዝብ ጥያቄ ግራ የሚያጋባ መልስ ሰጠ። የፖለቲካ ባለሙያዎች “ይህ መንግስት ከአምባገነንነት ተፈልቅቆ የወጣ በመሆኑ በሕግ የበላይነት እና በአምባገነንነት መካከል ያለው መስመር ላይ ብዠታ አለበት” ብለው ተናገሩ። የመንግስት ሕግን የማስከበር ብቃት ላይ ጥያቄ እየበረታ ሲሄድ እና በተለይም የሕግ የበላይነትን ማስከበር አጀንዳ ሆኖ ሲወጣ መንግስት በአፉ እንዳለው ወደአምባገነንነት የሚመራ መንገድን መከተል ጀመረ። ጅምላ እስር ተጀመረ!

## ምስጋናን ማመቻቸት

ቅዱስ መጽሐፉ “ከሕጻናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ” እንዲል የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አስተዳደር በኢትዮጵያ ሕዝቡን ያማረረው “የመንግስት አልባነት” ባህሪ መገለጫ የመሰለ የቡድን እና ግለሰቦች ማን አለብኝነት ጉዳይ ያስነሳቸውን ጥያቄዎች እና ምሬቶች ለራሱ ማስመስገኛ አድርጎ ተጠቀመባቸው የሚሉ አስተያየቶች መደመጥ ከጀመሩ ቆይተዋል። ሕዝብ የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አስተዳደር ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በሀገሪቱ የተፈጠሩ ብጥብጦችን እና ችግሮችን መሰረት በማድረግ “ሀገር በስብከት ብቻ አትመራም”፣“መንግስት ‘መንግስት መንግስት’ ይሸተት”፣“ህገወጦችን ለመግራት ምክር ብቻ ሳይሆን የተመጣጠነ ኃይልም ያስፈልጋል” ወዘተ ማለት ሲጀምር መንግስትም በበኩሉ “ቀስ እንበል፣ ለሃይል አንቸኩል፣ ነገር በዚህ መልክ አይቀጥልም፣ ይረጋጋል” አይነት የዓይናፋር ቅልስልስ መግለጫዎችን ሰጠ። በዚህ መካከል መንግስት ሕዝብ ነገሩን አጀንዳ እስኪያደርገው ድረስ የነበረውን ቆይታ የፈለገው ወደፊት ለሚወስደው እርምጃ ማመቻቸትነት ነው ብለው የተቹም ፖለቲካ አዋቂዎች ነበሩ። መንግስት ይህንን ጥያቄ በወሰደው እርምጃ ሳቢያ ቀጥሎ ለሚመጣው ▶

**የፓርቲው ሊቀመንበር ፕሮፌሰር መረራ እንደሚናገሩት የኦፌኮ አባላቶች በገፍ እየታሰሩ ነው። የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) በጋራ ከ1000 በላይ አባሎቻቸው መታሰራቸውን ነው ቪኦኤ ላይ ቀርበው ያስታወቁት።**

የሕዝብ ተቃውሞ መልስ እንደሚያደርገው ቀድሞም ግምት ነበር:: “እርምጃውን የወሰድነው ሕዝብ ገፋፍቶን እና ራሱ ጠይቶን እንዲሁም ወቅሶና ተቆጥቶን ነው:: እንደመንግስት የህዝብን ጥያቄና ፍላጎት ማሟላት ግድ ነው” ለሚል ቀጥሎ ለሚወስዳቸው ህጋዊ መሰል ሕገወጥ እርምጃዎች የጥፋት ማካካሻ ምክንያት (excuse factor) መነሻ አድርጎ እንደሚጠቀመውም ግልጽ ነው:: የዘገየ መልስ ደግሞ ለእንዲህ አይነት ትርጉም እንደሚዳርግ ለመረዳት የፖለቲካ ተንታኝ መሆንን አይፈልግም::

## ዘንዶው ሲነቃ

“ዘንዶ ከፍ ያለ እንስሳ ከዋጠ በኋላ ያንን ፈጭቶ አብላልቶ ምግብ አድርጎ ሆዱ ባዶ እስኪሆን ድረስ ወራት ከተኛበት አይነቃም ይባላል:: በላዩ ሳር እስኪበቅልበት ድረስ ሊቆይም ይችላል:: ሲነቃ ግን በአዲስ ጉልበት እና በከፍተኛ የምግብ ፍላጎት ስለሆነ አደገኛነቱ ከፍ ይላል:: ደካማ መንግስትም ጥፋት ሲፈጽም እያየ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ጠበቅ ሳይሉ፣ ሕግንም በአግባቡ እርምጃዎች ማመሳሰያነት ሲጠቀሙባቸው እንደነበር የሩቅ ጊዜ ትውስታ አይደለም:: የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር ከሰሞኑ መውሰድ የጀመራቸው የእስር እርምጃዎችም መነጋገሪያ እና የተቃውሞ መነሻ የሆኑት በዚህ ምክንያት ይመስላል::

## እስር እንደህግ የበላይነት መገለጫ?

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ወደስልጣን ከመጡ በኋላ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት ተቀምጠው የመጀመሪያውን የመንግስታቸውን የስራ ሪፖርት ሲያቀርቡ ጥያቄዎች ተዠጎድጉደውላቸው ነበር:: በጊዜው የለውጥ ሙቀቱ ከፍ ብሎ ስለነበር እና የሙስና እና ሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀሎች ፈጽመዋል የተባሉት የሕወሓት ባለስልጣናት ጉዳይ የብዙዎች ቁጭት እና በቀል ማርጠቢያ ጥያቄ ሆኖ ስለነበር፤ “ለምን እርምጃ አልተወሰደም?” የሚል ጥያቄ ከዚህም ከዚያም ተነስቶ ነበር:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምላሻቸው አንድ ብዙዎችን ያስደነቀ እና “ከቀደመው የኢህአዴግ አስተዳደር ፍጹም የተለየ ኢህአዴግ መጣ” ያስባለ ምላሽ ሰጡ:: “ከዚህ በኋላ ማንንም ሳናጣራ አናስርም” አሉ::

ዛሬ ያ ቃል በተግባር ተተርጉሟል ወይ? አጠያያቂ ነው:: በርግጥ በጊዜው የሕወሓት ባለስልጣናት ላይ ማስረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ነው ተይዘው ክስ የተመሰረተባቸው:: ሰሩ የተባለው ወንጀልም ሰዎቹ ከመያዛቸው አስቀድሞ በዶክዩመንተሪ ተዘጋጅቶ በኢቲቪ ስለተለቀቀ፣ በህዝቡ ዘንድ “የቀደመው ኢህአዴግ ጅሃዳዊ ሃረካት ልምድ በአዲስ መልክ መከሰቱ ነወይ?” የሚል ቅሬታም አስነስቶ ነበር:: ያም ሆኖ ተጠረጠሩበት የተባለበት ወንጀል ጉዳይ ክስ ሆኖ ቀርቦባቸው ብዙዎቹ አሁንም በፍርድ ሂደት ላይ ናቸው:: በጊዜው “በሀገሪቱ ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል የሚዳኝበት ዘመን መጣ ይሆን?” የሚል ተስፋ ቢጤም ናኝቶ ነበር::

ከጊዜ በኋላ ግን “አጣርቶ ማሰር” የሚለው ቃል ተቀልብሶ በጅምላ ማሰር እየሆነ መዝለቁን ማስተዋል ተችሏል:: ቃል አልተጠበቀም:: ከሰሞኑ በብዙዎች ዘንድ መነጋገሪያ የሆነው በመላው ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ውስጥ እየተፈጸመ ያለ እስርም የዚህ እርምጃ አካል ነው ተብሎ እየተተቸ ነው:: ከእስር ዜናዎቹ ጥቂቱን እንመልከት::

## የአማራ ክልል እስር

አ.ብ.ን የአማራ ብሄር ንቅናቄ ፓርቲ ነው:: በምርጫ ቦርድ የተመዘገበ እና እውቅና ያገኘም ፓርቲ ነው:: ከሰሞኑ በአማራ ክልል ከተከሰተውና መንግስት “መፈንቅለ መንግስት” ብሎ ስም ከሰጠው ድርጊት ጋር በተያያዘ የፓርቲ አመራሮቹን ጨምሮ በባህር ዳር፣ በአዲስ አበባ እና በሀረር የሚገኙ አባላትና ደጋፊዎቹ ታፍሰው ታስረዋል:: በተለይ ክርስቲያን ታደለ ሲታሰርና ከስር ያሉት አመራሮች በሙሉ ሲለቀሙ እንዲሁም አ.ብ.ንን በመደገፋቸው ብቻ ሀረር አካባቢ የሚገኙ በርካታ ዜጎች በቁጥጥር ስር ሲውሉ ብዙዎች የጅምላ እስር ዘመን ተመልሶ መጣ ብለዋል:: አ.ብ.ን ከአመራር እስከአባላቱ ድረስ ተለቅመው ሲታሰሩበት እንደፓርቲ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር እያደረገ ያለው ተግባር ፍጹም የማይጠበቅ ስለመሆኑ መግለጫ ሰጥቷል:: በብዙዎች ግምት ግን በአማራ ክልል የድርጅቱን አባላትን ጨምሮ በርካቶች በቁጥጥር ስር የዋሉት በክልሉ ከተፈጸመው አሳዛኝ ድርጊት ጋር በተያያዘ የብ/ጀ/አሳምነው ጽጌ ኔትዎርክ በመሆናቸው እጃቸው አለበት ተብለው ነው:: በዚህ አስከፊ ወንጀል ሂደት የተሳተፉ ካሉ በርግጥም መቀጣታቸው ተገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ሰበብ በማድረግ ግን ዒላማ የተደረጉ አካላትን ማሰር ግን በመላው ሀገሪቱ በየእስር ቤቱ ታጉረው የነበሩ ብዙ ሺህ ዜጎችን ከፈታ መንግስት የሚጠበቅ ተግባር አይደለም::

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት መንፈቅለ መንግሥት ከተባለው ድርጊት ጋር በተያያዘ ከ738 በላይ ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል:: የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን በሰጠው መረጃ ደግሞ በአማራ ክልል 218 የሚሆኑ ሰዎች ታስረዋል ነው ያለው:: ይህንኑ መረጃ በጥቂት ከፍ በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አረጋግጦታል:: በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ግጭት አስነስተዋል ተብለው የተጠረጠሩ 224 ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውሎ ምርመራ እያካሄደ መሆኑን ነው ጠቅላይ ዐቃቢ ህጉ ያስታወቀው:: በቁጥጥር ሥር የዋሉት በምዕራብና በማዕከላዊ ጎንደር ዞኖች በኦሮሞ ብሄረሰብና በሰሜን ሸዋ ዞኖች እንዲሁም በቤንሻንጉል ጉሙዝ አዋሳኝ አካባቢዎች የሚገኙ መሆናቸውን ዐቃቤ ሕጉ ተናግሯል::

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ለምርጫ ቦርድ በሰጠው ሪፖርት መሰረት ደግሞ በ17 ስፍራዎች የሚገኙ 532 አባላቱ በፖሊስ

**“…. እስክንድርን እና ደጋፊዎቹን ማሰርና ማዋከብ ሊቆም ይገባል! እንዲህ የተፈራውስ ምን ድብቅ ተንኮል ቢኖር ነው ያስብላል። ስለ ዲሞክራሲ እያወራን ማንም ሰው ሃሳቡን በሰላማዊ መንገድ እንዳያራምድ መከልከል የትም አያደርስም። የተረኛነት ስሜትና የፖለቲካ መሰሪነት ሁለቱም አክሳሪና በመጨረሻም ሀገር የሚበትን ነው የሚሆነው!!!**

ማስከበር ተስኖት ተኝቶ ከከረመ በኋላ ህዝብ መንግስትነቱን ጥያቄ ውስጥ ሲከትትበት ድንገት ነቅቶ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ወደአምባገነንነት የተጠጉ ከባድ እና ሕጋዊውን ከሕገወጡ የቀላቀሉ እርምጃዎች ይሆናሉ:: እንዲህ አይነት ድንገት የሚነቃ መንግስትም ተኝቶ የነቃ ዘንዶ አይነት ስለሆነ አደገኛ ነው” ይላሉ የስነመንግስት አጥኚዎች እና የፖለቲካ ተንታኞች::

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንዲህ አይነት ክስተቶችን በጂኒ መስለው ሲገልጿቸው ተስተውሏል:: “ለዓመታት ጠርሙስ ውስጥ ታሽጎበት የኖረው ጂኒ ከጠርሙሱ ሲወጣ የሚመልሰው የለም” አይነት ንግግሮችን ለመንግስታቸው

የታሰሩበት መሆኑን አስታውቋል። የአ.ብ.ን ሕዝብ ግንኙነት ሓላፊ አቶ ክርስቲያን ታደለ በአማራው ህዝብ ላይ እየተካሄደ ያለው የጅምላ እስር በአስቸኳይ ካልቆመ ደጋፊዎቻችንን አስተባብረን በሰላማዊ መንገድ ትግላችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ብሏል። በሌላ ዜና ደግሞ ድርጅቱ ከ350 በላይ አባላቱ እና አመራሩ በእስር ላይ እንደሚገኙ ተናግሮ ነበር። ከሰሞኑ የተወሰኑት ቢለቀቁም በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ቦታዎች የአብን አባላት በስፋት በመታሰር ላይ መሆናቸውን ነው የተናገረው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የፈረሙትን የቃልኪዳን ሰነድ እንዲያከብሩም ድርጅቱ በመግለጫ ጠይቋል።

መረጃዎች እንዳሰፈሩት 738 ከሚጠጉት በተለያዩ ቦታዎች ከታሰሩት የአማራ ብሄር ተወላጆች መካከል ከፍተኛ አመራሮች፣ የፖለቲካ ድርጅት አባላት፣ ጋዜጠኞችና የሲቪክ ድርጅት አባላት ይገኙበታል። “በአዲስአበባ የሚገኙት አብዛኞቹ በቀዝቃዛና ጠባብ ክፍሎች ታስረዋል። ዘመድ እንዲጠይቃቸውም አልተደረገም። ስልኮቻቸውን ወስደው የfacebook፥ WhatsApp፥ imo እና telegram አድራሻዎቻቸው እየተበረበሩ ነው” ተብሏል።

## እስር በኦሮሚያ

ስላልተነገረለት እና ስላልተወራለት እንጂ ከአማራ ክልል በበለጠ ብቻ ሳይሆን እጅግ በባሰ ሁኔታ በኦሮሚያም እስር ተጧጡፏል እየተባለ ነው። በተለይም የክልሉ ፓርቲ ኦዴፓ በኦሮሚያ ለተከሰቱት ጥፋቶች ሁሉ ምክንያት ነው ብሎ ጣቱን የጠቆመበት “ኦነግ ሸኔ አባላት ናችሁ” ብሎ ከየቤታቸው እየወሰደ ያሰራቸው ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ ነው። በአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚመራው ኦነግ ያለው የታጠቀ ሰራዊት ክንፍ ተገንጥሎ ጫካ በመግባቱ እና ጃል መሮ በሚባለው አዛዥ እየተመራ ከማዕከላዊው ኦነግ ጋር በመቆራረጡ መንግስት በህገወጥነት ፈርጆታል። በዚህ ሳቢያም ህዝቡ ወጥቶ “ጫካ ያለው ቡድን አይወክለንም” የሚል ሰላማዊ ሰልፍ ካደረገ በኋላ ከዚህ ቡድን ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ ሁሉ ተለቅመው ታስረዋል። በአካባቢው የሰፈረው መከላከያ ሰራዊት እርምጃ እንዲወስድ በመታዘዙ የዚህ ቡድን እንቅስቃሴ ነው ብሎ የሚገምተውን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ያወድማል። በዚህ መካከል እስር ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ መብት ጥሰት ጭምር እየተካሄደ ኦሮሚያ ውስጥ ምሬት በርትቷል የሚሉ መረጃዎችም እየወጡ ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚካሄደው ጅምላ እስር ወደኔ ቤትም ገብቷል ብሏል የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ)። የፓርቲው ሊቀመንበር ፕሮፌሰር መረራ እንደሚናገሩት የኦፌኮ አባላቶች በገፍ እየታሰሩ ነው። የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) በጋራ ከ1000 በላይ አባሎቻቸው መታሰራቸውን ነው ቪኦኤ ላይ ቀርበው ያስታወቁት።

## የህሊና እስረኞች በዐቢይ ዘመን?

ብዙዎች በፖለቲካ አመለካከታቸው እና በጻፉትና በተናገሩት የሚታሰሩበት ዘመን አክትሟል ተብሎ የታሰበበት ዘመን አንድ አመት ሳያስቆጥር የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች በቁጥጥር ስር መዋላቸው ግራ አጋብቷል። ከዚህም አልፎ የሀገር መከላከያ ሰራዊትም ህዝብና ሰራዊቱን ለማጋጨት በሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች እና ሚዲያዎች ላይ ክስ ለመመስረት መዘጋጀቱን መናገሩ ሌላ ውጥረት ፈጥሯል። ይህንን ነው እስክንድር ነጋ “የህሊና እስረኞች ዛሬም በኢትዮጵያ ስላሉ ዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ እንዲፈቱ ግፊት ያድርግ” ብሎ የተናገረው።

ዘንድሮው የዓለም የፕሬስ ቀን በኢትዮጵያ ሲከበር መሰረታዊው ምክንያት ሀገሪቱ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ አንድም ጋዜጠኛ ያልታሰረባት ሀገር ሆና በመገኘቷ ነው። ይህ ቀን ከተከበረ እና ዩኔስኮም ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የሰላም ሎሬት ሽልማትን ለማበርከት ከወሰነ በኋላ የተከተሉት ጊዜያት እስር የነጠፈባቸው ሳይሆኑ የተጀመረባቸው ሆነዋል። ለምሳሌም በቅርቡ የአስራት ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ እንዲሁም የቀድሞ ዕንቁ መጽሔት ጋዜጠኛ ታስረዋል። እነዚህን ጋዜጠኞች መንግስት በጸረ ሽብር ህግ ከስሶ ሲያስራቸው ብዙዎች ታሪክ ራሷን ደገመች እያሉ ነው። አምነስቲ ኢንተርናሽናል ሰሞኑን በሰጠው መግለጫ “ኢትዮጵያ በፕሬስ ነጻነት ከነበራት ደረጃ ዳግም ቁልቁል እየተጓዘች ነው፣ ጋዜጠኞቹ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ” ብሏል።

በጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የሚመራው የአዲስ አበባ ባለአደራ ምክር ቤት ባሳለፍነው ሳምንት መጀመሪያ አካባቢ በሰጠውና በሆኑ ቡድኖች በተበተነው መግለጫ ላይ “በአዲስ አበባና ኦሮሚያ በንፁሃን ላይ በቅንጅት ህገ ወጥ የእስር ዘመቻዎች እየተፈጸሙ ነው” ብሏል። በፀረ ሽብር ሕግ የተከሰሱ የሕሊና እስረኞች በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውንም ተናግሯል።

በማህብራዊ ድረገጽ አስተያየታቸውን ያሰፈሩ እና ፍቃድ ስላልተጠየቁ ስማቸውን በዚህ ጽሁፍ ለመግለጽ ያልተቻለው ጦማሪ የባለአደራው ምክር ቤትን መንግስት ዒላማ አድርጎ አባላቱን በሰበባ ሰበብ በእስር ማመናመኑን በተመለከተ የጻፉትና ያጋሩት አስተያየት እንዲህ ይላል ።

“…. እስክንድርን እና ደጋፊዎቹን ማሰርና ማዋከብ ሊቆም ይገባል! እንዲህ የተፈራውስ ምን ድብቅ ተንኮል ቢኖር ነው ያስብላል። ስለ ዲሞክራሲ እያወራን ማንም ሰው ሃሳቡን በሰላማዊ መንገድ እንዳያራምድ መከልከል የትም አያደርስም። የተረኛነት ስሜትና የፖለቲካ መሰሪነት ሁለቱም አክሳሪና በመጨረሻም ሀገር የሚበትን ነው የሚሆነው!!! ሀገር ከተበተነ ደግሞ እመኑኝ ማንም ማንም ማንም አያተርፍም!!!! አሁንም መሆን ያለበት ሁሉም ሃሳቡን በነፃነት እንዲያራምድና ህዝብ እንዲፈርድ መተው እንጂ፣ በጥላቻ፣ በቂም ፣በተበለጥኩ ወይም በተረኛነት ስሜት ማሰብ ሁላችንንም ሀገር ያሳጣናል። ብዙዎችን ህይወታቸውን ያሳጣቸዋል። ጥቂቶች ላሽ ብለው አውሮፓና አሜሪካ ይገባሉ። አዲዮስ!!!!”

## ሕግ የበላይ እንዲሆን እስር በህግ ይሁን

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የህግ የበላይነት አለመከበር ጉዳይ ጠንክሮ መንግስታቸው ሲተች በነበረበት በዚህ ሰሞን ወደፓርላማ መጥተው በሃገሪቱ ሰሞነኛ ሁኔታ ላይ ማብራሪያ ሲሰጡ ወደእርምጃ ሊገቡ መሆኑን ያስታወቁበትን ማስጠንቀቂያ ነበር ያስቀደሙት። “ተቀምጠው የሰቀሉትን ቆሞ ማውረድ የሚቸግርበት ጊዜ እንዳይመጣ ሁሉም ሊጠነቀቅ ይገባል …በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የሚመጡ ኃይሎችን ብረት ይዘን እንዋጋቸዋለን” ነበር ያሉት።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችን እና ሕዝብን ያስመረሩ የቡድን እና ግለሰብ ማን አለብኝነቶችን ለማስቀረት እርምጃ መውሰድ መጀመራቸው ሊበረታታ እንጂ ሊነቀፍ የማይገባው ተግባር ነው። አስከፊው ነገር ግን በዚህ ሕግን የማስከበር እና የበላይነቱን የማረጋገጥ ሰበብ በመያዝ የፖለቲካ ፍላጎትን ማስፈጸም እና ስጋቶቼ የሚላቸውን አካላት ማዳከም ነው። በብዙዎች ዘንድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሁን የተጠቀሰውን ተግባር የሚፈጽም መንግስት ይዘው እየተጓዙ ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ ህግ የበላይ እንዲሆን እና እንዲከበር የግድ ዜጎች በጅምላ መታሰር የለባቸውም። አጥፊዎች እና ደህነኞች ሳይለዩ የፖለቲካ ታርጌት ውስጥ የገቡ የሚመስሉ በየእስር ቤቱ ሲገኙም ያስከፋል። ሕግ የሚከበረው ዜጎች ከጥፋት እንዲወጡ የሚያስቡ መንግስታዊ ቅንነትን እና ቀጥተኛ ፖለቲካን በመተግበር እንጂ በጥርጣሬ የተሞላ “ተረኝነት” ስሜት የተጠናወተው የፖለቲካ አቅጣጫ በመያዝ አይደለም። ፖለቲካ ሲበሰበስ ራሱንም መሸከም ያቅተውና በብዙሃን ስቃይ እና እንግልት ውስጥ ይደገፋል። ይህ ደግሞ የቀደመው ኢህአዴግም ያላዛለቀው ደርግም ቢሆን ለውድቀት ያቀረበው ምክንያት ነው። እናም የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር አስቀድሞ የተናገረውን “ሳያጣሩ ያለማሰር” እቅድ እውን ማድረግ ይጠበቅበታል። መሬት ካልወረደ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ብቻ ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው። ይህ ደግሞ አዲሲቱ የተስፋ አድማስ የተባለችውን ኢትዮጵያን የሚመሰርት ሳይሆን የሚጥል ሂደት ነው። ለሕግ የበላይነት መከበር እስር መገለጫ ሊሆን የሚችልበት ዕድል የለምና።

# ከሰሞነኛው ዕስርና ካልተሻሻለው፣ “የሽብርተኞች ሕግ” ጀርባ ምን አለ?

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ስልጣን በያዙ ማግስት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ፊት፣ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ውስጥ መሰንቀር፣ በአዕምሮውም መቅረት የቻለ ማራኪ ንግግር አደረጉ፡፡ ዜጎች ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት የከፋ በደል ሲፈፀምባቸው ከመቆየቱ ባሻገር በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችም እንደደረሱ አረጋገጡ፡፡

ከምንም በላይ ከሕዝብ ይልቅ መንግስት ሲያሸብር እንደኖረ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ ዕውን መሆንና ጭቆናን ለማስወገድ በሰላማዊ መንገድ ትግሉን ሲያካሂድ እንደኖረ በመግለፅ፣ “እኛ ነን አሸባሪዎቹ” ሲሉ በአደባባይ መሰከሩ፡፡ በተለይም በሽብርተኝነት ስም ዜጎችን ማሰር፣ መግረፍ፣ ማሰቃየት፣ ጨለማ ቤት መወርወር የፖሊስ፣ የደህንነትና የፀጥታ አካላት መደበኛ ስራ እንደነበር በመግለፅ “ከእንግዲህ በኋላ ግን ይህ አይሆንም፡፡ ፖሊስና የፀጥታ አካላት ለህግና ሕግ ብቻ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ፖሊስ የድርጅት አባል ይመስል የወገንተኝነት ስራ አይሰራም በማለት፣ “የወያኔ አጎንባሽ” የነበሩ ከከተማ እስከ ፌደራል ፖሊስ ያሉትን የሕግ አካላት ኩምሽሽ ያደረገ፣ በአንጻሩ የኢትዮጵያውያንን አንገት ቀና ያስባለ አስገራሚ ንግግር አደረጉ፡፡

በለውጡ ቡድን መሪነት ወደ አገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን እርከን የወጡት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ አስቀድሞ ስልጣን ላይ የነበረው ሕወሓት መራሹ መንግስት ይከተለው በነበረው ፖለቲካዊ ሂደት፤ ሕዝቡን አፍኖና ቀጥቅጦ ለመግዛት ያስችለው ዘንድ ባፀደቃቸውየተለያዩ ሕጎች መሀል “አስከፊ” ነው የተባለለት የሽብርተኝነት ሕጉ እንደሚሻሻልም ቃል ገብተው ነበር፡፡ በርካታ የአማራና የኦሮሞ ወጣቶች ለአራት ወራትና ከዛ በላይ ከቤተሰብ ሳይገናኙ፣ ዘግናኝ ግፍ ሲፈፀምባቸው የኖረው በዚህ የተሳሳተ ሕግ ነበር፡፡

ሕጉን ለማሻሻል ጥናት እየተደረገ ነው ቢባልም፣ ጠ/ሚኒስትሩም አገሪቱን መምራቱን ከጀመሩ አንድ ዓመት ቢያልፍም፣ የብዙዎችን ሕይወት የቀጠፈው፣ አካል ያጎደለውና ዘር ያመከነው… በአጠቃላይ ተጠርጣሪዎችን ለማሰቃየት ምቹ የሆነው የሽብር ሕግ አንዳችም ሳይሻሻል፤ አሁንም ዜጎች በሽብርተኝነት ክስ ተጠርጥረው የሚያዙበት፣ በፍርድ ቤቶችም በቀደሙት ዓመታት የተለመደው የሃያ ስምንት ቀናት ቀጠሮ (ለአራት ጊዜ) የሚተገበርበትን አሰራር ለማየት በቅተናል፡፡

ሰሞኑን ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉት ግለሰቦችን ጉዳይ በተመለከተ፤ “የፖሊስ የክስ አቀራረብ ይዘት ሕወሓት መራሹ መንግስት ከሚጠቀማቸው የፈጠጡ ድርጊቶች ጋር በእጅጉ የሚቀራረቡ ናቸው” የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው፡፡ የጠ/ሚ/ር ዐቢይ መንግስት በፍትህ ተቋሙ ላይ እንደወሰደው ዓይነት ተገቢና ትክክለኛ ዕርምጃ በፖሊስና ደህንነት መ/ቤቱ አካባቢ ባለመተግበሩ፣ በብቃትና ዕውቀት ረገድ አጠያያቂ የሆኑ፤ ብሎም ስልጣን ላይ ከነበረው አካል ጋር በጥልቀት የተነካኩ ሰዎች አሁንም በየቦታው የተሰገሰጉ መሆናቸው “የማይሻሻሉ የማይመስሉ” ነገሮችን ዛሬም እንድንመለከት አስችሎናል፡፡ እነዚህ የፀጥታ ተቋማት በገለልተኛና በትክክለኛ ሙያዊ የአመራር ብቃት ባላቸው ሰዎች መቀየር ባለመቻሉ ወደ ፊት ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ይህን ስንል፣ ሰዎች ለምን በሽብርተኝነት ተጠረጠሩ? ከሚል እሳቤ ሳይሆን የሽብርተኝነት ሕጉ በራሱ ተጠርጣዎችን ለመብት ረገጣ የሚያጋልጥ መሆኑ፣ እግረ መንገድም ሰሞኑን ከተለያየ አቅጣጫ እንደሚሰሙት ዓይነት ጥፋቶች እንዳይከሰቱ ከመስጋት ጭምርም ነው፡፡ አንድ መንግስት “አስነዋሪና አሳዛኝ ነው” ብሎ፣ እንደሚያሻሽለውም ማረጋገጫ በሰጠበት አዋጅ እንደገና ወደ ኋላ ተመልሶ፣ በዛው መንገድ እየተጓዘ ተመሳሳይ ክስ መመስረት በራሱ ብዙ የሚያስነሳቸው ጥያቄዎችና ቅሬታዎች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም፡፡

በሌላ በኩል በዝምታ ውስጥ ተሸብቦ የነበረው የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ መንግስት ሰሞኑን በአዲስ አበባ፣ በአማራና ኦሮሚያ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን በማሰር ላይ እንደሆነ ተሰምቷል፡፡ ግለሰቦቹ የሚያዙበት መንገድ በአብዛኛው የሕግ አግባብን ተከትሎ አለመሆኑ ደግሞ ዜጎች ተስፋ ባደረጉበት የለውጥ ቡድንና የአገሪቱ አመራሮች ላይ ጥርጣሬን እንዲያነሱ በር ከፍቷል፡፡ “ፖሊስ ያለ ፍርድ ቤት መያዣ ማንንም ቢሆን አንጠልጥሎ መውሰድ ወይም መያዝ አይችልም” የሚለው መግለጫ ተረስቶ፣ በማንአለብኝነት በአደባባይ የፈለጉትን ሰው እየጎተቱ (ካሻቸውም እየቀጠቀጡ) የሚወስዱ የሕግ አካላት በብዛት እንዳሉም እየሰማን ነው፡፡

አገሪቱ ካለችበት ፖለቲካዊ ውጥረት አኳያ መንግስት የወሰደው የኃይል ዕርምጃ ተገቢ መሆኑ በምንም መልኩ ባያጠራጥርም የፀጥታ አካላት ተጠርጣሪን እንደ ጠላት፣ ራሳቸውን እንደ ታማኝ የኢህአዴግ አገልጋይ፤ ወይም እንደመጡበት ብሔር ተኮር ፓርቲ “ጉዳይ አስፈፃሚ” አድርገው የሚመለከቱበት መንገድ በፍጥነት ሊታረም ይገባል፡፡ ማንኛውም ዜጋ ሲያዝ ሕጋዊ መብቱ ተከብሮ፣ የፍ/ቤት መያዣ ወጥቶለት፣ የፀጥታ ኃይሎችም በስርዓቱና ሕግን በተከተለ መንገድ ሊወስዱት እንደሚችሉ ማወቅ ብሎም ከቤተሰብም ሆነ ከጠበቃቸው ጋር በተገቢው መንገድ መገናኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በመጨረሻም ደግመን ደጋግመን የምንመክረው መላ ኢትዮጵያውንን ያላቀሰው፣ ዘላለም ከብዙዎች ሕሊና በመጥፎ ገፅታ የተሰነቀረው የሽብርተኝነት ሕጉ እግረ መንገድ የፖለቲካ ልዩነት ኖሯቸው፣ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ ሌሎች አካላትን መበቀያ እንዳይሆን በዚህ የፀረ ሕግ ማንም መዳኝት ስለሌለበት በአዲስ እንዲሻሻል የተዘጋጀውን ሕግ ወደ ተግባር ማምጣት አስፈላጊም ተገቢም መሆኑን ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**

**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**

ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**

ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ

ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**

ብሩክ መኮንን

ፍቅርተ ተሾመ

ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**

ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)

ተረፈ ወርቁ

ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**

ፍፁም ንጉሴ

**ጸሐፊ**

ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09

የቤት ቁጥር 552/1

አምባቸው ህንፃ 2ተኛ

ፎቅ ቢሮ ቁ. 207

ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029

ስልክ ፡ +251 911 22 76 61

+251 912 165606

+251 118 12 2333

ኢ-ሜይል፡

enqu2013@ gmail.com

Ghion2011meg@gmail.com

**Facebook**

Gihon-meg Fekadu

www. facebook.com/enqu2013



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም




**አታሚ**

ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ

ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ

0911223335/ 0911420506

# እስከመቼ ነው ክልሎችን "ሉዓላዊ ናችሁ" እያልን የምንሸነግላቸው?



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

ባለፉት ወራት በወጡ በርካታ የሕትመት ውጤቶች በርካታ ምሁራን ሥለ ሉዓላዊነት ያላቸውን እውቀት አካፍለውናል፡፡ ከእነዚህ ትንታኔዎች ተነስተን የምናገኘው ትርጉም ሉዓላዊ ክልል ወይም መንግስት ማለት በራሱ የውስጥ ጉዳይ ማንንም ሳያማክር መወሰን የሚችል፣ የራሱን ሕግ ማርቀቅ፣ ርዕዮት ዓለም መምራት የሚችል፣ በአለም አቀፍ ተቋማት ማለት UN, EU እውቅና ያለው፣ ከማንኛውም አለማቀፋዊ ተቋም ጋር ሕጋዊ ውል መዋዋል የሚችል፣ ውሉ ችግር ሲገጥመው መክሰስንም መከሰስንም የሚያጠቃልል መብት ያለው፣ በአየር ክልሉ ላይ ለብቻው መወሰን የሚችል፣ ከማንኛውም አለማቀፋዊ ተቋም ጋር ሕጋዊ ውል መዋዋል የሚያስችል መብት ያለው፣ የራሱን ገንዘብ ማተም የሚችል፣ የራሱን ፓስፖርት መጠቀም የሚችል… የመሳሰሉትን መብቶች የተጎናፀፈ አገር ወይም ክልል ሉዓላዊ የሚለው ማዕረግ ይኖረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 39 የኢትዮጵያ ብሄር ብሄሬሴቦች እራስን በራስ ማስተዳደር እስከ መገንጠል ሲል በመጀመሪያ እራስን በራስ ማስተዳደር እንዴት? በየትኛው የሐብት ምንጭ፣ በየትኛው መብት? የሚለውን ሁኔታ ለመዘርዘር አልሞከረም፡፡ ሁለተኛ ክልሎች ተጠሪነታቸው ለማዕከላዊ መንግስት ሳይሆን ለራሳቸው ሲሆን፣ በዚህ መልኩ በክልላቸው ያሉትን ሕዝቦች እንዴት አድርገው ነው ፍትሐዊ አገልግሎት መሥጠት የሚችሉበትን መንገድ አላስቀመጠም፡፡ ይህ ማለት የክልል ባለስልጣናት ችግር ሲፈጥሩ ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ፣ ባለሐብቶች ወይም ዜጎች በክልሎች ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት ሲያቅታቸው ወደ ሌላ ከፍተኛ ተቋም በመሄድ አገልግት ማግኘት የሚችሉበትን አሠራርም አላስቀመጠም፡፡

በመሆኑም ባለፉት ሩብ ክፍለ ዘመን ይዘን የተጓዝነው ሕገ መንግስት የወንጀል ሰነድ ነው ቢባል በእጅጉ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ሉዓላዊ መብት ሊኖራቸው የማይችሉ ክልሎችን "ሉዓላዊ ናችሁ" እያለ የሚሸነግል ሕገ መንግስት በመሆኑ ነው፡፡

የክልሎች ድንበር (ጠ/ሚ/ር ዐቢይ እንደተናገሩት አስተዳደራዊ ድንበር) ከሆነ አስተዳደራዊ ድንበር በማንኛውም ጊዜ ያለ ብዙ ውይይት መለዋወጥ ይቻላል፡፡

ለምሣሌ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የቀበሌዎችን ድንበር በፈለገው ጊዜና ወቅት ባጭር ጊዜ መለዋወጥ ይችላል፡፡ ሕዝቦችም ምንም ቅሬታ አያቀርቡም፡፡ አሁን ግን በክልሎች ያለው ድንበር የአገር ድንበርነት ሥሜት ሥለ አለ "የአገሬ ድንበር አይነካም" የሚል አይነት ሥሜት ስለበዛ የክልሎች ድንበር የፀብ፣ የጦርነት ምክንያት እየሆነ ያለው፡፡

በመሆኑም ስለ ክልሎች ድንበር ማውራታችንን ትተን በመጀመሪያ ደረጃ ሕገ መንግስቱን ግልፅ በሆነ አማርኛ "ክልል ማለት የተገደበ ሥልጣን ያለው፣ በፌደራል መንግስት ሥር የሆነ፣ የአንድ አገር ክፍልፋይ አስተዳደር ወይም subrigion" ተብሎ በግል መቀመጥ የመጀመሪያ ሥራ መሆን አለበት፡፡

ባለፉት ዓመታት በተጨባጭ ማየት እንደታቸለው የክልል ባለሰልጣናት በክልል ሕዝቦች ላይ እንደ መዥገር ተለጥፈው፣ የክልሉን በጀት እንደፈለጉ መጫወቻ አድርገው፣ የክልል ሕዝቦችን ለድህነት መዳረግ ቻሉ እንጂ በራሳቸው መንገድ ሄደው ሕዝቡን ተጠቃሚ ያደረገ ተግባር መከወን አልቻሉም፡፡

ሌላው ቢቀር ደፍረው የሄዱ ባለሀብቶችን እንኳን በአግባቡ ማስተናገድ አልቻሉም፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበላሸና ወደ መፈናቀል፣ እርስ በርስ ግጭት፣ በዚች ድሃ አገር ያፈራናትን ትንሿን ሐብት እስከማውደም የደረሰ ተግባር ማየት የተለመደ እየሆነ መጥቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ላይ ምንም ጊዜ ሳናባክን እርምጃ መውሰድ ለነገ የሚባል ተግባር አይደለም፡፡

ክልሎች ልማትን በተመለከተ የፌደራል መንግስት ያለው ተቋማት መቼም አይኖራቸውም፡፡ ለምሣሌ የፌደራል መንግስት እንደ ሲቪል አቬሽን፣ ባቡር ኮርፐሬሽን፣ የማዕድን ሚኒስቴር የመሳሰሉ ከፍተኛ ኤክስፐርቶች ያሉባቸው መስሪያ ቤቶች አሉት፡፡ እነዚህ ተቋማት ሊሰሩት የሚችሉትን ሥራ መቼም ክልሎች መሥራት የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡ በመሆኑ እነዚህን የመሳሰሉ መሥሪያ ቤቶች አንድ ተግባር ለመፈፀም ሲነሱ ክልሎች በምንም መልኩ ችግር ፈጣሪ መሆን የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር የለበትም፡፡ የታዘዙትን እሺ ብለው ነው መፈፀም ያለባቸው፡፡

እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ክልሎች ብዙ ችግር በመፍጠራቸው በርካታ የልማት ተግባራት በተፈለገው ፍጥነት መከናወን አልቻሉም ወይም የተሳሳተ የሉዓላዊነት ሥሜት ስላላቸው፡፡ ስለ ሉዓላዊነት ስናነሳ የአውሮፓ ሕብረት አገሮች ጥሩ ምሳሌ ስለሚሆኑ እዚህ ላይ መጥቀሱ በእጅጉ ትምህርት ሰጪ ነው፡፡

የአውሮፓ ሕብረት አባል አገሮች ሁሉም የራሳቸው የሆነ ሉዓላዊ መብት ያላቸው አገሮች ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ አገሮች ካላቸው ሉዓላዊ ሥልጣን ቀንሰው እንደ ገንዘብ ማተም፣ በጋራ የውጭ ፖሊሲ ማራመድ፣ የጋራ ኢንዱስትሪ ስታንዳርድ፣ የጋራ የጠፈር ምርምር ተቋም ተግባራትን ለአውሮፓ ሕብረት በፍቃደኝነት በመሥጠት የጋራ ተጠቃሚ ለመሆን ችለዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ አገሮች በጋራም ሆነ በተናጠል በፈለጉት ጊዜ ይህንን መብት መልሰው ለራሳቸው መውሰድ ይችላሉ፡፡

እነዚህ የአውሮፓ አገሮች በአመዛኙ ውሕደታቸው ኢኮኖሚያዊ ነው፡፡ በፖለቲካው መስመር አሁንም ሁሉም አገሮች የራሳቸውን ፓስፖርት ያትማሉ፣ ሁሉም አገሮች ኤምባሲዎች በየአገሩ አሉዋቸው፡፡ ይህንን የመሳሰሉ መብታቸውን አሳልፈው ለሕብረቱ ለመስጠት እስከ አሁን ቁርጠኝነት አላሳዩም ወይም አውሮፓዊ ብሄርተኝነትን መፍጠር አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም በርካታ መቶ አመታት ይዘውት የቆዩትን ማንነት እንዲህ በቀላሉ ለመተው ወኔው ሊኖራቸው አልቻለም፡፡

አውሮፓውያን አለምን ይገዙ በነበረበት ጊዜ፣ በሳይንስ በቴክኖሎጂ እጅግ የበላይ በነበሩበት ወቅት እጅግ ድሃ አገር የነበረችው ቻይና አንድነቷን ጠብቃ፣ ሰፊ አገርና ሕዝብ ይዛ፣ ጠንካራ አመራር ታክሎበት ብቅ በማለቷ ዛሬ አውሮፓውያንን በልጣ የአለም ታላቋ አገር (በኢኮኖሚና በሌሎችም ዘርፎች) ለመሆን ትንሽ ነው የቀራት፡፡ በሌላ አነጋገር የአውሮፓ አገሮች ለታሪካዊ ሉዓላዊነታቸው የሰጡት የተጋነነ ቦታ ወደ ድሕነት እየመራቸው ነው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን ከዚህ ብዙ መማር አለብን፡፡ ያለፈውን ሳይሆን የወደፊቱን ነው መመልከት ያለብን፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ክልሎች ባለፉት አንድ ዓመት ይህንን ሁሉ ዜጋ ለዘመናት ከኖረበት ቦታ ለማፈናቀል ወኔ ያገኙት እሚፈሩት ነገር ስላጡና እራሳቸውን እንደ ሉዓላዊ አገር ስለቆጠሩ ነው፡፡ የፌደራል መንግስት የመጀመሪያው ሰው ሲፈናቀል እርምጃ ለመውሰድ ወኔ እና ስልጣን ቢኖረው ኖሮ ይህ ሁሉ አደጋ ባልደረሰ ነበር፡፡

በመጨረሻም ጠ/ሚ/ር ዐቢይ እንዳሉት ሕገ መንግስቱ ላይ ግን ግልፅ በሆነ ቋንቋ ያልተቀመጠው የክልሎች የስልጣን መጠን የግድ በፍጥነት ተስተካክሎ፣ ክልሎች ተቆርሶ የተሰጣቸውን ስልጣን ብቻ ተግባራዊ እያደረጉ ያለንን ጊዜና ገንዘብ ድሕነትን ለመዋጋት ብቻ ብንጠቀምበት የተሻለ ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

# አዲሱ መንግሥት "በፕሬስ ላይ ባለው አቋም" ወቀሳና ትችት እየቀረበበት ነው!

Committee to Protect Journalists

የኢትዮጵያ መንግሥት "ህግና ሥርዓትን ለማስከበር በሚል ሽፋን" የጀመረውን ጋዜጠኞችን የማሰር ዘመቻ በመቃወም ሁለት ዓለም አቀፍ ተቋማት መግለጫ አውጥተዋል፡፡

በመላው ዓለም ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸው የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ዓለም ዓቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ሲፒጄ በተናጠል ባወጧቸው ወቅታዊ መግለጫዎች "ሰኔ 15 በአማራ ክልል ተሞክሮ ከሸፈ" ከተባለው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ ጋዜጠኞችን በስም ጠቅሰው የመንግሥትን እርምጃ በፅኑ አውግዘዋል፡፡

"ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን ከመጡ ወዲህ በሚዲያ ነፃነት ላይ ድንቅ እመርታ እየታየ የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ሁኔታዎች የመቀልበስ አደጋ ተጋርጦባቸዋል" ያለው የአምነስቲ መግለጫ "ይህ በአዲስ መልክ የተጀመረው ጋዜጠኞችን የማሰር ዘመቻ የታየውን የፕሬስ ነፃነት ወደ ኋላ የሚመልስ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የታሰሩ ጋዜጠኞችን በአስቸኳይ ይፍታ፤ ክሳቸውም አሁኑኑ ውድቅ ይደረግ" ሲል አቋሙን አስታውቋል፡፡

ዓለም ዓቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ሲፒጄ በበኩሉ "ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው የመገናኛ ብዙሃንን የመቆጣጠርና ጋዜጠኞችን የማሰር ሁኔታ ቀድሞ ወደነበረበት ጭቆና እንዳይመለስ ስጋት አለኝ" በማለት ገልፆ "ይህ ሁኔታ በዚህ የሚቀጥል ከሆነ የሀገሪቷ መገናኛ ብዙሃን የወደፊት ዕጣ ፈንታን አሳሳቢ ያደርገዋል" ብሏል፡፡

በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ የተሰማሩ እና ለሙያው ቅርበት ያላቸው ሰዎች ስለሁኔታው ምን እንደሚሰማቸው ጠይቆ ሀሳባቸውን ያካተተው የሲፒጄ መግለጫ በሁኔታው ላይ የመንግሥትን አቋም ለመረዳትም የመንግሥት ቃል አቀባይዋ ቢልለኔ ስዩምን ማነጋገሩን ጠቅሷል፡፡

በአማራ ክልል ሰኔ 15 ተሞከረ የተባለውን መፈንቅለ መንግሥት ተከትሎ የኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጡና "ጨቋኝ ነው" የተባለው የፀረ ሽብር ሕግ ተመልሶ ለጋዜጠኞች እስር መዋሉ እጅግ አሳሳቢና አደገኛ አካሄድ መሆኑን ያወሳው የሲፒጄ መግለጫ "ለውጥ እየተካሄደ ባለበት በአሁኑ ወቅት መንግስት የኢትዮጵያ ፕሬስን ለመቆጣጠር አሮጌውን ዘዴ እየተጠቀመ ነው" ሲል ድርጊቱን ኮንኖታል፡፡

በአሁኑ ወቅት በእስር እንዲቆዩ ተደርገው ከሚገኙት ጋዜጠኞች መካከል የአስራት ቴሌቪዥን ዋና አዘጋጅ በሪሁን አዳነ እና የቀድሞዋ ዕንቁ መጽሔት ዋና አዘጋጅና የአዲስ አበባ ባለአደራ ም/ቤት ፀሐፊ ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ የሚመራው አዲስ የለውጥ መንግሥት ጋዜጠኞችን በማሰር ዓለም ዓቀፍ ወቀሳን ማስተናገድ ከመጀመሩ በፊትም፣ በተለይ በነፃው ፕሬስ ላይ የሚከተለው አቋም ግልፅ ያልሆነና ከቀድሞው የተሻለ መሆኑን ለመገምገም አዳጋች እንደሆነ፣ በተለይም በሙያው ውስጥ ባሉ ጋዜጠኞች አስተያየት ሲሰጥበት ነው የቆየው፡፡

የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞችን የማግለልና እንደ ዴሞክራሲ አጋዥ ቆጥሮ በሂደቱ ተሳታፊ ያለማድረግ፣ አልፎም በጠላትነት የመፈረጅ ዝንባሌ የነበረው የቀድሞው የሀገሪቱ መንግሥት በነፃ ፕሬስ ውጤቶችና በአዘጋጆቹ ላይ እጅግ ከፍተኛ ወከባና ጥቃት ሲፈፀም መኖሩን ያወሱ ሙያተኞች እንደሚሉት፤ አሁን በሀገሪቱ መንግስታዊ የሥርዓት ለውጥ እውን ሆኗል ቢባልም በነፃ ፕሬስ አኳያ ይሄ ነው የሚባል ለውጥ አልታየም፡፡ ይልቁንም ቀድሞ የነበሩ ችግሮች ሁሉ አሁንም እንዳሉ ናቸው፡፡

"ከለውጡ መንግሥት የምንጠብቀው እጅግ ዘርፈ ብዙ አዳዲስ ዕይታዎችና እርምጃዎች የነበሩ ቢሆንም አንዳችም አይነት የተለወጠ ነገር አላየንም" በማለት አስተያየቱን የሰጠ ነባር የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኛ "የጠ/ሚ/ር ዐቢይ መንግሥት በመንግስታዊ መግለጫዎች የነፃ ፕሬስ ተቋማትን ያለመጥራትና የማግለል ዝንባሌን ከማሳየቱም አልፎ፤ አሁን በወረቀት ዋጋ ላይ በፍጥነት እየተከሰተ ያለው የዋጋ ጭማሪም መንግሥት ለነፃ ፕሬስ ያለውን አሉታዊ አመለካከት በግልፅ የሚያመላክት ነው" ብሏል፡፡

"መንግሥታዊ የሥርዓት ለውጡ እውን እንዲሆን ከቁሮ እና ፋኖ በላይ ለአመታት ሲታገል የቆየው የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ቢሆንም አዲሱ መንግሥት ለዚህ እውቅና መስጠት አይፈልግም" ያሉ ሌላ አንጋፋ የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኛ በበኩላቸው "የለውጡ መምጣት ለፕሬስ ዕድገትና መጠናከር የላቀ አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል ተስፋ ተፈጥሮብን የነበረ ቢሆንም፤ እየታየ ያለው ነገር ሁሉ የቀድሞውን አፋኝ ስርዓት የሚያስታውሰን እንጂ መንግሥት ለነፃ ፕሬስ ያለውን ቀናዒ አመለካከት የሚያሳይ አይደለም" በማለት ሁኔታውን በምሬት ገልፀዋል፡፡

ሲፒጄ ያነጋገራቸው የመንግሥት ቃል አቀባይዋ ቢልለኔ ስዩም ለሀገሪቱ መገናኛ ብዙሃን አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር መንግስት ቁርጠኛ መሆኑን ቢገልፁም፤ በአብዛኛው የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ዘንድ ግን ይህ የቃል አቀባይዋ ሀሳብ ከወሬ በዘለለ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ ለዚህ ደግሞ እርሳቸው የሚመሩት የጠ/ሚኒስትሩ ፕሬስ ሴክሬተሪያት በየትኛውም መንግስታዊ መግለጫዎች የነፃ ፕሬስ ተቋማትን አለመጋበዙና ለሚዲያዎች በሚበተን የጥሪ ማስታወቂያም የነፃ ፕሬስ ሚ ዲያ ተቋማትን የማግለል ግልፅ አቋማቸው የ ሚንፀባረቅ መሆኑ በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

በነፃ ፕሬስ የህትመት ሚዲያ ውጤቶች ላይ በአዘጋጅነት የሚሰሩ አብዛኛዎቹ ጋዜጠኞች የለውጥ መንግሥቱ ላይ የበዛ ተስፋ የነበራቸው ቢሆንም፤ በሂደት እየታየ ያለው የመንግሥቱ አቋም ግን ተስፋቸውን የሚያለመልም ሊሆን አልቻለም፡፡ ሀገራዊ የስርዓት ለውጡ በህዝቡ ዘንድ ድጋፍና ተቀባይነት እንዲያገኝ ከማድረግ ጀምሮ ለውጡ እንዳይቀለበስ ሁሉም ነቅቶ መጠበቅና ማገዝ እንዳለበት እስከ ማንቃት ባለው ጠንካራ ሀገራዊ ተልዕኮ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን የላቀ ፋይዳ ያለውን ተግባር ሲወጣ የቆየው የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ዛሬም ከፈተናዎች የወጣና ከስጋት የተላቀቀ እንዳይሆን እየተደረገ ነው የሚገኘው፡፡

እንደ ብዙኃኑ የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች እምነት ከሆነ አዲሱ መንግሥት የነፃ ፕሬስ ዘርፉን ለማሳደግና ለመደገፍ አንዳችም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ካለማድረጉም ባሻገር፣ ከቀድሞው አፋኝ ስርዓት በተሻለ መልኩ ይህ ነው ተብሎ የሚጠቀስ ተግባራዊ የለውጥ እርምጃዎችን ሊወስድም አልታየም፡፡

የወረቀት ዋጋን ከማረጋጋት ጀምሮ የጋዜጠኞችን አቅም የማሳደግ፣ መንግሥታዊ መ/ቤቶችን ለመረጃ ክፍት የማድረግ፣ ከመንግስታዊ የሚዲያ ተቋማት ባልተናነሰ ፍትሃዊ የማስታወቂያ ክፍፍል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማስቻል እና ለለውጡ ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ በይፋ እውቅና የመስጠት እርምጃዎችን ይወስዳል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የቆየው የለውጡ መንግሥት ይባስ ብሎ ጋዜጠኞችን ወደ ማሰርና የቀድሞው አምባገነን ሥርዓት "ሆነ ብሎ ዜጎችን ለማፈን እንዲጠቀመው ባፀደቀው" የፀረ ሽብር ህግ ጋዜጠኞችን ተጠያቂ ወደማድረግ እርምጃ መሸጋገሩ በአብዛኛው የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኛ ዘንድ ቅሬታ፣ ስጋትና ጥርጣሬን እየፈጠረ ይገኛል፡፡



ተሾመ ሽፈራው

# የማንነት’ ፖለቲካ፤ የኢትዮጵያ ፍፃሜ

**“የለህም እንዳንል፣ ይነጋል ይመሻል አለህም እንዳንል፣ እንዲህ ይደረጋል።”...**

እስተዳደራዊ በደል ቁም ስቅሉን ካሳየው ከቀድሞው የኢትዮጵያ ሕዝብ የወጣ እንባ - እንባ የሚል ግጥማዊ ተረት ጥልፍልፉ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ንፁሃኑን የጦስ ዶሮ ማድረጉን ቀጥሎበታል። የሚጎነጎነው የሴራው ሀረግ ይበልጥ እየተጫነብን ነው። ከጥንቱም ጀምሮ ሴረኛውና የሴራ ሰለባው ድብልቅልቅ እንዳለብን ነው። ዛሬም፤ አሁንም ህዝባዊውና የፀረ ህዝባዊውን መለየት ቸግሮናል፤ ባንዳና አርበኛው ተምታቶብናል። በራሱ ወገን ላይ ሰይፍ ከሚመዘው ከጨካኙ ከካችምናው የኢትዮጵያ ፖለቲካ አልማር ያለው የዚህ ዘመን ፖለቲካችን ጀግና ልጆቻችንን ከመሬት እየደባለቀብን ነው።

ለብሄራዊ ውድቀት /national shame/ ላይ ከጣለን እርስ በርስ በመጠሳጠስ የሚታወቀው የቀደመው ታሪካችን እነሆ ዛሬም ነፍስ መዝራቱን ቆመን እያየን ነው። ዘመን አሽሟጣጩ ዛሬም ያንን የእርስ በርስ የመጫረስ ገድላችንን እያስታወሰን ነው። ኢትዮጵያን ያድናል ያልነው ኢትዮጵያን ሲገድላት እያየን፤ ህዝብ ያሻግራል ያልነው ህዝቡን ሲያስለቅስ እያየን ነው። መሬት ያለው መራራ ሀቅ ይሄው ነው። እንዲያውም የዚህ ዘመኑ መጠላለፍ የእኛው ዘመን የፖለቲካ ገመድ መሳሳብ ከባለፉት የኢትዮጵያ የሴራ ፖለቲካ ሺህ እጥፍ አጥፊ፣ ጨካኝ ነው። አትጠራጠሩ ከዚያ ካለፍንበት የደም አፍሳሹ “አዋራጅ” የፖለቲካ ህይወታችን በክፋቱ የኛውን ዘመን መጠላለፍ የሚሆነው የለም።

ምክንያቱም የዚያ ዘመኑ “መጨራረስ” ከመደብ ቅራኔ ወይ ደግሞ ከስልጣን ጥም የሚመነጭ ነው። የእኛን ዘመኑን ይበልጥ “ትራጄዲ” የሚያደርገው ነገርየው የብሔር ታርጋ መለጠፉ ነው። ከብሔር የተወለደ “መቃቃር” ደግሞ የጭካኔው ልክ ወደር- ወሰን የለውም። እንዲህ ብሄራዊነት እየኮሰለመነ፣ ብሔርተኝነት እየገነነ ለማየታችን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቀንቃኞች ለብዙ ክረምትና በጋዎች የደከሙበት የወዛቸው ውጤት ነው።

በዳይና ተበዳይ፤ ጨቋኝና ተጨቋኝ ማኅበረሰብ አለ ብሎ በተበላሸ የፖለቂካ “ቀኖና” መሰረቱን የጣለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተባለው የተምታታ የፖለቲካ ርዮት መቸም ያላደረሰብን ግፍ፣ ያላስተማረን መጨካከን፣ ያላጠፋብን ማንነት፣ ያላጎደለብን ዕሴት፣ ያልሰረቀን ታሪክ፣ ያላሸከመን- ያላወረደብን ነውር የለም። ከዚሁ ከብሔር ማህፀን ከተወለደው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የጡት ልጅ የሆነው የዐቢይ ሥርዓተ - መንግስት የብሔር ፖለቲካ ሰለባ እየሆነ እያየነው ነው። እውነት ነው፤ አዲስ ስርዓት በአሮጌው ባዕል መጎተቱ አይቀሬ የሽግግር ወቅት ወግ - ልማድ ነው። ይሄ ግን (አዲስ ተብዬው ቅርፀ መንግስት) እንደዛ አይመስልም የውስጥ ሞራው ሲነበብ።

ሽግሽጉ የስርዓት ሳይሆን የስም፣ ስር ነቀል ሳይሆን የጥገና “ቅይይር” መሆኑን እንደ ብርሃን አምድ ቦግ አድርጎ እያሳየን ነው። ያኖረን “የዜግነት ፖለቲካ” ተጠየቅም ሳይኖበት በተቃራኒው ከኢትዮጵያዊነትና ከሰውነት የወረደ “ሰውነትን” በነገድና በቋንቋ ቁና እየሰፈረ መደብ በሚፈጥረው “ማንነት” የሚሉትን የፖለቲካ ዘሩን የዘራው አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ የዘራውን እያሳጨደን ነው ዛሬ። ከሕወሓት ጭብጥ ውስጥ ፈልቅቀው የአራት ክሱቶቹ ብሶት በወለደው “የኦዴፓ” ጀግኖች ቢነጠቅም አሁንም ርቆ እንዳልራቀ የመቃብር ቤቱን ፈንቅሎ፣ አፈሩን ምሶ ለመነሳቱ ምልክቶችን ጣል ጣል እያደረ ነው።

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ልጆች ክንዳቸው አልዛለም፤ ከሴረኛው ፖለቲካችን አልራቁም። ሕወሓት በተለይ ከቅርቡ ጊዜ ወዲህ ከማዕከላዊ መንግስት መራቁ ከደረሰበት ድንጋጤው ተላቆ ፤ ከቅስም ስብራቱ አገግሞ፣ ከወደቀበት አንሰራርቶ በዘወርዋራ የደባ ፖለቲካችን ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የጀመረ ይመስላል። በእርግጥ ይሄ መላምት ነው። ሕወሓት የገዛ ሕዝቡን በደባ ፖለቲካ ውስጥ አስገብቶ የማስጨነቅ ተክለ ስብዕና ያለው ጨካኝ ፓርቲ ስለሆነ እንጂ በሚታማው ልክ ላይሆንም ይችላል። ያው የጊዜ ወንፊት ያጠራዋል፤ መቼም እየሆነ ያለው በማን እና እንዴት እየተፈፀምብን እንደሆነ።

አንድ ሃቅ አለ፤ ዘመኑን የሚዋጅ “የዘመኑ” ኪሎን ቤተ መንግስት ቁልፍ የወሰዱት የአባገዳ ጋሜዎች ከመጡበት ባለፉት 15 ወራቶች ውስጥ ያየነው ይሄንኑ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባህሪ ነው። ለዚህም ነው በሕወሓት እና በተረኛ ኦዴፓ መካከል ስውር “ያልተቀደሰ ጋብቻ” አለ እያለ ሀገሬው በአደባባይ የሚያንሾካሹከው።

**. . .በእንዲህ አይነት እርስ በርስ “የመጠሳጠስ” አባዜ በወረሰው የኢትዮጵያ ፖለቲካ በሚመዘዘው ሰይፍ ለሚሰኪኑ ህዝብ እንደተረፈ፤ የትኛው ትክክለኛ የህዘብ ልጅ፤ የትኛው ነፃ አውጭያችን እንደሆነ መለየት እንደቸገረን አለን. . .**

ይሄን ህዝባዊ ጉምጉምታ፣ ይሄን ጠሃይ የመታው ሀሜት እውነት የሚያስመስለው ደግሞ አልፎ አልፎ የሚከሰቱብን ረቂቅ የፖለቲካ ሴራዎች ናቸው። የቀድሞው አምባገነኑ ሕወሓት አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ተሰይሞ የኢትዮጵያን ማህበረ- ፖለቲካ አቅጣጫ የሚቀያይርበትን “ሪሞቱን” በዘመን መተዳደሪያ መርዕ “ሰይፍ ሳይሆን ሀሳብ ይገዛል” በሚባልበት ስልጡኑ 21ኛው ክ/ ዘመን መሸነፍን በሞት ሂሳብ ማወራረድ የጅል ፖለቲከኛ ቀመር ነው።ጣናን ደረቷ፣ አባይን መቀነቷ ባደረገችው ውቢቷ ባህር-ዳር ላይ የተፈፀመው የጠራራ ፀሃይ ግፍ ማንም ይፈፅመው ማንም በሃሳብ ዘመን “ሰይፍን የመዘዘ” የሰነፍ ፖለቲከኛ አዋጭ ያልሆነ የመጨረሻ ውሳኔ ነው። በተረፈ በቀድሞ በሀገሪቱ አስጨናቂ ወቅቷቾ እንደ ጋለ ናስ እየተቀጠቀጡ፤ ያንን መረራ ዘመን እንደ ብረት ጠንክረው የዛሬን ጠሃይ ያነጉልንን፤ ከጀነራሉ እስከ ዶክተሩ ድረስ ያሉትን “ከንቱ” ▶

መስዋዕትነት የገበሩ ድንቅ የህዝብ ልጆች ሁሌም በመራራ ሃዘን የምናስታውሳቸው ናቸው። እንኳንስ ዶ/ር አምባቸው ይቅርና ቃታውን ስቦ ገድሎታል የተባለው ጀነራል አሳምነው ጽጌም ሞታቸው፤ ያው የእምዬ ኢትዮጵያም ሞቷ ነው፤ እንኳንስ ለእልፍ ዘመናት "በትንሽ ትልቁ አውደ ውጊያ ላይ ሳት በጆሮ ግንዱ እያፏጨበት ዘመኑን የገፋው ጀነራል ሰዓረ ይቅርና በታላቁ ሰው ላይ ጨክኗል የተባለው የሰዓረ ገዳዩም ሞት፤ ያው የአገርም ነው ሞቱ።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዲህ ነው፤ ራሱን በራሱ ቅርጥፍ አድርጎ የሚበላ "ኦክቶፐስ" አሳ አይነት ነገር ነው። ቀን በጎደለበት ጀንበር የራሱን ስጋ(ዘር) ሲጥ - ዋጥ አድርጎ እንደሚበላው "ኦክቶፐስ" አሳ ዝርያ። አዎ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደ "ኦክቶፐስ" አሳ አይነት ነው፤ስጋውን የሚያጭድ ጨካኝ። እነዚህ ብሔራዊ ሀዘን ጭነውብን ያለፉት ፖለቲከኞቻችን አሳዛኝ ፍፃሜ፤ የተራራቀ የርዕዮተ ዓለም ልዩነት ሳይኖራቸው ተልካሻ በሚባል የአካሄድ ልዩነት እርስበርሳቸው ተጠላልፈው የወደቁትን "የዛን ትውልድ" ጎረምሳ ፖለቲከኞቻችንን ነገረ - ምግባር እንድናስታውስ አስገድዶናል። ራቅ ሲል የሁለቱ ወንድማማች ፖለቲከኞች (የንዋይ ልጆች)፤ ቀረብ ሲል የነዋለልኝ እና ጥላሁን ግዛው የግብር (የአላማ) ልጆች የሆኑት የ66ቱ ዘመን ወጣት አብዮተኞች የመጨረሻ ጉዟቸው በእንዲህ ያለ የፖለቲካ "ትራጄዲ" የተጠናቀቀ ነውና።

**. . .የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዲህ ነው፤ ራሱን በራሱ ቅርጥፍ አድርጎ የሚበላ "ኦክቶፐስ" አሳ አይነት ነገር ነው፤ ቀን በጎደለበት ጀንበር የራሱን ስጋ (ዘር) ሲጥ - ዋጥ አድርጎ እንደሚበላው "ኦክቶፐስ" አሳ ዝርያ፤ አዎ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደ "ኦክቶፐስ" አሳ አይነት ነው፤ስጋውን የሚያጭድ ጨካኝ. . .**

የእውነት ግራ ግብት ጭንቅ ነው ያለን፤" ከፈርዖን" ብርቱ ክንድ ያላቀቀናል ያልነው ፈርኦኖችን አይነት እየሆነብን፤ ሀገር ይሰራል ያልነው ከሚያፈርሱት ጋር እያበረብን፤ ከመንፈስና ከአካል "ግዞተኝነት" ነፃ ያወጣናል ስንል ዞሮ እሱው አሳሪ - ገፊ እየሆነብን የእውነት የምንሆነው ቸግሮናል፤ ሞራል ያነገበ፤ ህዝቤ ይቅደም ያለ፤ ብሄርተኝነትን የናቀ..... በቃ! ድፍርስርሱን የሚያጠራ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ መሪ መጣ፣ ተገኘ ስንል ወዲያው የተስፋ ጉልላታችን የሚናድብን፤ በአይናችን ያየነው ተስፋ ብልጭ ብሎ ወዲያው እልም የሚልብን ግፋአን ህዝቦች ሆነን ቀረን። ወዲያው አግኝተን ወዲያው የምናጣ፤ ወዲያው አምነን ወዲያው የምንካድ- የግፍ ቀንበር የሚጫንብን ህዝቦች።

የወቅቱ የአገሬ ተክለ-ቁመና ደራሲ ገስጥ ተጫኔ "ነበር" በሚል ድንቅ መፅሀፉ ላይ ያነበብኩትን አጭር ሀረግ አስታውሶኛል። "ጊዚያዊ" ብሎ በዛው መንግስቱን ባፀናው ወታደራዊው ዘመን፣ እምዬ ኢትዮጵያ እጅግ ከባድ መከራ ውስጥ ተጥላ ነበረ።

በተለይ 1970ዎቹ መባቻ ገደማ። ያ ወቅት ወዲህ የጀነራል ዚያድ ባሬ መንግስት ወረራ፤ በዚህ በሻዕብያ "አለሁ" ባይነት ጡንቻቸውን አፈርጥመው የተነሱት የትግራይ አብዮተኞች አመፅ፤ ከዚህ ከመኃል ደግሞ የኢህአፓ "የውስጥ ግብግብ" ብቻ ኢትዮጵያ ድብልቅልቅ ወስጥ ነበረች። እናም ደራሲ ገስጥ ተጫኔ ያን የአገር ሰቆቃ ፤ያን የትራጄዲ ሰዓት እንዲህ በምትል ሀረግ የገለፀበት መንገድ ከአሁኗ መከረኛዋ ኢትዮጵያ ጋር ይመሳሰልብኛል...

"አጣብቂኝ ውስጥ ገብታ ነበር አገሪቱ፤ በአጭሩ አንድ ሰው ሁለት የተለያየ ቦታ ላይ የወደቀ ሬሳን ከአሞራ ለማስጣል ከወዲያ ወዲህ አንደሚል አይነት ሰው ነበር" ሲል ነው "የኮሚኒስት" መንጌን ዘመን ኢትዮጵያ የገለፃት። የትራጄዲው ደረጃ እና አይነት ይለያይ እንጂ ዛሬም ያችን መሳይዋ ኢትዮጵያ ላይ የደረሰን ይመስለኛል ።

የሚነፍሰው የፖለቲካ ንፋስ ደስ አይልም፤ የአገሪቱን የፖለቲካ መሪ ከሚያሽከረክሩት ልሂቃኑ መንደር የሚወራው-የሚያሰሙን ነገር እንቅልፍ አያስወስድም።

በተለይ በተለይ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በአገሪቱ socio poltics ሁኔታ ላይ እንደ መስከረም ምንጭ ጥርት ያለ አቋም አለመታየቱ ፣ ይኸው ግራ መጋባት ላይ ጥሎናል።

**ማጠቃለያ፡-** መቸም ከፖለቲካው አገር ትበልጣለች። ከብሔር ጥቅም በላይ ማዕከላዊ ሀሳብ የሆነው "ኢትዮጵያዊነት" ይቀድማል-ይልቃል። "የማንነት" ጥያቄ የሚመለሰው ከአገር ቀጥሎ ነው፤አገርን ጥሎ ማንነትን ማድመቅ፣አገርን አሳንሶ "መንደርተኛነትን" ማግዘፍ ኢ-አመክኖአዊ ብቻ ሳይሆን ከታላቁ የተፈጥሮ ሕግ ጋር መጋጨትም ነው (ልክ ፀሀይን በምዕራብ እናስወጣታለን እንደማለት)።

ስለዚህ አገር እየመራ ያለው መንግስት፤ የዚህ በሽተኛ አስተሳሰብ ፤ የዚህን ርጉም ህልም ነብያትን የዚህ መዓት አውርድ ፖለቲኮች፣ የጎሳ ዛር የሰፈረባቸውን የብሄር ልሂቃን በጊዜ ማረቅ ለዚህ አገራዊ ህመም ጥሩ ወጌሻ ነው። ካልሆነ እንደአያያዛችን መጨረሻ የት ሊያደርሰን እንደሚችል ምልክቱ እየታየብን ነው።

"ብረትን የምትቀርፀው እንደ ጋለ ነው" በጊዜው ያልተስተካከ-_ለ ነገር፣ በጠዋቱ ያልታከመ ሕመም ሲያድር ልክፍቱ አገር ያደርስና አገር በጥኑ ትታመማለች፤ አገር ትወድቃለች። ስለዚህ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባለቤቶች፤ ሰሪና አፍራሽዋ ከሆኑት ልሂቃን ነን ባዮች ላይ ስራው ይሰራል። አልያ ግን የማንነት ፖለቲካ የኢትዮጵያ ፍፃሜ ይሆናል። እንደ ቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያኑ፡-

"የለህም እንዳንል፣ ይነጋል ይመሻል
አለህም እንዳንል፣ እንዲህ ይደረጋል።" የሚለውን የሰቆቃ ዘመን ዜማ አንጎራጓሪዎች ሆነን መቅረታችን ነው። ከዚሁ ሁሉ መዓት ያውጣን።

**ኢትዮጵያችን ለዘላለም ኑሪ!**

## አንደበት



“ያነሳኸው ነገር እውነት ነው፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት 650 ሔክታር መሬት በተደራጁ ኃይሎች ተዘርፏል፤ ከአንድ ሺኅ በላይ ቤቶች በሕገ ወጥ መንገድ ተገንብተዋል፤ ሃረማያ ዩንቨርስቲ ፍራፍሬ የሚያመርትበት ሴራት ፓርኪንግ ተዘርፏል፤ ቤተክርስቲያንና መስጊዶች ተደፍረዋል፡፡ የሚሰግድበትን መስጊድ ደፍሮ ቤት የሰራ አለ፤ በርካታ የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች ተቀምተዋል፤ ገንዘብ ቆጥበው ኮንዶሚኒየም ቤት የሰሩ መምህራንና ሠራተኞች ለአንድ ዓመት ተኩል ከቤታቸው እንዲፈናቀሉ ተደርገው፣ በቤቱ ሌሎች ሰዎች ይኖሩበት ነበር፡፡ ችግሩ ይሄ ብቻ አልነበረም፣ ሕገ ወጥ ቤቶች እየተሰሩ በዩኔስ የተመዘገቡት ቅርሶችም አደጋ ላይ እየወደቁ ነው፡፡ ጀጎል ውስጥ ፓርኩ አከባቢ ሕገ ወጥ ግንባታዎች በመስፋፋታቸው ለፓርኩ አደጋ ሆኗል፡፡”

**አብዱላኪም ዮኒስ /የሐረሪ ክልል የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ /አዲስ ማለዳ ሰኔ 29 ቀን 2011 ዓ.ም**



“እንደሌላው ሀገር ቢሆን የጣና ችግር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚታወጅበት ይሆን ነበር፡ ፡ ብዙ ጊዜ ሐይቆች በከፍተኛ መጠን ሲጎዱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይታወጃል፡፡ በዚያ ሐይቅ ዙሪያ ለአስር ዓመት አካባቢ ምንም ዓይነት ነገር እንዳትጠቀምበትና ሐይቁ እንዲያገግም ይደረጋል፡፡ አንዳንዴ ተራራዎችንም እንደዚያ ይደረጋል፡፡ ግን አሁን ጣና እንደምታውቀው የዓሳ ምርቱ እየቀነሰ ነው፣ እንቦጩ ዳርዳሩን ስለሸፈነው ገበሬው ውሃ ማግኘት አልቻለም፤ /እምቦጩ ውሃውን የመበከልና ሽታ እንዲኖረው የማድረግ ባህሪ አለው/፤ ገበሬው የሚጠጣ ውሃ እንኳን ማግኘት አልቻለም፡፡”

**ዶ/ር ሰለሞን ክብረት በኩር ጋዜጣ ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም**



“ኢህአፓ ሲጀመር ለእኔ ብሎ የተነሳ ድርጅት ባለመሆኑ የእኔነት በሽታ ኢህአፓን በጣም ያሳስበዋል፡፡ የእኔነት በሽታ ሙስናን፣ የዘመድ፣ የጓደኛና የቤተሰብ ትስስርን ያመጣል፡፡ በለውጡ ውስጥ እነዚህ ነገሮችን ታያቸዋለህ፡፡ ለውጡን የምታየው ወደ ላይ ቀና ስትል ብቻ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ዙሪያ ባሉ አከባቢዎች ነው፡፡ ወደታች ወረድ ስትል 27 ዓመት የነበረው መዋቅርና ሰዎች እንዳሉ ናቸው፡፡ ሥርዓቱ አልተለወጠም፡፡ ይህ ያሳስበናል፡፡”

**ወ/ሮ ቆንጂት ብርሃን /የኢህአፓ ከፍተኛ አመራርና የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል/ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም**



“እግር ኳስን ጨምሮ አጠቃላይ ስፖርት ከዘረኝነት ነፃ የሆነ መድረክ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የሚሰራው እንዲህ እንዲሆን ነው በኛ ሀገር ግን አሁን ላይ ያለው ሁኔታ ያስጠላል ዘረኝነቱ ኳሱ የሠላም መስበኪያ መድረክ የሆነው እግር ኳሳችን ላይ ዘረኝነት መንፀባረቁ አሳፋሪ ነው….. ክለብ ሲደገፍም ፖለቲካና ብሔርተኝነት ይንፀባረቅበታል ከዚህ በኋላም ካልተስተካከለ አደጋ አለው ደጋፊውም የኳሱ ባለድርሻም ከዘረኝነት ነፃ ሆኖ ነው መመልከት ያለበት፡፡”

**አቶ ሙጂብ ቃሲም /የፋሲል ከነማ ተጫዋች/ ሀትሪክ ጋዜጣ ሐምሌ 3 ቀን 2011 ዓ.ም**

## ግጥም

### አግዜር እንዳይከፋው

ደስ ያለው ሊያሞግስ ……………… የከፋውም ሊከስ
በዳይ እንዲቀጣ ……………………… ተበዳይ ሳያለቅስ
ተቀጭ እንዲፀፀት …………………… አሳሪ እንዲፈታ
መስማማት ነበረ
እኔ የሚሉት ሰው …………….ቤቱ የታሰረ
ሲፅፍ እንዲገረፍ ……………….. ሸንጎ እየመከረ
አለዚያ እንዲታሰር …………….. ደግሞ ከዘመረ
ሲቀኝ እንዲሰቀል ………………. ቅኔው ከሰመረ
በብር እንዲቀጣ …………….ሀቅ ከተናገረ
ይህኛው ህግ ደርሶት …………እኔ ተቸገረ
ይግባኝ አይል ነገር ………………ለዚህ ይግባኝ የለው
ሳምላኩ ይጮሃል ………………. እንዳው በጨለማው
በደሉን እያየ ………………….. አግዜር እንዳይከፋው፡፡

***ደም የተፋ ብዕር በደሳለኝ ስዩም***

## አስገራሚ ነገሮች

😐 እንስሳት ህመም ሲያሰቃያቸው የሚታዘዝላቸው መድኃኒት ዲክሎፌናክ ይባላል፡፡ የዲክሎፌናክ መርፌን የተወጋ እንስሳሳ የሚበሉት አሞራዎች ግን በዚህ መድኃኒት ተመርዘው ይሞታሉ፡፡

😐 አንድ ቶን ወረቀትን ሪሳይክል አድርጎ እንደገና በጥቅም ላይ ማዋል አስራ ሰባት ሺኅ ዛፎችን እንደ መታደግ ይቆጠራል፡፡

😐 ፒትሮ አሬኖቲ የተባለ የመካከለኛው ዘመን ጣልያናዊ ደራሲ የሞተው ከመጠን በላይ ሲስቅ ትን ብሎት ነው፡፡

## አባባል

- አይሆንም ወይም አይደለም ለማለት ድፍረት ይኑርህ፤ ሁልጊዜም እውነታውን ለመጋፈጥ ወኔው ይኑርህ፤ ትክክል ስለሆነ ብቻ ትክከለኛውን ነገር አደርግ፡፡ እነዚህ ህይወትህን በመልካም ስነምግባር ለመኖር ቁልፍ ነገሮች ናቸው፡፡
- አንዳንድ ጊዜ መቀየር የማንችላቸው ነገሮች በምትኩ እኛኑ ቀይረውን ቁጭ ይላሉ፡፡
- ይቅርታ ማድረግ ከበደለን ነገር ይልቅ ለበደለን ሰው ትልቅ ቦታ እንዳለን የምናሳይበት መንገድ ነው፡፡
- ጓደኛ ማለት ስናወራ ከልቡ የሚያዳምጠን፣ ስናዝንና ስንከፋ የሚረዳን እንዲሁም በመንገዳችን የሚመራን ነው፡፡
- ስትዋሽ ደካማነትህን እየተናገርክ ነው፡፡ ምክንያቱም እውነታውን ለመጋፈጥ አቅም እንደሌለህ እየገለፅክ ስለሆነ፡፡
- እውነተኛ ጓደኛሞች አንዳቸው ለሌላኛቸው “እውነተኛ ጓደኛዬ ነህ!” አይባባሉም፤ እንዲሁ ያውቁታል፡፡
- ወቀሳ ከፈራህ ምንም ነገር አትናገር፣ ምንም አትስራ….. በአጭሩ ምንም አትሁን፡፡

## የኢትዮጵያ ፋና ወጊ ባለሙያዎች

- የመጀመሪያው ሐኪም ዶ/ር ወርቅነህ እሸቴ
- የመጀመሪያው የንግድ ጄት አብራሪ ካፒቴን አለማየሁ አበበ
- የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሬድዮ ዜና አንባቢ ክቡር ዶ/ር ከበደ ሚካኤል
- የመጀመሪያው ዘመናዊ ፀሐፊ ተውኔት ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ
- የመጀመሪያ ሳይንሳዊ መፅሐፍ ደራሲ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ

# “በአፍሪካ ደረጃ በጥራትና በፍጥነት አገልግሎት መስጠት ተቀዳሚ ግባችን ነው”

*ሳምራዊት ሽፈራው*

**በዛየን ኢንቴርየር ዲዛይን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የኢንተርየር የዲዛይንና የፊኒሺንግ ሥራ ያጣመራቸውን ሁለት የሙያ ባለቤቶች፣ በ7ኛው የሆቴል ሾው አፍሪካ ኤግዚብሽን ላይ፣ ኢንቴርየር ዲዛይን ኃላ የተ የግል ማህበር (ካምፓኒ) ሼር ሆልደርና የፊኒሺንግ ዲፓርትመንት ማናጀር ከሆኑት አቶ ቸርነት ተካና፣ የካምፓኒው ሼር ሆልደርና ዋና ስራ አስኪያጅ የዲዛይን ዘርፍን በማኔጅመንት እየመራች ላለችው ሳምራዊት ሽፈራው ጋር የግዮን ጋዜጠኛ ሙሉጌታ አክሊሉ ጋር ያደረጉትን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡**

**ግዮን፡- “ዛየን ኢንቴርየር ዲዛይን” የሚለውን መጠሪያ እንዴት ልትመርጡ አሰባችሁ?**

ሳምራዊት፡- “ዛየን” ቀጥተኛ ትርጓሜው ጽዮን ሲሆን፣ አክሱም ጽዮን ወደሚለው ኢትዮጵያዊ አጠራር የመሄጃ መንገድ ጥርጊያ እንዲሆነን ስለምንፈልግ ነው መጠሪያውን የሰጠነው፡፡

ኢንቴርየር ዲዛይን ሀሳቡ ለኢትዮጵያኖች አዲስ ቢመስልም በሂደት እየተለመደ የመጣ ነው፡፡ በአጭሩ ኢንቴርየር ዲዛይን ስንል አንድን የተሰጠንን ቦታ (ስፔስ)፣ ቤት፣ ቢሮ፣ ሆቴል…. ወዘተ ባለው “ላይት ኢፌክት፣ ፈርኒቸር፣ ቀለም…”.. የመሳሰሉትን ተጠቅመን አነስተኛ፣ ተመጣጣኝና ተገቢ በሆነ ዋጋ ማስዋብ ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- ዛየን ኢንቴርየር ዲዛይን ከተመሰረተ ምን ያህል ጊዜ ሆነው?**

ሳምራዊት፡- ሦስት ዓመት ሆኖናል፡፡ አድራሻችን አዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወርቁ ህንፃ አከባቢ፣

ከሆሊውድ ሆቴል ፊትለፊት ኮ/ል ደስታ የገበያ ማዕከል 3ኛ ፎቅ ላይ ነው የምንገኘው፡፡

ድርጅቱን ስንመሰርተው በኢንቴርየር ዲዛይኑና በፊኒሺንጉ ዘርፍ ነው የመሰረትነው፡፡ የሚሰጠው አገልግሎትም እንደ ዲፓርትመንት ሲሆን፣ የኢንቴርየር ዲፓርትመንትንና የፊኒሺንግ ጠቅላላ የሥራ ዘርፍ ላይ አቀናጅተን ይዘን ነው እየሰራን የገፋንበት፡፧

**ግዮን፡- የዛየን ኢንቴርየር ዲዛይንና የፊኒሽንግ ስራ የሀሳቡ አመንጪ ማነው? ምን ያህል ሰራተኞችስ በስሩ አቅፏል?**

ሳምራዊት፡- በ50 ሺ ብር ካፒታል ነበር አነሳሳችን፡፡ የሀሳቡ አመንጪነት የእኔና የቸርነት ተካ የጋራ ሀሳብ ነው፡፡ እርሱ በፊኒሺንጉ ዘርፍ እኔ በኢንቴርየር ዲዛይኑ ዘርፍ፡፡ አንድ ላይ ተቀናጅተን ለመሥራት ነው የጀመረነው፡፡

በተለያዩ አጋጣሚዎች ከእዚህ ሥራ ጋር ሁለታችንም በሙያችን ቅርበት ነበረን፡፡ አገራችን ላይ በዘርፉ ብዙ ክፍተቶች አሉ፡፡ ብዙ ሰው ሙሉውን ህንፃ ይሰራና ቀለም ቀብቶ ጨርሶ “ውይ ይህንን ቀለም አልወደድኩትም” ይልና ሌላ ቀለም ይቀባል፡፡ አንዳንዴም ትላልቅ ወጪዎች ወጥቶባቸው ሥራዎች ይሰራሉ፧ የመጨረሻ ውጤታቸው ሲታይ ግን እንከኖች አይጠፉም፡፡ እነዚህ ነገሮች ናቸው ይህንን



ሳምራዊት ሽፈራው

ካምፓኒ ለመመሥረት መነሻ የሆኑን፡፡ ሀገራችን ላይ ያለውን ክፍተት እኛ በምንችለው አቅም መዝጋት እንችላለን ብለን ነው ካምፓኒውን ፎርም ያደረግነው፡፡ በኢንቴርየር ዲዛይኑ ዘርፉ በሙያው የተሰማ ከ60 እስከ 70 የሚደርሱ ሰራተኞችና ከ6 በላይ አርክቴክቶች በእዚህ ካምፓኒ ስር ይተዳደራሉ፡፡

**ግዮን፡- የኢንቴርየር ዲዛይንና የፊኒሺንግ ሥራ ልዩነታቸውን እንዴት ትገልፁታላችሁ?**

ሳምራዊት፡- ኢንቴርየር ዲዛይን ሲባል ሥራው በአብዛኛው የሚያልቀው “ሶፍትዌር” (ስሪዲዎችና ዲቴል ድሮዊንግ) ላይ ነው፡፡ እያንዳንዱ የመብራት ሲስተም፣ የፈርኒቸር አቀማመጥ፣ የመጋረጃው አይነት የምንጣፉ አይነትና እያንዳንዱ ነገር በጥንቃቄ ተሰርቶ በሶፍትዌር (በሲዲ) መልክ ነው የሚጠናቀቀው፡፡

የፊኒሺንግ ሥራ ሲባል በአካል እዚያው በቦታው ላይ የእኛም ባለሙያዎች ሆኑ ሌላ ሰው (የደንበኛው) ባለሙያዎች በቦታው ላይ ተገኝተው በቀጥታ የሚሰሩት ሥራ ነው፡፡

የፊኒሺንግ ሥራዎቻችን ላይ የቀለም፣ የጂብሰም፣ የግርግዳ፣ የአልሙኒየም፣ መሬት ላይ የሚነጠፉ ሴራሚኮችና ሌሎችንም የፊኒሺንግ ሥራዎች ያካትታል፡፡ የኢንቴርየር ዲዛይን ሥራ ደግሞ ለሆቴሎች፣ ለባርና ሬስቶራንት ለሱፐር ማርኬቶች፣ ለመኖሪያ ቤቶች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ቦታዎችና ድርጅቶች ቀጥታም ሆነ ሙሉውን ፕሮፌሽናል በሆነ ደረጃ፣ እንዲሁም ዘመኑ በሚፈቅደው የፈርኒቸር ዓይነት ሙሉ ለሙሉ የኢንቴርየር ዲዛይኑ ሥራ ይሰራል፡፡

ኢንቴርየር ዲዛይኑ በሙያው ዙሪያ ለተሰማሩ አርክቴክቶች፣ የኤሌክትሪካልና ለሳኒተሪ መሀንዲሶች የቀረበ በመሆኑ በፕሮፌሽናል (ደረጃውን በጠበቀ) መልኩ እንሰራለን፡፡ ፊኒሽንጉም ላይ ራሳቸውን የጠበቁ ባለሙያዎች ስላሉን ውጤታማነታችንን እያሳየን ነው፡፡

**ግዮን፡- ሙያውን እንዴት አገኛችሁት?**

ሳምራዊት፡- ሙያው ደስ ይላል፡፡ በተለይ እያንዳንዱን ነገር በአካል ሰርተህ ሥትጨርስና ደንበኛው አይቶት እርካታውን ሲገልፅልህ የሰውን ፍላጎት ያማከለ ዲዛይን በመሆኑ ደስታን ይሰጣል፡፡ እያንዳንዱን ፍላጎት ማሳያ የሚሆነን በኢትዮጵያ ብቻ ከ80 ብሔረሰብ በላይ ቢኖሩና የእነርሱ የቤት አሰራር የሚለያይ ባህሪ ቢኖረው፣ ስራው እየተዝናናህበት አዲስ ፈጠራ እያከልክ የምትሰራው በመሆኑ እርካታውም ሰፊ ነው፡፡

**ግዮን፡- ከበጎ አድራጎት አንፃር ምን ለማድረግ አስባችኋል?**

ሳምራዊ፡- ዛየን ኢንቴርየር ዲዛይን ከሙዳይ የበጎ አድራጎት ማህበር ጋር በሙያችን ልናግዛቸው የሚገባውንና አቅማችን የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገብተንላቸው፣ ያገኙትን መሬት ተረክበው የመሰረት ድንጋይ ከተጣለ በኋላ ቀደም ሲል አብሯቸው ለመሥራት ቃል ከገባላቸው ድርጅት ጋር ለማገዝ ከጎናቸው መሆናችንን ነግረን ተሥማምተናል፡፡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በቋሚነት ለማሳደግ ቃል ገብተን በመተግበር ላይ ነን፡፡

**ግዮን፡- ሙያውን ያገኛችሁት በልምድ ነው? ወይንስ በትምህርት?**

ሳምራዊት፡- ሙያው በተለየ መልክ ይፈለጋል፣ እኔ በሙያዬ አርክቴክት ነኝ፡፡ አርክቴክቸራል ትምህርቱም ይጠቅማል፡፡ በኢንቴርየር ዲዛይን ዘርፉ እንግሊዝ አገር ከሚገኝ ት/ቤት ጋር የርቀት ትምህርት እየወሰድኩኝ ነው፡፡ የተሟላ አርክቴክቸራል ዲዛይን ስላለን ከፊኒሺንጉ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት አቀባበል አለ፡፡

**ግዮን፡- ቀጣይ የሥራ ግቦቻችሁ ምን ይመስላሉ?**

ሳምራዊት፡- ዛየን ኢንቴርየር ዲዛይን ኃ/የተ/የግ/ማህበራችንን ወደ ትልቅ ደረጃ ማድረስ እንፈልጋለን፡፡ በተለይም ወደ ማሰልጠኛ ተቋም ከፍ ማድረግና ከትንንሽ ዕቃዎች ጀምሮ፣ ትላልቅ ፈርኒቸሮችና ሙያው ሊጠይቀው የሚችል መገልገያዎችን አሟልተን ደረጃውን ከፍ አድርጎ በአፍሪካ ደረጃ በጥራትና በፍጥነት አገልግሎት መስጠት ተቀዳሚ ግባችን ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ከ3 ዓመት በኋላ በጥንካሬ ተጉዘን እንደምናሳካ ተሥፋ አለኝ፡፡

ዘርፉ ሰፊ ነው፡፡ አሁን ላይ የእንጨት ሥራ ሾው ሩም አለን፡፡ ግን ይሄ በቂ ነው ብለን አናስብም፧ ወደፊት ሰፋፊ የሆኑ ወርክሾፖችን የመክፈት ፕላኑ አለን፡፡

**ግዮን፡- ማስተላለፍ የምትፈልጊው ነገር አለ?**

ሳምራዊት፡- በቅድሚያ ድንግል ማርያም ምስጋና ለእርሷ ይሁን፡፡ 2ኛ በአጋርነት በብዙ ነገር ከጎናችን ሆነው የደገፉን ድርጅቶችና ግለሰቦች፧ ሙሉ ኃላፊነት ጥለውልን ሥራውን አጠናቀን ለሰጠናቸውና ወደፊትም አብረውን ለሚሰሩና ለመሥራትም ለሚመጡት በጥሩ ደስታ ልንቀባለቸው ዝግጁ ነን፡፡

# “ከኢንተርኔት አምጥተን የምንሰጣቸው የሚመስላቸው ሰዎች አሉ”

አቶ ቸርነት ተካ

**ግዮን፡- የሥራ አቀባበላችሁ ምን ይመሥላል?**

ቸርነት፡- እኛ ጋር የሚመጣ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት “ዲዛይን ብቻ ነው ማሰራት የምፈልገው” የሚል ከሆነ ዲዛይኑን ብቻ እንሰራለታለን፡፡ “ዲዛይኑና ፊኒሺንጉን በጥምረት ይሰራልን” የሚሉ ከሆነ ጥያቄያቸውን በሰራነው ዲዛይን መሰራት ፊኒሺንግ ሥራውንም ሰርተን ሙሉውን አጠናቀን እናስረክባለን፡፡ ወይንም ሌላ ቦታ ዲዛይኑን አሰርተው መጥተው ከሆነ ባሰሩት ዲዛይን መሰረት የፊኒሺንግ ሥራዎቹን እንሰራላቸዋለን፡፡

**ግዮን፡- በሙያው የት የት ሰርታችኋል? ለአብነት ጥቂቱን ብትጠቅሱልኝ?**

ቸርነት፡- እኛ ኢንቴርየር ዲዛይንና የፊኒሺንግ ካምፓኒ ነው ብለን ስንመሰርት ለግለሰብም ሆነ ለድርጅቶች አገለግሎት እንሰጣለን ብለን ነው፡፡ በሦስት ዓመታት ውስጥ በጣም ብዙ ለሚባሉ ካምፓኒዎች፣ ግለሰቦች ይህንን አገልግሎት ሰጥተናል፡፡ በዋነኛነት መጥቀስ ካስፈለገ ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ዋናው መ/ቤት የእንግዳ መቀበያቸውን ከነዲዛይኑ ፊኒሺንጉንም ጨምሮ የሰራንላቸው እኛ ነን፡፡ የአዋሽ ባንክን አዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭም የተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች እየተዟዟርን ከ15 በላይ ቅርንጫፎቻቸውን ሰርተንላቸዋል፡፡ ከእዚያ ውጭ ኤዶሚያስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ ማህበርን ሂውማን ሪሶርስ ላይ የሚሰራ ካምፓኒን ሙሉውን የዋና መ/ቤታቸውን ቢሮ ኢንቴርየር ዲዛይኑንና ፊኒሽንጉን የሰራንላቸው እኛ ነን፡፡ ማክፋ ሎጀስቲክስ ትልቅ ካምፓኒን ሙሉ ኢንቴርየር ዲዛይንና በተጨማሪም የእንግዳ መቀበያ አካባቢውን ከነ ፊኒሽንጉ ሰርተን አስረክበናቸዋል፡፡

**ግዮን፡- በዘርፉ ምን ምን ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጋችሁ እየሰራችሁ ነው?**

ቸርነት፡- እዚህ እኛ ካምፓኒ ውስጥ እየሠሩ የሚገኙ ፕሮፌሽናሎች አርክቴክቶች ሲቪል መሀንዲሶች፣ ኤልክትሪካልና ሳኒቴሪ መሀንዲሶች አሉ፡፡ በፊኒሺኒንግ ዘርፍ ላይ ከሴራሚክ (የመሬት ወለል ንጣፍ) ባለሙያዎች ጀምሮ የቀለም ቅብ ባለሙያ፣ የጂብሰን ባለሙያ የአልሙኒየምና የእንጨት ባለሙያዎችን አካትቶ የያዘ ድርጅት ነው፡፡

**ግዮን፡- ሙያውን እንዴት አገኘኸው?**

ቸርነት፡- አንዳንድ ጊዜ ሙያው አንድ ወላጅ ልጅ ወልዶ፣ አድጎና ተምሮ ለቁምነገር ሲበቃ ያለው እርካታ ዓይነት ስሜት ነው የተሰማኝ፡፡ አንድ ባዶ መሬት ላይ ዲዛይን አድርገህ፣ በዚያ ዲዛይን መሰረት እያንዳንዱን ነገር ሰርተህ፣ ህይወት ስትዘራበት የሚሰጠው እርካታ ነው የሚሰማህ፡፡



አቶ ቸርነት ተካ

**ግዮን፡- ከቀደሙ የሥራ ተሞክሮዎቻችሁ ምን አይነት ጥቅም አገኛችሁ?**

ቸርነት፡- ሥራው ት/ቤትም ጭምር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁልጊዜ ዲዛይን ነው የምትሰራው፡፤ ከመጀመሪያው ሥራ ሁለተኛውንና ሦስተኛው ሥራ የበለጠ የተሻለ ፊኒሺንግና ዲዛይን ነው፡፡ ልምድም እያገኘህ ስለምትሄድ ሙያው በራሱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም (ዩኒቨርስቲ) ነው፡፡

**ግዮን፡- ማህበረሰቡ በኢትዮጵያ ለኢንቴርየር ዲዛይንና ለፊኒሺንግ ያለው ግምት ምን ያህል ነው?**

ቸርነት፡- በፊት ስለሙያ ግንዛቤው ስለሌለው አነስተኛ ነበር፡፡ ከ3 ዓመት ጀምሮ ግን ሰው የተሻለ የአመለካከት ለውጥ በዘርፉ እያመጣ ነው፡፡ አሁን ላይ የኮንዶሚኒየም ቤት ኖሮት ዲዛይን ለማሰራት ወደእኛ ካምፓኒ የሚመጣ ሰው አለ፡፡

ከዚያ ውጭ ከኢንተርኔት አምጥተን የምንሰጣቸው የሚመስላቸው ሰዎች አሉ፡፡ ግን የእኛ ካምፓኒ የሚሰራው፣ ከአንድ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ጋር ተስማምተን ሥራ ስንጀምር መጀመሪያ የእነርሱ “ሳይት” ላይ ሄደን ሥምምነቶችን ወስደን፣ በእነርሱ መሥፈርት መሰረት ፍላጎታቸውን ጠይቀን ነው ዲዛይኖቹን የምንሰራው፡፡ ቢቀነስ፣ ቢጨመርና ቢስተካከል የሚሉትን ሀሳብ በደስታ እንቀባላለን፡፡

አንዳንዴ በጣም የወረደ አመለካከት በትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ አለ ለምሳሌ፡- ሆቴል ፕሮጀክቶችና ትላልቅ የአፓርትመንት ፕሮጀክ ቶችን በተመለከተ ለእኛ አገር ባለሙያ የሚሰጠው ግምትና ለውጭ አገር ባለሙያዎች የሚሰጠው ግምት የተለያየ ነው፡፡ የእኛ አገር ባለሀብቶች የሀገራቸውን ባለሙያ ካላበረታቱ ማደግ የሚባለው ሂደት እየቀጨጨ ይሄዳል፡፡

**ግዮን፡- ዲዛይንና የፊኒሺንግ ሥራ ልዩ ባህሪ ውስጥ ጥቂቱን ብትነግረን?**

ቸርነት፡- የዲዛይን ሥራ “ዲዛይን ነው”፣ ቤት ወይንም መሬት ላይ ያለ ቦታን ለምትፈልገው ዓላማ ምቹ መሆን መንገድ፣ ባለህ አቅም እንዴት መጠቀም ትችላለህ? የሚለውን ግራፊካሊ ዲዛይን አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ በተቀመጠው ዲዛይን መሰረት እያንዳንዱን ነገር ፈርኒሽ አድርገህ፣ የሚቀባው ተቀብቶ፣ የሚነጠፈው ተነጥፎ ሥታስቀምጥ “ፊኒሺንግ” ይሰኛል፡፡

**ግዮን፡- በትላልቅ ኤክስፖዎች ላይ ሥራዎቻችሁን አቅርባችሁ ታውቃላችሁ?**

ቸርነት፡- አዎን! በሆቴል ሸው አፍሪካ ዝግጅቶች ላይ ለ3 ተከታታይ ዓመታት በሚሊኒየም አዳራሽ ተሳትፈናል፡፡ አብዛኛው ወደ ኤግዚብሽኑ የሚመጣ ጎብኚ፣ ሆቴል፣ አፓርትመንት ትላልቅ ቢሮዎችን የሚሰሩ ባለሀብቶችና ግለሰቦች የሚመጡበት ስለሆነ 1ኛ የገበያ ትስስር እንፈጥርበታለን፡፡ 2ኛ እንደኛ በኤክስፖው ተሳታፊ ከሆኑ ካምፓኒዎች ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሥራችን የሚያገናኝን ሥለሆነ ጥሩ የሆነ የእርስ በርስ የሥራ ትስስር እንፈጥርበታለን፡፡

**ግዮን፡- በሙያችሁ ያገኛችሁት ዕውቅናና ማበረታቻ አለ?**

ቸርነት፡- አዋሽ ባንክ ብዙ ስራዎችን ሰርተንላቸው ከእነርሱ ያገኘነው የእውቅና ሰርተክፌት አለ፡፡ ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ ከኤዶምያስ ኢንተርናሽናል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር፣ ከዲጂታል ታይም፣ ከስቲቫ ጃራ ትሬዲንግ የእውቅና ማበረታቻ አግኝተናል፡፡

**ግዮን፡- ሮል ሞደሌ ነው የምትለው አለ?**

ቸርነት፡- “እከሌ” በማለት የምገልፀው ባይኖርም የውጭ ፕሮግም ላይ “ፒንክ ማይ ራይድ”› የሚል ፕሮግራም አለ፡፡ በዛ ሾው በጣም ያረጁ መኪኖችን ወስዶ በሚገርም ሁኔታ ሰውን “ሰርፕራይዝ” ሲያደርጉ አያለሁ፡፡ ከዚያም የተነሳ የምንኖርባትን ቤት፣ የምንሰራበትን መ/ቤትና ቦታ ለምንድን ነው ማስዋብ የማንችለው? በሚል እሳቤ መነሻዬ ሆኖኛል፡፡

**ግዮን፡- ማስተላለፍ የምትፈልጉት ነገር አለ?**

ቸርነት፡- የግዮን መጽሔት ዕድሉን ስለሰጠን እናመሰግናለን፡፡ ኃያሉና ገናናው አምላካችን እግዚአብሔር ከጎናችን በመሆኑ ክብር ምስጋና ይድረሰው፡፡ በቆየንባቸው 3 የሥራ ዓመታት ውስጥ የእኛን ሥራ ተማምነው በሙሉ ልብ ሥራ ለሰጡን አጋሮቻችንና ግለሰቦች፣ ድርጅቶች (ካምፓኒዎች) ከልብ ምሥጋናችንን እናቀርባለን፡፡ አብረውን ለሚሰሩ ሠራተኞችና ካምፓኒ በአጋርነታችን አብረን እንዝለቅ እንላለን፡፡

# መረባ ሌላኛዋ መፃኢ ኮከብ



የሶሎ ሙዚቃ አቀንቃኝ የሆነችው ኢትዮ-አሜሪካዊቷ ማርያን መረባ ጁላይ 9 2019 አዲስ የለቀቀችውን የሳንድስቶርም ሙዚቃ ቪድዮ ተከትሎ በቮጉ መፅሄት ሽፋን አግኝታለች፡ ፡ መረባ የሙዚቃ ፍቅሯ ከልጅነቷ የጀመረ ሲሆን ከትምህርቷ ጋር አብራ ስታስኬደው ቆይታለች፡፡ የመድረክ ስሟ መረባ ሲሆን 7 ነጠላ ዜማዎችን እ.ኤ.አ በፈረንጆች አቆጣጠር ከ 2014 ጀምሮ እስከ 2019 ሴፕቴምበር ድረስ ራዲዮ ፍላየር ፣ ቤት፣ ብላክ ትራክ፣ ፕላኔት ዩ፣ ሌት ብሉመር፣ ሳንድስቶርም የሚሉ ነጠላ ዜማዎችን ለቃለች፡፡ መረባ በሙዚቃ ህይወት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ የገባችበት ለመሆኑ ማሳያው ከዘፋኝነቱም ባሻገር የሙዚቃ ግጥም ፀሃፊ እና ፕሮዲውሰርም ነች፡፡

ተወልዳ ያደገችው በአሜሪካን ሃገር ፊላደልፊያ ከተማ ሲሆን የሙዚቃ ፍቅር ያደረባት ገና በ4 አመቷ ነበር፡፡ በመዝፈን የጀመረችውን የሙዚቃ ዝንባሌ ወደ ፒያኖ ከዛም ጊታር ወደ መጫወት አሳድጋዋለች፡ ፡ ቤተሰቦቿ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ሲሆን ወደ ተለያዩ አከባቢዎች በመዘዋወር ይሰሩ ነበር ፡፡ በመሆኑም መረባ የሃይ ስኩል ትምህርቷን በካሮላይናና ግሪንስቦሮ ትምህርት ቤት ተከታትላለች፡፡ በአባቷ ሃገር ኢትዮጵያም ወደ አንድ አመት የሚጠጋ ጊዜ ቆይታለች፡ ፡ የሃይ ስኩል ትምህርቷን እንዳጠናቀቀችም በቤተሰቦቿ ጉትጎታ በአስራ ሰባት አመቷ በፒትስበርግ የካርኒግ ሚሎን ዩኒቨርስቲ የተቀላቀለች ቢሆንም በኋላ ግን አትላንታ ጆርጂያ በሚገኘው ስፔልማን ኮሌጅ በመግባት በእንግሊዝኛ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያገኘች ሲሆን ሙዚቃንም በማይነር ወስዳለች፡፡ እ.ኤ.አ በ2000ዓ.ም ማለት በኮሌጅ ቆይታዋ ከደፍ ጃም ጋር በመዋዋል የሙዚቃ ግጥሞችን ትፅፍ ነበር፡፡

በኋላም ሩም ፎር ሊቪንግ፣ ሬዲዮ ፍላይር እና ስፒሌጅ ቪላጂ የተሰኙትን ሙዚቃዎች እ.ኤ.አ ከ2013 ጀምሮ የለቀቀቻቸው ሙዚቃዎች

## ግላዊ መረጃዎች

የመዝገብ ስም - ማርያን መረባ
የትውልድ ዘመን -1990 እ.ኤ.አ
የሙዚቃ ዘውግ - አር ኤንድ ቢ እና ሶሎ
የስራ መስክ - ሙዚቀኛ፣ የሙዚቃ ግጥም ፀሃፊ፣ ፕሮዲውሰር
ተጓዳኝ ተሰጥኦ - ፒያኖ እና ጊታር

## የሙዚቃ ስራዎቿ በከፊል

የተለቀቁበት ጊዜ- አታሚ
ዘ ጃንግል ኢዝ ዘ ዌይ አውት(አልበም)
ቬብሩዋሪ 27 ፣2019
በኢንተርስኮፕ ሪከርድስ
ኮተን ሃውስ፣ቅፅ 1 ፌብሩዋሪ 10፣2017
በጃም ሶሉውሽን/ሪሞት ኮንትሮል ሙዚቃ
ሩም ፎር ሊቪንግ (ነጠላ ዜማ ስብስብ)
ቬብሩዋሪ14፣2013 ግኋ

ሲሆኑ ሩም ፎር ሊቪንግ በሙሉ ስሟ የወጣ ስራዋ ነው፡፡ በመቀጠል ይለቀቃል ተብሎ የተለጠፈው የሬዲዮ ፍላይ ነጠላ ዜማዎች ስብስብ ስራዎቿ ባይለቀቁም በ2017 ግን ኮተን ሃውስ ቅፅ አንድ የነጠላ ዜማዎች ስብስብ ውስጥ ሴፕቴምበር እና ሬዲዮ ፍላየርን በጃም ሶሊዩሽን ስር ተካተው ተለቀዋል፡፡ መረባ ቢርስ ላይክ ዚስ ቱ በሚለው የአትላንታ ሂፕ ሆፕ ስብስብ ከሆነው ስፒሌጅ ቪሌጅ ጋር በመሆን ስራዋን በ2015 አካታ አውጥታለች፡ ፡ በተጨማሪም ከኧርዝ ጋንግ፣ ጁ.አይ.ዲ እና ሲክስ ላክ ጋር በመሆን በተለያዩ ስራዎች ላይ ተጣምራ ሰርታለች፡፡

በ2018ም ከኢንተር ስኮፕ ሪከርድስ ጋር ተፈራርማ ብላክ ትራክ እና ፕላኔት ዩ የተሰኙ ነጠላ ዜማዎችን የለቀቀች ሲሆን እነዚሁ ዜማዎችም በቀጣይ በመጀመሪያ አልበሟ ‹‹ ዘ ጀንግል ኢዝ ዘ ዌይ አውት›› ውስጥ በ2019 አካታ ለቃዋለች፡፡

መረባ ኢትዮጵያዊ ቅርሶቿ በሙዚቃዎቿ ውስጥ ዋነኛ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንደሆኑ ትናገራለች፡፡ የነጂይዚ፣ ማዶና፣ ማይክል ጃክሰን እና ዘ ኖቶሪየስ ቢ.አይ.ጂ የሙዚቃ ስራዎች አሻራም እንዳረፈባት እንዲሁ፡ ፡ ‹‹ ኮከቤ ቪርጎ ነው እኛ ደግሞ ታግሎ ማሸነፍን እንወዳለን፣ ግን ተመልሰን እዛው አዙሪት ውስጥ እንገባለን በብዙ አውሎ ነፋስ ውስጥ፣ ማናችንንም ደስተኛ በማያደርግ ስለዚህ ከአውሎ ነፋሱ አይን አምልጫለሁ›› ትላለች ይህን አልበም ለማውጣት የነበረባትን ውጣውረድ ስትናገር፡፡ ክረምቱን ቀጣይ ስራዎቿን በአውሮፓ ለማስተዋወቅ ከመውጣቷ በፊት አዳዲስ ስራዎች በስቱዲዮ በመቆየት እየሰራች የማሳለፍ እቅድ ያላት ሲሆን ይህም እውነተኛና ጥሬ የሙዚቃ ስራዎች ለመስራት ካላት ፍቅር የተነሳ እንደሆነ ይነገራል‹‹ ከዚህም በኋላ የምሰራቸው ሙዚቃዎች የሙዚቃን ተለዋዋጭ ጣዕም ብቻ ሳይሆን ሙዚቃን የመስራት ሂደቱን በራሱ እንዲወዱት የሚያበረታታ ስራ እንዲሆን እፈልጋለሁ›› በማለት ታስረዳለች፡ ፡ ‹‹ ሙዚቃዬ ሁሌም የጥሩ፣ የመጥፎ እና አስቀያሚ ጉዞዎች ማሳያ ይሆናል›› ትላለች፡፡

በመፅሄቱ መረባ ለስላሳ የሆነው ድምጿ የሙዚቃው ርዕሰ ጉዳይ ማንኛውም አይነት ቢሆንም እንኳ ለተመስጦ የሚጋብዝ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በሙዚቃ ስራው የመራሔነቱን ስራ የሰራው ኢትዮጵያዊው ዳዊት ሲሆን ከእርሱ ጋር በመሆን በሙዚቃ አልበም ስራዋ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ለዛ ለመስጠት መስራታቸውን ትገልፃለች፡፡ ‹‹ እኔ እና ዳዊት በህይወት ሂደታችን ኢትዮጵያዊ ቤተሰቦቻችን ውስጥ ያየነውን የጥቁር ውበት መያዝ ፈልገናል እናም ምስራቅ አፍሪካዊውን ዘውዳዊ ውበት ከቀለም እና ጌጦች ጋር አካተን ተጠቅመናል›› ትላለች፡ ፡ ፀጉሬን ለረጅም ጊዜ አፍሮ አርጌ ቆይቻለሁ በኋላም ለስላሳ ግራጫ ፀጉር ተመኘቼ ብቆይም ፀጉሬን ተፈጥሮውን መቀየር ሳያስፈልገኝ ማቆየትም ሌላ መንገድ መሆኑን ተረዳሁኝ፡፡›› ጠይም ኢትዮጵያዊ መልክ ያላት መረባ የፊት ገፅታዋ ውበት ራሷን የምትገልፅበት መንገድ አድርጋዋለች፡፡ አዲስ በለቀቀችው አልበምም ፀጉሯን በቴዎድሮስ ሹሩባ አስውባ ትታያለች፡፡

# የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በደቡብ አፍሪካ ከትናንትና እስከ ዛሬ



ተረፈ ወርቁ

ከሁለት ሳምንት በፊት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከትን ማእከል አድርጎ፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለመላው ጥቁር ሕዝቦች እና ለደቡብ አፍሪቃ ነጻነት ያበረከተችውን አስተዋጽኦ በተመለከተ አንድ ጽሑፍ ማስነበብ ጀምሬ ነበር፤ ለዛሬ ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል እነሆ ብያለሁ።

## የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ምሥረታ በደቡብ አፍሪቃ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በደቡብ አፍሪቃ ምድር የተመሠረተችበት ሐዋርያዊ ተልእኮ የሚመዘዘው ቤተክርስቲያኒቱ ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ነጻነት፣ ሉዓላዊነት ከከፈለችው መሥዋዕትነትና ለሕዝቦቿ ፍቅር፣ ሰላም እና ኅብረት መሠረትና መምህር ከመሆኗ እውነታ የሚመዘዝ ነው።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በደቡብ አፍሪቃ እውን መሆን ጅማሬውና ሂደቱ ባለፈው ጽሑፌ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ዘመናትን ከሚሻገረው የቤተክርስቲያናችን እና የደቡብ አፍሪቃውያን ነጻነት ናፋቂ ሕዝቦች የመንፈስ ግንኙነት ወይም ትስስር ነው። እናም "የዓለም ሕዝብ መኖሪያ ምድር/Rainbow Nation" ደቡብ አፍሪቃ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፍ ሐዋርያዊ ተልእኮ እና የስብከተ-ወንጌል አገልግሎት/Great Commission and Ministry ትልቅ መሠረት የጣለ ሕያው የታሪክ ምስክር ነው ማለት ይቻላል።

ይህን የቤተክርስቲያናችንን ሐዋርያዊ ተልእኮ በደቡብ አፍሪቃ ምድር ልዩ መገለጫ እንዲኖረው ያደረገው ደግሞ ከነጻነት በኋላ በመቶ ሺሕዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወደዛ ምድር መፍለሳቸው ነው። የእነዚህ ወገኖቻችን በደቡብ አፍሪቃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየተበራከተ መምጣትና በዛ ምድር ለቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት እና ሐዋርያዊ ተልእኮ ትልቅ በርን እንዲከፈት ዋንኛ ምክንያት ሆኗል።

ይኽም ጥንታዊት/Ancient፣ ሐዋርያዊት/Apostolic፣ አንዲትና ኩላዊት/Universal፣ አፍሪቃዊት እናት ቤተክርስቲያን/Mother African Church የኾነችውን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን በዓይናቸው ለማየት ይመኙ ለነበሩና በሩቅ ይሳለሚትና ይናፍቋት የነበረችው ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተክርስቲያን በመካከላቸው መገኘቷ ለደቡብ አፍሪቃውያን ጥቁር ሕዝቦች ትልቅ መነቃቃትንና ሐሴትን ነበር የፈጠረላቸው።

በደቡብ አፍሪካ የዘረኛው የአፓርታይድ ሥርዓት መገርሠሥ በኋላ በአሜሪካና በካረቢያን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ነፍሰ ኄር ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ያደረጉት ሐዋርያዊ ጉብኝት በደቡብ አፍሪካ ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ን እና በኢትዮጵያ እናት ቤ/ን ግንኙነት መካከል ታሪካዊ ሊባል የሚችል የመሠረት ድንጋይ አስቀመጠ። ከዛም በመቀጠል ነፍሰ ኄር ፓትርያሪክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አባቶች በ፲፱፻፺ዎቹ መጨረሻ ገደማ በደቡብ አፍሪካ ያደረጉት ሐዋርያዊ ተልእኮና መንፈሳዊ ጉብኝት በኹለቱ አገራት በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የእናት እና ልጅ ግንኙነትን ዕውን አደረገው።

በወቅቱም ቅዱስነታቸው ነፍሰ ኄር ፓትርያሪክ አቡነ ጳውሎስ ከብፁዓን አባቶች ጋር በደቡብ አፍሪካዊቷ የወደብ ከተማ በፖርት ኤልዛቤት በሚገኘው የደቡብ አፍሪካውያኑ ቅዱስ መስቀል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተገኝተው ባስተላለፉት መንፈሳዊ መልእክታቸው እና የወንጌል ስብከታቸውም፡-

‹‹… የአፓርታይድ ዘረኛ መንግሥት ቅዱስ



ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ

ወንጌል በአንድ መንፈስ ያስተሳሰራቸው ሕዝቦች እንዳይገናኙ የጋረደው ፅልመታዊ መጋረጃ ተነሥቷል፣ ከአሁን ወዲያ ቤተ ክርስቲያናችን ቤተ ክርስቲያናችሁ፣ ሕዝባችንም ሕዝባችሁ፣ ታሪካችንም ታሪካችሁ ነው!›› በማለት ነበር የወንጌል ቃል እውነት ያስተሳሰራቸውን የኹለቱ አብያተ ክርስቲያናትን የእናት እና ልጅ ጠንካራ የኾነ የመንፈስ ግንኙነታቸውንና ትስስራቸውን ያበሰሩት።

ነፍሰ ኄር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በተጨማሪም ከደቡብ አፍሪካውያኑ መካከል ካህናትን እና ዲያቆናት በመሾም በኹለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተጀመረው ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ትልቅ አሻራን ትተዋል። ከእነዚህ ካህናት መካከልም በፓትርያሪክ አቡነ ጳውሎስ ግብዣ በኢትዮጵያ ተገኝተው የከተራንና የጥምቀትን በዓል አብረውን እንዲያከብሩ፣ በአገራችን የሚገኙ ታላቅ ገደማትና አድባራት በመጎብኘም የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊ ታሪክ፣ ቅርስ፣ ባህልና ትውፊት በማየት ለሕዝባቸው በሚገባ እንዲያስተምሩ ዕድል አመቻችተውላቸውም ነበር። በተጨማሪም በቅዱስ ሲኖዶስ ትእዛዝና መመሪያ ሦስት መምህራን በደቡብ አፍሪካ የስድስት ወራት ቆይታ በማድረግ ለደቡብ አፍሪካውያኑ ኦርቶዶክሳውያን ሥልጠናም ሰጥተው ነበር።

ከዚህም ጋር ተያይዞ የዛን ጊዜው ቆሞስ አባ ገብርኤል የአሁኑ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ወደ ደቡብ አፍሪካ ተሹመው መምጣት በደቡብ አፍሪካ ምድር፣ የአገር ቤቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እናት ቤ/ን ህልውና እና ሐዋርያ ተልዕኮዋን ዕውን እንዲኾን አደረገው። ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት በነበራቸው ቆይታም ሕዝበ ክርስቲያኑን በማስተባበር በደቡብ አፍሪቃ የተለያዩ ግዛቶችና ከተሞች በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል፤ ጉባኤያትንም አስፋፍተዋል። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ ከኢትዮጵያ ውጭ ኹለተኛ የኾነውን ገዳም እና የካህናት ማሰልጠኛ በደቡብ አፍሪካዊቷ የሊጅስትሌቲቭ ከተማ በብሉምፎንቴን እንዲቋቋም አድርገዋል።

በደቡብ አፍሪቃ ያላቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ላለፉት አስራ አራት ዓመታት በመንፈሳዊ አባትነት እየመሩ ያሉት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በሀገረ ስብከቱ ቆይታቸውም በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል። ብፁዕነታቸው የመላው አፍሪቃ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ከመሾማቸው ባሻገርም የአፍሪቃ አብያተ ክርስቲያናት ►

ካውንስል ፕሬዚደንት ሆነው በሓላፊነት በቆዩባቸው ጊዜያትም በአህጉራችን አፍሪካ ሰላምና ፍትሕ እንዲሰፍን፣ ስደትና መፈናቀል እንዲወገድ፣ ራብና ድህነት ይቀረፍ ዘንድ በተለያዩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሃይማኖታዊ ስብሰባዎች ላይ በመጋበዝ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎችንና ንግግሮችን በማቅረብ የቤተክርስቲያኒቱን በዓለም አቀፍ መድረክ ሐዋርያዊ አገልግሎቷና ተልእኮዋ ከፍ እንዲል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ለአብነትም ያህል ባሳለፍነው በሚያዝ ወር 2011 ዓ.ም. የደቡብ አፍሪቃ ፕሬዚደንት ጽ/ቤት፤ Presedential Declaration for a Societal Renewal: Towards Achieving a South Africa We Want to Live In በሚል መርሕ ቃል ቃል በተዘጋጀው ጉባኤ ላይ በመገኘት፤ ብፁዕነታቸው በደቡብ አፍሪቃ ያለችው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለደቡብ አፍሪቃና ለመላው አፍሪቃ ሰላምና ፍቅር መጎልበት፣ አንድነትና ወንድማማችነት መጠናከር በርትታ እንደምትሠራ ገልጸው ነበር፡፡ ብፁዕነታቸው የደቡብ አፍሪቃው ፕሬዚደንት ሲሪል ራማፎሳና የአገሪቱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በተገኙበት በዚህ መድረክ ላይም ባደረጉት ንግግርም፤ "የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ከሃይማኖት አባቶችና መንፈሳዊ መሪዎች ጋር በመተባበር በደቡብ አፍሪቃና በአህጉሩ 'ሁለተናዊ ማኅበረሳባዊ ለውጥ' እንዲመጣ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የቤተክርስቲያኒቱ ሐዋርያዊ ተልእኮ አካል መሆኑንና ለሌሎች የአፍሪቃ ሀገራትም መልካም ተሞክሮ እንደሆነ አንስተው ነበር፡፡

ይህን የቤተክርስቲያኒቱን ሐዋርያዊ ተልእኮ በሀገረ ደቡብ አፍሪቃ በማስፋፋት ረገድ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ክብፁዕ አቡነ ያዕቆብ፣ ከቤ/ቱ መንፈሳዊ አባቶች፣ መሪዎችና አገልጋዮች ባሻገርም ኢትዮጵያውያንና ደቡብ አፍሪቃውያን ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ትልቅ ተሳትፎና ድርሻ ነበራቸው፤ አሁንም አላቸው፡፡ እንዲሁም የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት፣ በኢትዮጵያ የደቡብ አፍሪቃ ኤምባሲ እና የሥራ ሓላፊዎችም ሀገራችን ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለደቡብ አፍሪቃ ነጻነት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት እያበረከቱት ያለው አስተዋጽኦ በትልቁ የሚጠቀስ ነው፡፡

## እንደ ማጠቃለያ

በአፍሪቃ፣ በሰሜን አሜሪካ፣ በካረቢያንና በጃሜይካ በሚገኙ ሕዝቦች ዘንድ የነጻነት ተምሳሌት እና የተስፋ ምድር ተደርጋ የምትወሰደው የኢትዮጵያ ቤ/ን በጥቁር ሕዝቦች ዘንድ አሁንም ድረስ ልዩ ክብር እና ስፍራ ያላት ናት፡፡ በወንጌል ስብከት ስም የምዕራባውያን ቅኝ ገገርዎች የባህል ወረራ ያልነካት፣ ለበርካታ ዘመናት ብሉይን ከሐዲስ አስማምታ፣ የክርስትና ሃይማኖትን አስተምህሮ፣ መንፈሳዊ ሥርዓት፣ ባህል እና ትውፊት ጠብቃ የቆየች፣ ሐዋርያዊት ትክክለኛ፣ ቀደምት አፍሪካዊት እናት ቤ/ን (Independent African Mother Church) በሚል ክብር የሚጠሯት፣ የሚያሞኳሽዋት ናት፡፡

ከዚህ የታሪክ እውነታ ጋር በተያያዘም ከጆሐንስበርግ መድኀኔዓለም ካቴድራል እስከ ኬፕታውን ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክ፣ ከቡሉምፎንቴን የቅድስት ሥላሴ ገዳም እስከ ደርባን ቅድስተ ማርያም ቤ/ክ፣ ፒተስበርግ ቅድስት አርሴማ፣ ቦትስዋና ቅዱስ ጊዮርጊስ ... ወዘተ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በዛ ምድር መመሥረት እና ማበብ በደቡብ አፍሪቃውያን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የጸሎትና የምክር፣ የገንዘብ እና የቁሳቁስ፣ የጉልበትና የሞራል፣ የእውቀትና የሐሳብ ድጋፍ በትልቁ የሚጠቀስ ነው፡፡

ይህን ትልቅ ሕዝብ/የሰው ሀብት ለበለጠ መንፈሳዊ አገልግሎትና ለቤተክርስቲያን ሁሉን አቀፍ የልማት ሥራ የበረታ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ቤተክርስቲያን የጀመረችውን ትልቅ ሥራ አጠናክራ መቀጠል ይኖርባታል፡፡ ቤተክርስቲያን ከኖላዊነት ባሻገር የልጆቿን ኢኮኖሚያዊ አቅም እና ሳይንሳዊ እውቀታቸውን በመጠቀም በአፍሪካ ምድር ለታሪኳና ለክብሯ የሚመጥን ሥራን በመሥራት ረገድ በሙሉ አቅሟ እየተንቀሳቀሰች ነው ማለት የሚቻል አይመስለኝም፤ ስለሆነም ቤተክርስቲያን "ወደ እኛ ኑልን!" እያሉ የሚጣሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪቃውያንን ለመድረስ በደቡብ አፍሪቃ ያላትን ሐዋርያዊ ተልእኮ እና የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በሚገባ ማጠናከር አሁንም በእጅጉ ያስፈልጋታል፡፡

"ከዓለም ሁሉ ሕዝቦች ቀድማ የወንጌልን የምሥራች የሰማች፤ በታሪኳና በሥልጣኔዋ ታላቅና ገናና የነበረች ሀገር - በኋለኛው ዘመን አውሮጳውያን በወንጌል አገልግሎት ሰበብ አፍሪቃን ሲቀራመቱ፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ለዚህን ያህል ዘመናት ቅዱስ ወንጌልን ለአፍሪቃውያን ሕዝቦች እንዴት ሳታዳርስ ቀረች?!" ለሚለው የአፍሪቃውያን ከፍቅር፣ ከበረታ መንፈሳዊ ቅንአት እና ቁጭት የመነጨ ወቀሳ እና ክስ መልስ ለመስጠት ከተሠራ አሁንም የሚረፍድ አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቤተክርስቲያን በአፍሪቃ እና በመላው ጥቁር ሕዝብ ዘንድ ያላትን ይህን ትልቅ ተቀባይነት እና ክብር እንደመልካም አጋጣሚ መጠቀም ይኖርብናል፡፡

እዚሁ አሳቤ ላይ አንድ ቁም ነገር ግን አስረግጬ ላልፍ እፈልጋለኹ፡፡ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዓለም አቀፍ መድረክ ካላት ክብር እና ረጅም ታሪክ አንፃር ልንቆጭበት የሚገባ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ለሺሕ ዘመናት በሕገ ልቦና፣ በሕገ ኦሪት፣ ከዛም በሕገ ወንጌል ጸንታ የቆየች፣ የራሷ የኾነ ቋንቋና ፊደል ያላት፣ ዜማን ከእንምልክቱ ለዓለም ያስተዋወቀች፣ ሰማያዊ የኾነ የአምልኮ ሥርዓት፣ ጠንካራ መንፈሳዊ ባህልና ትውፊት ያላት ቤ/ን መሆኗን ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ መንፈሳዊ ሀብቶቿና ቅርሶቿ የረጅሙም ዕድሜያችንን ያህል በየትኞቹ አፍሪቃ ሀገራትና ሕዝቦች መካከል መንፈሳዊ አሻራውን ትቷል ብለን ብንጠይቅ ምላሹ እምብዛም የሚማርክ አይደለም፡፡


እናም የአሁኑ የቤተ ክርስቲያናችን ወጣት ትውልድ፣ መንፈሳዊ መሪዎችና አገልጋዮች ለዚህ የዘመናት የአፍሪቃውያን ወንድሞቻችን፤ "ከዓለም ሁሉ አስቀድማችሁ ወንጌልን የሰማችሁ እናንተ ኢትዮጵያውን የወንጌልን የምስራች ቃል ከእናንተ መስማት ሲኖርብን በኋለኛው ዘመን አውሮፓውያን በስብከተ ወንጌል ስም ምድራችን ሲወሩ ሀብታችን ሲዘርፉ፣ ሕዝባችንን በባርነት ሲያግዙ የት ነበራችሁ?!" ለሚለው ጥያቄቸው፣ ክስና ሙግታቸው መልስ መስጠት ግዴታችንም ኃላፊነታችንም መሆን ያለበት ይመስለኛል፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደምንታዘበው አሁንም ድረስ በርካታ አፍሪቃውያንና ጥቁር ሕዝቦች የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በጉጉትና በናፍቆት፣ በስስትና በአድናቆት ዓይን ነው የሚመለከቷት፡፡

እናም ቤተ ክርስቲያናችን በአህጉረ አፍሪቃ፣ በመላው ጥቁር ሕዝቦችና በተለይም ደግሞ በደቡብ አፍሪቃ ምድር ካላት ግዙፍ የሆነ ታሪካዊ መሠረትና ተቀባይነት አንፃር የስብከተ ወንጌል አገልግሎቷን ከራሷ ሕዝቦች አልፋ ሌሎች አፍሪቃውያንና የዓለም ሕዝቦች በማዳረስ ረገድ ገና ብዙ ሥራ እንደሚጠበቅብን ግልጽ ነው፡፡

ስለሆነም የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ አካልና የመንፈስ ቅዱስ ጉባኤ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስም ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን በደቡብ አፍሪቃ ያላትን የታሪክ ክብር፣ የነጻነት፣ የመንፈስ ልእልናን እና በዛ ምድር የሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የቤተክርስቲያን ልጆችን ናፍቆትና ጉጉት ከግምት ውስጥ በማስገባት በደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት የተጀመረውን ትልቅ ሐዋርያዊ ተልእኮ በቅርብ ትኩረት ሰጥቶ ሊከታተለው የሚገባው ነው እላለኹ፤ ምክንያቱም የደቡብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊ ሐዋርያዊ ተልእኮና መንፈሳዊ አገልግሎት ትልቅ እና ዋና ማእከል መሆን የሚችል ነውና!! ሰላም!!

***...የቤተክርስቲያናችንን ሐዋርያዊ ተልእኮ በደቡብ አፍሪቃ ምድር ልዩ መገለጫ እንዲኖረው ያደረገው ደግሞ ከነጻነት በኋላ በመቶ ሺሕዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወደዛ ምድር መፍለሳቸው ነው...***

*ዲ/ን ተረፈ ወርቁ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ እና ቅርስ አስተዳዳር የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ሠርተዋል፤ በመቀጠልም በደቡብ አፍሪቃ ኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ በአፍሪቃ ታሪክ እና ቅርስ ጥናት የድኅረ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆኑ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በደቡብ እና ምዕራብ አፍሪቃ ሀገረ ስብከት ለኹለት ዓመት ያህል ዋና ጸሐፊ/General Secretary በመሆን አገልግለዋል*



ብሩክ መኮንን

# ሀገር አሳሹ ዋልተር ሚትልሆዘር በኢትዮጵያ!!!



ሀገር አሳሽ የአቪየሽን ፈር ቀዳጅ በአውሮፕላን ዓለምን በመዞር የፎቶግራፍ ባለሙያ የሆነው የሲዊስ ዜግነት ያለው ዋልተር ሚትልሆዘር በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ እንዲሁም በአፍሪካ አህጉርን በአውሮፕላን በመዞር ከዓለማችን እውቅ ሀገር አሳሾች ተርታ የተሰለፈ ባለሙያ ነበር፡፡

በአፕሪል 2 ቀን 1864 በሲውዘርላንድ ሴንት ጋሊየን የተወለደው ዋልተር ሚትልሆዘር በ23 ዓመቱ በ1917 ዓ.ም ነበር የመጀመሪያውን የአብራሪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘው፡፡ የበራራ ትምህርቱን በመቀጠል በጦር አውሮፕላን አብራሪነት ለአንድ ዓመት የወሰደውን ስልጠና አጠናቆ በ1918 መጨረሻ ላይ በዲፕሎም ተመረቀ፡፡

በኖቬምበር 5 ቀን 1919 (እ.ኤ.አ) የራሱን ከአየር ላይ ፎቶግራፎችን የማንሳት ስራ የሚሰራ የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን ከሜት ሚትልሆልዘር ኩባንያን አቋቋመ፡፡

በ1920 ኢድ ኦስተር ኦሮ ከተሰኘ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም ካለው ሌላ ኩባንያ ጋራ በመዋሃድ የኩባንያ ዳይሬክተርና በኩባንያው ስር ያሉ አብራሪዎች ዋና አብራሪ ሆኖ ይሰራ ጀመር፡፡

ኢድ ኦተር ኢሮ የተባለው ኩባንያ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም ስለነበረው ከዓመታት በኋላ የዝነኛው የሲዊስ አየር መንገድን ኩባንያን ከ ዋልተር ሚትልሆዘር ጋራ በመሆን መሰረቱ፡፡

ዋልተር ሚትልሆዘር ለመጀመሪያ ጊዜ ከአውሮፓ ወደ ደቡብ አፍሪካ ያደረገውን 77 ቀናት የፈጀ ጉዞ ከዙሪክ ዲሴምበር 17 ቀን 1926 በመነሳት በአሌክሳንደሪያ አድርጎ ኬፕታውን (ፌብሩዋሪ 21 ቀን 1927) በመድረስ በስኬት አጠናቋል፡፡

ዋልተር ሚትልሆዘር ከ1923 ጀምሮ በሞሮ ፕሌን በጃከር በመብረር ውጤታማ የአየር ላይ ቅኝት እና የፎቶግራፍ ማንሳት ስራዎችንም አከናውኗል፡፡

ሀገር አሳሹ ዋልተር ሚትልሆዘር ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኋላ በዓለም ፖለቲካ ውስጥ እየገነኑ የመጡት የጀርመኑ የናዚ ፓርቲና የኢጣልያ የፋሺስት ፓርቲ አመራሮች ሙሉ ድጋፍ ነበረው፡፡ በተከታታይ አመታት ባደረጋቸው በረራዎች ያነሳቸው ፎቶግራፎች እና ፊልሞች በናዚ አመራሮች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትና ከበሬታ አስገኝተውለት ነበር፡፡

በ1930ዎቹ መጀመሪያ ላይ ስለ አየር ላይ ጉዞው እና በአፍሪካ እና በመካከለኛው ምስራቅ ያደረገውን የሀገር አሳሽነት ተግባር የሚተርኩ በተከታታይ ያሳተማቸው መጽሐፎች ላይ ቀዳሚ ቃል የፃፉለት የጀርመን የናዚ ፓርቲ ቁልፍ ባለስልጣን፤ እንዲሁም የጀርመን አየር ኃላፊዎች የሊፊትዎፍ ዋና አዛዥ ሐመርን ጎሪንግ እና የኢጣልያው የአቬዬሽን ሚኒስትር ኢታሎ ቦልቦ የተሰኙት ታዋቂ ግለሰቦች ነበሩ፡፡

ሐመርን ጎሪንግ የዋልተር ሚትልሆዘር ያሳተመው መፅሐፍ ላይ ባሰፈረው ቀዳሚ ቃል “ዋልተር ሚትልሆዘር የፎቶግራፍ ባለሙያ ድንቅ ብቃቱን ያሳየበት ሥራ ነው፡፡ ከደመና በላይ ሆኖ የምንገዛትን ዓለም በካሜራው በደንብ ቃኝቷል፡፡ ዋልተር በየደረሰበት በአፍሪካ የጀርመን፣ የኢጣልያ፣ የብሪታኒያ የፈረንሳይ ቀኝ ግዛቶቻችን መልከአምድርንና ሕዝቦችን በሚገባ የማስተዋወቅ ሥራ ለማከናወን ችሏል፡፡ ስለዚህ ሊመሰገን ይገባዋል” ብሏል፡፡

ዋልተር ሚትልሆዘር በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ያደረገውን ሀገር አሳሽነት ተግባር ሲያከናውን በናዚዎች “አድብ” የሚል ማስጠንቀቂያ ያልተሰጠው ምናልባትም እነርሱ በዓለም ብቸኛዋን ኃይል መንግስት ለመመስረት ያላቸውን አላማ ተቀብሎ ለእነርሱ ይሰራ ስለነበረ ነው የሚሉ ወገኖች አልታጡም፡፡

ከናዚዎች ከፍተኛ ድጋፍ ከማግኘቱ በተጨማሪም በዓለማችን የፋይናንስ ከሞላ ጎደል ይቆጣጠራሉ፡፡ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪነት ሚና የነበራቸው የባንኮች ባለቤት የሶሻሊስት ርዕዮት አራማጅ በአሳታሚነት በዓለማችን ታዋቂ የመገናኛ ብዙሃንን በቁጥጥራቸው ስር ያደረጉ የሊዮስ ቮን ሮትሺቻይልድ ከፍተኛ የገንዘብ እገዛ ስፖንሰርነት ጉዞውን እንደሚያደርግ ይታወቅ ስለነበረ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ሀገር አሳሽ የስዊስ የአቭየሽን ፈር ቀዳጅ የፎቶግራፍና የፊልም ባለሙያ የሆነው ዋልተር ሚትልሆዘር ከኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት ከአፄ ኃይለስላሴ ጋራ የቀረበ ወዳጅነት እንደነበረው ይነገራል፡፡

አፄ ኃይለስላሴ ሀገራቸው የዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰብ ደርሶበታል ብለው የሚያምኑ የአቪየሽን እድገት ተቋዳሽ እንድትሆን ሲንቀሳቀሱ ከዋልተር ሚትልሆዘር ጋራ በበርካታ ጉዳዮች ላይ መምከራቸው ይነገራል፡፡

ኢትዮጵያ ከ1930 ጀምሮ የአቪየሽን እንቅስቃሴን በመጀመር በፈረንሳዮች እና በጀርመኖች አማካይነት አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ኢትዮጵያውያን አብራሪዎች እንዲሰለጥኑ በማድረግ “ጃንካርስ ፓቴዝ እና ፈርማን” የተሰኙ ኩባንያዎች ▶

ያመረቷቸው አውሮፕላኖችን በመግዛት በደሴ፣ ድሬድዋ ደብረማርቆስና በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች በተዘጋጁ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎች አማካይነት የመንገዣ አገልግሎት ይሰጡ ነበር።

ዋልተር ሚትልሆዘር ከንጉሰ ነገስቱ የቅርብ አማካሪዎች ከነበሩ የሀገሩ ዜጎች ጋራ በተመካከረው መሰረት በዳይሬክቶሬት የሚያስተዳድረው የአየር ትራንስፖርት ኩባንያ ንብረት የሆነች ፎክር FVIIB የተባለ አውሮፕላን በመያዝ ከዙሪክ አዲስ አበባ ድረስ የተሳካ በረራ ለማድረግ ችሏል።

ዋልተር ሚትልሆዘር በ1934 ከዙሪክ በመነሳት 71118 ኪሎሜትርን የሸፈነ በርካታ ሳምንትን የወሰደ ሥራ ለማድረግ ከአውሮፕላን አብራሪው በተጨማሪ ስምንት መንገደኞችን በማሳፈር ወደ ኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ ለመብረር ሲዘጋጅ ብዙዎች እንዴት ነው ነገሩ ? የሚል አቋም ይዘው ተቃውመውት ነበር።

ስድስት ወንዶች ሁለት ሴት ተሳፋሪዎች ያሳፈረው አምስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠኝ ኪሎ ግራም የመጫን አቅም ያለው ፎከር አውሮፕላን ከፓይለቱ ጋር በመረዳዳት በሰዓት 168 ኪሎ ሜትሮች እየተጓዘ ነበር፤ ጃንዋሪ 24 ከዙሪክ በመነሳት ወደ አዲስ አበባ መብረር የጀመረው ዋልተር ሚትልሆዘር።

ሀገር አሳሹ ወደ ኢትዮጵያ እያበረረ ያመጣው ፎከር አውሮፕላን ንብረትነቱ የሲዊስ ኤየር የነበረ ሲሆን ለኢትዮጵያ መንግስት እንዲያገለግል በስጦታ የተሰጠም ነበር። አውሮፕላኑ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ ለንጉሰ ነገስቱ በስጦታ የሚሰጡ በርካታ ሻንጣዎችንና የአፄ ኃይለስላሴ "ቀ.ኃ.ስ" የሚል የክብር ምልክት በወርቅ የተለበጠ አዲስ ወንበርም ጭኖ ነበር።

ፌብሪዋሪ 16 ቀን 1934 ሀገር አሳሹ ዋልተር ሚልሆዘር ከሱን ዋዲ ሔልፋ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ እያመራ መሆኑን በቴሌግራም ለንጉነገስቱ አሳውቆ ስለነበር አውሮፕላኑን ለመቀበል አዲስ አበባ ያሉ የሲዊስ ተወላጆችና ንጉሳዊ ቤተሰቦች በአዲሱ አውሮፕላን ማረፊያ ይጠባበቁት ጀመር።

ዋልተር ሚትልሆዘርና ሲዊሳውያን ባልደረቦቹን የያዘው ፎከር አውሮፕላን አዲስ አበባ ደርሶ በሰላም እንዳረፈ፤ ለእንግዶቹ ክብር የሪሴፕሽን ግብዣ ተካሄደ። ዋልተር ሚትልሆዘር አውሮፕላኑን ለቀዳማዊ ኃይለስላሴ አስጎብኝቶ ያመጣቸውን በርካታ ሻንጣ ገፀ በረከቶች እና ንጉሱ እንደ ዙፋን የሚገለገሉበት በወርቅ የተለበጠ አዲስ ወንበር ለንጉሱ አስረከበ።

ለጥቂት ሳምንታት ወደ ደቡባዊ ኢትዮጵያ የንጉሰ ነገስቱ ግዛቶች በማምራት ሲጎበኝ እና የታወቀበትን የሀገር አሳሽነት የፎቶግራፍ ማንሳት ሥራውን ሲያከናውን የቆየው ዋልተር ሚትልሆዘር በቅርቡ ከሌላ የአቪየሽን ባለሙያዎች የሚገኙበት ቡድን የፊልም አንሺ ባለሙያዎች ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ቃል በመግባት ወደ ሲዊስ ለመመለስ እየተዘጋጀ እያለ አፄ ኃይለስላሴ ለስዊሱ የአቭየሽን ፈርቀዳጅ ሀገር አሳሽ ዋልተር ሚትልሆዘር በወርቅ የተለበጠ ጋሻ እና ጎራዴ እንዲሁም ልዩ ልዩ ስጦታዎችን አበርክተውለት የመሸኛ ግብዣ አድርገውለት ወደ ዙሪክ ይመለሳል።

ከጥቂት ሳምንታት የስዊዘርላንድ ቆይታ በኋላ ዋልተር ሚትልሆዘር "ቤርና ቮም ፍሉግ" የተባለ የፊልም ባለሙያዎች የያዘ ቡድን እንዲሁም የፎከር አውሮፕላን ቴክኖሎጂን የሚያስተዋውቁ ቴክኒሺያኖች በመያዝ ሁለተኛውን ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ያደርጋል።

ለወራት በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር የፊልም ቀረፃ ሥራ እንዲሁም መኳንንቱ ጭምር በመኖሪያ ቤታቸው፣ በቤተክርስቲያን፣ በቤተመንግስት፣ በፍርድ ቤቶች የሚካሄዱትን የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች፣ የተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦችን ባህልና የአኗኗር ስርዓትን የተመለከቱ ፊልሞችን ሲያስቀርፅ አብሮ ሲያካሄድ ከሰነበተ በኋላ ተልዕኮውን አጠናቆ ወደ ሀገሩ ይመለሳል።

ሀገር አሳሹ ዋልተር ሚትልሆዘር በአፍሪካ በርዝመቱ ተወዳዳሪ የሌለውን የኪሊማንጀሮ ተራራ አናት ላይ በመብረሯ ኬንያና ሱዳን ታንዛኒያ ግብፅን የሸፈነ ታሪካዊ በራራ እና የፊልም ቀረፃ ስራዎችንም አካሄዷል።

ለበርካታ ጊዜያት ወደ ኢትዮጵያ በማምራት በኢትዮጵያ በርካታ ጉዞዎችን የፊልም ቀረፃዎችን ያካሄደው ዋልተር ሚትልሆዘር በቀጣይ የዓለማችን በርዝመቱ ተወዳዳሪ የሌለው የኤቨረስት ተራራ አናት ላይ ለመብረር አቅዶ እየተዘጋጀ ነበር።

ዋልተር ሚትልሆዘር በጊዜው ያደረጋቸው በነበሩ በረራዎች በአሁኑ ጊዜ ያሉ የአቭየሽን ኢንዱስትሪ ባልደረቦች የማይሞከርና ራስን ከመግደል ያልተናነሰ ተግባር ነው የሚሉት ዓይነት በርካታ በርሜል፣ ለአውሮፕላኑ የሚያስፈልጉ የአውሮፕላን ነዳጅን በአወሮፕላን ውስጥ ጭኖ ነበር የሚጓዘው።

ከ1931 ጀምሮ የራሱ ኩባንያን ኢድ ኦስፖርር ኢሮ ኩባኒያን ከሌላ "ባልኤ" ከተባለ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭ ኩባንያ ጋራ በማዋሀድ የስዊስ አየር የተባለው ኩባንያ ቴክኒካል ዳይሬክተር በመሆን የሰራው ዋልተር ሚትልሆዘር በኢትዮጵያና በአፍሪካ እንዲሁም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በመዘዋወር ያነሳቸውን ፎቶግራፎ ከጉዞ ማስታወሻዎች ጋራ በማጣመር በርካታ መፅሐፎችን አሳትሟል።

ከዚህም በተጨማሪ በርካታ ቁጥር ያላቸው ፊልሞችን ሰርቶ ለቴሌቭዥን፣ ለሲኒማ ኢንዱስትሪዎች በመሸጥ ከፍተኛ ገቢ አግኝቷል።

በ1937 በኦስትሪያ ሆቪ ሸዋብ ማሰይፉ በተባለ ከፍተኛ ርዝመት ያለውን ተራራ ከባልደረቦቹ ጋራ በመወጣት ላይ እያለ በደረሰበት አደጋ ሜይ 9 ቀን በአርባ ሶስት አመቱ ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል።

ታዋቂው ሀገር አሳሽ ስዊስ አቬየሽን ፈር ቀዳጅ ዋልተር ሚትልሆዘር አብራሪነት ከስዊስ አየር መንገድ ለአፄ ኃይለ ስላሴ የተበረከተው ፎከር አውሮፕላን ከፌብሩዋሪ 23 ቀን 1934 ጀምሮ አገልግሎት እየሰጠ ቆይቶ የኢጣልያን ወረራ መጀመርን ተከትሎ የኢትዮጵያ የአቬየሽን አገልግሎት አደጋ ላይ ስለወደቀ አውሮፕላኑ ከሌሎች አውሮፕላኖች ጋራ ተፈታቶ ወደ አንድ ያልታወቀ ስፍራ ተወሰደ።

በ1936 ሜይ ወር ተፈታትው የተደበቁት አውሮፕላኖች ተደብቀው የተቀመጡበት ስፍራን በሚጠብቅ አንድ ጠባቂ አማካይነት እሳት ተለኩሶበት አውሮፕላኑ ወደመ።

ዋልተር ሚትልሆዘር ለበርካታ አመታት በመላው አለም በመዘዋወር ያነሳቸው 18 ሺህ 500 በላይ የሚሆኑ ድንቅ የፎቶግራፍ ሥራዎቹ፣ የፊልም ጥቅሎች በአሁኑ ወቅት በስዊዝ ሀገር በዙሪክ አቲ ቤ መጻሐፍት ወመዛግብት ውስጥ በክብር ተቀምጠዋል።

ሀገር አሳሹ የስዊስ አቬየሽን ፈር ቀዳጅ የፎቶግራፍ ባለሙያው የዋልተር ሚትልሆዘር የሌሎች የስዊስ አየር መስራቾች መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የሲዊስ የፖስታ ድርጅት በ1977 የፖስታ ቴምብሮች ያሳተመላቸው ሲሆን በዙሪክ አለምአቀፍ አየር ማረፊያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለዋልተር ሚትልሆዘር መታሰቢያ ሐውልት ቆሞለታል፡

**አማካሪዎች ከነበሩ የሀገሩ ዜጎች ጋራ በተመካከረው መሰረት በዳይሬክቶሬት የሚያስተዳድረው የአየር ትራንስፖርት ኩባንያ ንብረት የሆነች ፎከር FVIIB የተባለ አውሮፕላን በመያዝ ከዙሪክ አዲስ አበባ ድረስ የተሳካ በረራ ለማድረግ ችሏል።**

# "ልዑል አስወደደኝ!"

## የአፄ ኃይለስላሴ የልጅ ልጅ

ብሩክ መኮንን



ከዓመታት በፊት ነበር የእንግሊዘኛ ቋንቋ የዶክትሬት ትምህርቴን አቋርጬ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኝ ቡቲክ ውስጥ ሥራ የጀመርሁት፡፡ ይህ ውሳኔዬ በአጠቃላይ የሕይወቴን አቅጣጫ የቀየረ እንደሆነ ግን አላውቅም ነበር፡፡ ውሳኔዬን ተከትሎም መላ የሕይወት መንገዴ ሌላ መልክ ያዘ፡፡ ያደግሁት የተለያዩ ዝርያዎች ውሀድ በሆነ ቤተሰብ ውስጥ፣ በደስታና በፍስሃ፣ በእንክብካቤ ነው፡፡ ቤተሰባችን እርስ በርሱ ይዋደዳል፤ ሁለት እህቶች እና አንድ ወንድም አለኝ፡፡

አባቴ ደራሲ ነው፤ ቀደም ሲል የሶሺዮሎጂ ፕሮፌሰር ነበር አሁን በኬንታኪ የአንድ ፋውንዴሽን የሥራ መሪ ነው፡፡ እናቴም በጉያና የወርልድ አርትና ሂውማኒቲ ላይ የሚሰራ ተቋም ስራ አስኪያጅ ናት፡፡ መላው ቤተሰባችን በስነጥበብ እና በኪነጥበብ ዘርፍ ልዩ ትኩረት የሚያደርግ፣ በመማር የሙያ ባለቤት በመሆን ለማኅበራዊ ፍትህና የህዝብ ተጠቃሚነት የበኩሉን አገልግሎት ለመስጠት የሚተጋ ታታሪ አባላት ያሉት ነው፡፡

ሁላችንም ወደዚህ አለም ስንመጣ ካገኘነው የበለጠ የሰው ልጆችን የተሻለች ዓለም እንድትሆን የበኩላችንን በማድረግ እንባዝናለን፡፡ በዋሽንግተን በልብስ መሸጫ ቡቲክ መስራት ከጀመርኩ ብዙም ሳይቆይ በአንድ የሳምንቱ መጨረሻ ምሽት ከጓደኞቼ ጋራ ለመዝናናት ወደ ምሽት ክለብ ጎራ አልን፡፡ በናይት ክለቡ እንደ እኛው እየተዝናና ካለ አንድ መልከ መልካም ወጣት ተዋወቅሁ፡፡ወጣቱ እኔና ጓደኞቼን ስንጨፍር አይቶ ስትታዩ "የቦንቤ ሲጋራ ማስታወቂያ የምትሰሩ ትመስላላችሁ" ሲል በነገር ጠቅ አደረገን፡፡

...ልብ ለልብ ተፈቃቅደን አብረን መውጣት ጀመርን

በዚህ መሐል ነበር ያስተዋወቀኝ ጓደኞቹ "ልዑሉ እንዴት ነው?" እያሉ ሲጠይቁኝ ራሱን "ልዑል ነህ እንዴ?" ስል ጠየቅሁት እየሳቀ "አዎን ልዑል ነኝ፤ ልዑል ነው የወደድሽው" አለኝ...

መልከመልካም፣ ተጫዋች፣ ግልፅ አንዴ ከተዋወቁት ራቁት የማያሰኝ ልዩ መስህብ ያለው ወጣት ነው፡፡ በአባባሉ እየተሳሳቅን ጨዋታ ጀመርን፡፡ ወጣቱ ጆል እንደሚባልና በአሜሪካ ዩንቨርስቲ በዓለምአቀፍ ንግድ ሥራ ሁለተኛ ዲግሪውን ለማግኘት እየተማረ እንደሆነ፣ ወደ ናይት ክለቡ በዚያ ምሽት የተከሰተው የመጨረሻው ሴሚስተር ፈተናን ወስዶ ስላጠናቀቀ ዘና ለማለት እንደሆነ ነገረን፡፤

ጆል ወደ አሜሪካ ለሁለተኛ ዲግሪው ከመምጣቱ በፊት ይኖር የነበረው ፈረንሳይ ሀገር "ኒሳ "ውስጥ እንደነበርና የመጀመሪያውን ዲግሪ ትምህርቱ እዚያው ማጠናቀቁም ነገረን፡፡

በናይት ክለቡ የዳንስ ወለል ላይ እየደነስን እያለ ነው በፍቅሩ የወደቅሁት፡፡ ፍጹምተግባቢ፣ ጨዋታው ቀልብን የሚማርክ፣ ከተሜነቱ በራሱ ልዩ መስዕብ የፈጠረለት ነው፡፡ ይህው ጉብል የተወለደው ሮም ኢጣሊያ ሲሆን፣ በስዊዘርላንድ በሚገኝ የታወቀ አዳሪ ትምህርት ቤት ተምሯል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖር የነበረ ብዙ ቋንቋዎችን የሚናገር ነው፡፡

ከዚያ ምሽት በኂላ በደንብ ተግባብተን ስለቤተሰባችን ስናወራ፤ ጆል እናቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው እንደሚሰሩ፣ አባቱ በኢትዮጵያ ክቡርዘበኛ ሰራዊት ውስጥ ሻምበል እንደነበሩና ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ ነገረኝ፡፡ ይህን ያህል መተዋወቁ በቂ ነው ብዬ ስላመንኩኝ ስለቤተሰቡ ለማወቅ ብዙ ነገር አልጠየቅሁትም፡፡ ልብ ለልብ ተፈቃቅደን አብረን መውጣት ጀመርን፡፡

በዚህ መሐል ነበር ያስተዋወቀኝ ጓደኞቹ "ልዑሉ እንዴት ነው?" እያሉ ሲጠይቁኝ ራሱን "ልዑል ነህ እንዴ?" ስል ጠየቅሁት፡፡ እየሳቀ "አዎን ልዑል ነኝ፤ ልዑል ነው የወደድሽው" አለኝ፡፡

ይሄን ጊዜ በጥርጣሬና በድንጋጤ ተውጬ " እውነትህን ነው?" ስል በድጋሚ ጠየቅሁት፡፡ አሁንም በፈገግታ ታጅቦ "አዎን! ግን ብዙም ቦታ አትስጭው" አለኝ፡፡ አባባሉን በቀላሉ ሰምቼ አላለፍኩትም፤ "በጉዳዩ ላይ ማውራት አለብን" አልኩት፡፡ እሱ ግን ብዙም ፍላጎት አልነበረውምና ተወው፡፡ እኔ ግን እንዲነግረኝ ደጋግሜ ወተወትኩት፡፡

ጆልም ጥያቄዬ ሲጠነክር " ቅድመ አያቴ ቀደማዊ ኃይለ ስላሴ ናቸው" አለኝ፡፡ እኔም እንደ እናቴ ያሉ በዌስት ኢንድስ ተወላጆች ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ልዩ ስብዕና፣ አክብሮትና ፍቅር እንዳላቸው አውቅና እሰማ ስለነበረ፡፡ በእርግጥም የሕይወት እጣ ፈንታዬ "ልዑል አስወደደኝ" ብዬ እንዳስብ አደረገኝ" ትላለች፤ ▶

ባለፈው ሳምንት town and country የተሰኘ መጽሔት ላይ የአጼ ኃይለስላሴን የልጅ ልጅ ያገባችው አሜሪካዊትዋ ኤሪን መኮንን ስለ ፍቅር ሕይወትዋና ትዳርዋ በፃፈችው ፅሁፍ፡ ፡ ከአሁኑ ባልዋ ከልዑል ጆል ዳዊት መኮንን ኃይለስላሴ ጋራ እንዴት እንደተገናኙም ማራኪ በሆነ አገላለጽ አቅርባዋለች፡፡

ኤሪክ የልዑሉንና የእሷን ታሪክ መተረኩን ቀጥላለች፡-“እጅግ እየተቀራረብን መጣን፡ ፡ በተዋወቅንበት ዓመት ጆል ትምህርቱን አጠናቆ ወደ ፈረንሳይ ተመለሰ፡፡ ከጥቂት ሳምንታት በኂላ የነሀሴ ወር ላይ ፈረንሳይን እንድጎበኝ ጋበዘኝ፡፡

አይደርስ የለም ነሐሴ ደርሶ ፈረንሳይ ተጓዝሁ፡፡ በደቡብ ፈረንሳይ እጅግ ደስ የሚያሰኝ የዕረፍት ጊዜን ከጆል ጋር አሳለፍን፡፡ በደቡብ ፈረንሳይ የባህር ዳርቻዎች ስንጓዝና ስንዝናና፣ በየጠዋቱ ትኩስ ፍራፍሬዎች እየበላን የኬኒዌስት እና የፈረንሳይ ሂፕሆፕ ሙዚቃ እየሰማን፣ በበርካታ የዳንስ ፓርቲዎችና በባህር ዳርቻ ላይ የሚዘጋጁ የምሽት ጭፈራዎች ላይ እየታደምን ነበር ያሳለፍነው፡፡

በዚያ አንድ ወር ውስጥ ይበልጥ እርስ በርሳችን ተቀራርበን ተቆራኘን፡፡ ነገር ግን ሕይወት በራሷ አቅጣጫ መጓዟ ግድ ነውና በፈረንሳይና በኢትዮጵያ የነበረንን ቆይታ አጠናቀን ተለያየን፡፡ በቀጣዩ ዓመት ወደ አሜሪካ መጥቶ እንደገና ተገናኝተን የፍቅር ቁጠማችንን እናጭድ ጀመር፤ ከጥቂት ወራት በኂላም እኔም ጓዜን ጠቅልዬ ወደ ፈረንሳይ ተጓዝኩ፡፡

ፓሪስ ለመኖር የወሰንሁት በሕይወቴ ልዩ ቦታ የምሰጣቸው ደራሲዎችና የጥበብ ሰዎች በዚያ ስለሚኖሩ ለእኔ ልዩ ቦታ ነበር፡፡ ከጆል ጋራ ለአንድ ዓመት ያህል ተራርቀን ከቆየን በኂላ እንደገና ተገናኝተን ፍቅራችንን እንደ አዲስ አደስን፡፡

ይህን ጊዜ ነበር ስለቤተሰቡ የሚያውቀውን ሁሉ የነገረኝ፡፡ ፍፁም የሆነ ግለኝነት የሌለበት ግልጽና ደግ ነው፡፡ ስለ ራሱ፣ ስለቤተሰቡ ሲተርክልኝ ታሪኩን እንደሚወድና ታሪኩን የሚነገረኝም ለጓደኛው መነገር ስላለበት ብቻ ነበር፡፡ በእውነት ነው የምላችሁ ለእኔ ጆል በዓለም ላይ ምርጡ ተራኪ ነው፡፡

ጆል በዓለም ላይ ረጅም አመትን ያስቆጠረ የነገስታት የዘር ግንድ ውስጥ እንደሚገኝና ከ3ሺ አመት የዘለቀ ከንጉስ ሰለሞን እና ንግስተ ሳባ የሚመዘዝ ሀረግ ያለው፣ የኢትዮጵያ ነገስታት ውስጥ ቅድመ አያቱ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ንጉሰ ነገስት ዘ ኢትዮጵያ ናቸው፡፡ እኚህ ንጉስ ረቂቅ፣ ታላቅ ስብዕና ያላቸው ንጉስ ነበሩ፡፡

በ1966 ዓ.ም “አብዮት” ከስልጣን ተወግደው በግፍ ሲገደሉ፣ በርካታ የንጉሳዊ ቤተሰብ አባላት ለግድያና ለእስር ተዳርገው ነበር፡ ፡ ከአስራ ሰባት አመት በኂላ ኮሚኒስቱ የመንግስቱ ኃይለማርያም መንግስት በትጥቅ ትግልና በአሜሪካ መንግስት ዕርዳታ ከስልጣን ተወገደ፡፡ ኢሕአዴግ መንግስት ሲመሰርት በእስር ላይ የነበሩ የንጉሳዊ ቤተሰቦች ከእስር ቤት ተፈትተው፣ በውጭ አገር በስደት ይኖሩ

**...የጆል እናት የታዋቂው የእምሩ ዘለቀ ልጅ ሲሆኑ ባለቤታቸው ልዑል ዳዊት መኮንን ኃይለስላሴ ከሞቱ በኋላ ልጆቻቸውን የማሳደግና የማስተማር ኃላፊነቱ በእሳቸው ላይ ነበር ወድቆ የነበረው...**

የነበሩትም ወደ አገራቸው እንዲገቡ ተፈቀደ፡፡

የልዑል መኮንንና የልዕልት ሣራ ግዛው አራተኛ ልጅ፣ የዳዊት መኮንን ልጅ ነው ጆል፡፡ የጆል አባት ልዑል ዳዊት መኮንን በሮም ኢጣልያ በስደት እያሉ ነው አብዮቱ የፈነዳው፡፡ ደርግ በተደጋጋሚ ልዑሉ ወደ አገር እንዲመለሱ ሲወተውት የነበረ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ጦር ውስጥ የሻምበልነት ማዕረግ የነበራቸው የጆል አባት ግን ወደ አገራቸው ቢመለሱ ከሚጠብቃቸው እስር እና ግድያ እንደማያመልጡ ስለተረዱ እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ የደርግን መንግስት በማጋለጥና ለመጣል በሚደረጉ ትግሎች ውስጥ ሲሳተፉ ነበር የኖሩት፡፡

የጆል እናት የታዋቂው የእምሩ ዘለቀ ልጅ ሲሆኑ ባለቤታቸው ልዑል ዳዊት መኮንን ኃይለስላሴ ከሞቱ በኂላ ልጆቻቸውን የማሳደግና የማስተማር ኃላፊነቱ በእሳቸው ላይ ነበር ወድቆ የነበረው፡፡

ደርግን የተካው የኢሕአዴግ መንግስት የልዑል መኮንን ንብረት የነበረው ዋቢሸበሌ ሆቴልን ለወራሾቻቸው መልሶላቸው በባለቤትነት እያስተዳደሩት ይገኛሉ፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በርካታ የኢትዮጵያ ንጉሳዊ ቤተሰቦች አካላት ወደአገራቸው ተመልሰው መኖር ጀምረዋል፡፡ በተለይ የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና የፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ አስተዳደር ለበርካታ አመታት በስደት የነበረውን የኢትዮጵያን የዘውድ ምክር ቤት በይፋ ወደ አገር ቤት ገብቶ እንዲንቀሳቀስ ፈቅዶ አዲስ ታሪክ ፅፏል፡፡

ከልዑሉ ፍቅረኛዬ ጋራ ስለቤተሰቡ ታሪክ፣ ስለአገሩ ባህል ታሪክ በሚገባ ያወቅሁት በሁለት ሺህ አስር ዓመተ ምህረት ነው፡ ፡ በ2010 ዓ.ም (በሚሊኒየሙ) የጆል አያት የልዕልት ሳራ ግዛው የልደት በዓል ድንቅ የኪነ ሕንፃ ጥበብ ባረፈበት የጀርመን ንጉሳዊ ቤተሰቦች መኖርያ ካስትል ውስጥ ከቫንግ ዳንስ ቤተሰብ ጋር ባዘጋጁት የአከባበር ስነ ስርዓት ላይ በእንግድነት ተገኘሁ፡፡ ይህ አጋጣሚ ደግሞ ይበልጥ የአውሮፓውያን ንጉሳዊ ቤተሰቦች ከኢትዮጵያ ንጉሳዊ ቤተሰብ ጋራ ያላቸውን ቅርበትና ወዳጅነት እንዳውቅ አደረገኝ፡፡

እኔና ጆል እርስ በርሳችን በጣም እንፋቀራለን፤ ነገር ግን ከ2010 ዓ.ም በኂላ ያሉ ቀጣይ አመታት ሕይወት ወደተለያዩ አቅጣጫዎች በየፊናችን መራችን፡፡ በ2012 ጆል ከሚማርበት የሕግ ትምህርት ቤት ትምህርቱን አቋርጦ በጄኔቭ ሥራ መስራት ጀመረ፡፡

እኔም በሐርቫርድ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርቴን መማር ቀጠልኩ፡፡ ትምህርቴን ካጠናቀኩ በኂላ ፍሬንች ቶማስ የተሰኘ ኩባንያ በማቋቋም የተለያዩ ባህላዊ እንዲሁም አስተማሪ ፕሮጀክቶችን በኒዮርክ ሲቲ እና በዋሽንግተን በማከናወን ላይ እያለሁ ነበር ጆል ወደ ዋሽንግተን በመምጣት በሐርቫርድ ዩንቨርስቲ የሕግ ትምህርቱን ይከታተል የጀመረው፡፡ በመጨረሻም ሁለታችንም የከፍተኛ ትምህርታችንን እንዳጠናቀቅን ለመጋባት ቀለበት አሰርን፡፡

ከወራት በኂላም ተጋባን፤ ሰርጋችን እጅግ ደማቅ ነበር፡፡ የጥንቱና የአሁኑ የአኗኗር ዘይቤ የተቀላቀለበት ጭፈራና ግብዣ የተካሄደበት ነበር፡፡ እኔም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነትን ተቀብዬ ክርስትና ተነሳሁ፡፡ የንጉሳዊ ቤተሰብ አባል በመሆኔ ስለኢዮጵያ ጥንታዊ ገናና ባህል ታሪክ እንዳውቅ አድርጎኛል፡፡ ስለዚህም የእኛ ትኩረት የዚያች ጥንታዊ አገር ነባር ታሪክ፣ ባህል አምባሰደሮች መሆን ነው፡፡

አሁን ከጆል ጋራ በዋሽንግተን ዲሲ በመኖር ላይ ነን፡፡ ጆል በሕግ አማካሪነት በጥብቅና ሥራ ላይ ከመሰማራቱ በተጨማሪ በተለያዩ የምግባረ ሰናይ እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋል፡ ፡

ልዑል ጆል ዳዊት መኮንን ጋዜጠኞች፣ ፊልም ሰሪዎች፣ የባህልና የቅርስ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ ወጣቶችን የሚያግዝ ፋውንዴሽን ላይ ንቁ ተሳታፊ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ዕድገቱ ምን እንደሚመስልና ስለ ስደት ሕይወት አጠቃላይ ታሪክ በመፃፍ የሚገልጽ የሕይወት ታሪኩን የሚገልጽ መጸሐፍ እያዘጋጀ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን ለውጥ በትኩረት ይከታተላል፡፡ የአገሩ ወጣቶች በንግድና በሥራ ፈጠራ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ፕሮጀክት ጥረቶችን ያግዛል፡፡

ከእኔ ከባለቤቱ ጋራ በመሆንም በዓለም ዓቀፍ የአመራር ምክር ቤት ሜሪዲያን ኢንተርናሽናል ሴንተር ውስጥ በአባልነት በመሳተፉ የተረጋጋች፣ ሠላማዊ ብልፅግና የሰፈነባት ዓለምን ለመፍጠር አስፈላጊ የሆነውን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ማዕከሉ አድርጎ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳታፊ ነን፡፡

ከባለቤቴ ከልዑል ጆል ዳዊት ጋር አንድ የአሁኑን እና የትላንቱን ታሪክ እንዲሁም የሕይወት ዑደትን የሚያስቃኝ የቴሌቭዥን ስርጭትም ለመጀመር እየሰራን ነው፡፡ ” ብላለች “town and country” ለተሰኘው ታዋቂ መጽሔት ላይ ለንባብ በበቃው ጽሁፏ ልዕልቲቱ፡፡

# የ"ሚዛን" ድራማ ወላጅ እናት ዛብሽ እስጢፋኖስ

*በተማሪነት (ወጣትነት) ዘመኗ ከኪነጥበብ ይልቅ ለስፖርት በተለይም ለጂምናስቲክ የተለየ ፍቅር የነበራት፣ ተሰጥኦዋንም ባገኟቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ሰዎች እንዲ ያዩላት ጥረት ታደርግ የነበረችው እንግዳችን ዛብሽ እስጢፋኖስ ዛሬ ለእውቅና እና አድናቆት ያበቃት የኪነ ጥበብ ሙያ ውስጥ የገባችው በብዙ ውጣ ውረድና አድካሚ በሆነ ጥረት ውስጥ አልፋ ነው። ኪነ ጥበብ ከዕውቀት ይልቅ በድፍረት በሚዘወርበት ዘመን፣ በዚህ ሙያ ውስጥ ከመሰማራት በፊት ራስን ማብቃት ቀዳሚ እንደሆነ ማመኗ ደግሞ ጉዞዋን ረጅምና አድካሚ አድርጎታል። ከዚያ ሁሉ በመሰናክል የታጠረ ጥረት በኋላ አሁን ላለችበት ዝነኝነት መብቃቷ ግን ለራሷ የሳቀ ደስታን ከመስጠቱ ባሻገር በአድናቂዎቿ ዘንድም በምክንያት የምትወደድ እንድትሆን አስችሏታል።*

*ዛብሽ እስጢፋኖስ ወደፊልም ሙያ ለመግባት ራስን ማብቃት መቅደም አለበት ብላ ስትነሳ መጀመሪያ ያደረገችው ስልጠና መውሰድን (መማርን) ነው። በዚህም ወደ ክቡር ዶ/ር አርቲስት ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) የስልጠና ማዕከል በመግባት መሠረታዊ የሙያ ክህሎት ማሳደጊያ ስልጠና ወሰደች። የፊልም ስክሪፕት አፃፃፍ፣ የዳይሬክቲንግ፣ ቀረፃና ትወና ስልጠናዎችንም ት/ቤት ገብታ ተምራለች። ከምታ ውቀው ታሪክ ተነስታ የፃፈችው "ልዩነት" የተሰኘ አጭር ድርሰቷ በኢቲቪ 2 ከታየላት በኋላ ግን ማንም የሚያቆማት አልነበረም። ከሕዝብ ባገኘችው አድናቆትና ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ ተገፋፍታ፣ ዛሬ አንቱ እያሰኛት ያለውን "ሚዛን" የተሰኘውን ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ለማሳየት በቅታለች። የደራሲና ፕሮዲዩሰር ዛብሽ እስጢፋኖስ የሙያ መንገድ ለብዙ ኢትዮጵያውያን የሚያስተምረው ቁምነገር እንዳለው የተረዳው የግዮን ጋዜጠኛ አለማየሁ ባዘዘው ከዚህች የጥረት ተምሳሌት ጋር ተከታዩን ቆይታ አድርጓል።*

**ግዮን፡- ለመጀመሪያ ጊዜ የድርሰት ችሎታሽን፣ ነገሮችን በጥልቀት የማየት ብቃትሽን ያሳየሽበት "ልዩ ነት" የተሰኘውና በኢቲቪ2 የታየል ሽ ድራማ ነው። ይህን ድርሰት ለ መፃፍ ያነሳሳሰሽ መሰረታዊ ሀሳብና ምክንያት ምን ነበር?**

ዛብሽ፡- መነሻ ያደረግሁት ሀሳብ በየሁላችንም ህይወት ውስጥ ያለው የኑሮ ሁኔታ ነው። የዓለም ተለዋዋጭና ዝብርቅርቅ መልክ የፈጠረላቸው ሁለት ተቃራኒ የህይወት ዕጣ ፈንታዎች ማለትም ድህነትና ባለፀጋነት፣ ምን ዓይነት ተፅዕኖ እንዳላቸው ማሳየት ነው። ማግኘትና ማጣት ከመወለድ ጋር አብረው የሚታደሉ ባይሆኑም፣ የሰው ልጆች ግን በሁለቱ ዕጣ ፈንታዎች ውስጥ ተወስነው የሚኖሩ ናቸው። አንዱ ሀብቱን የት ልጣለው? እስኪል ድረስ በናጠጠ ምቹ ዓለም ውስጥ ሲኖር፣ ሌላው ደግሞ ለዕለት የሚጎርሰው አጥቶ በረሃብ ቸነፈር ድፍት ብሎ ይቀራል። ማግኘትና ማጣት የምንኖርባት ምድር መገለጫ፣ መልኳ ሆኖ የሚገኝ በመሆኑ ይህንን ሀሳብ ይዤ በእነዚህ ተፃራሪ የኑሮ ሁኔዎች ውስጥ ያለውን ጉልህ ልዩነት ኪነጥበባዊ በሆነ መንገድ ለማሳየት የሞከርኩበት ነው።

**ግዮን፡- የተመልካቹ ስሜት ምን ሆነ? ከታየ በኋላስ በአንቺ ላይ የፈጠረው ተነሳሽነት እንዴት ያለ ነበር?**

ዛብሽ፡- በጣም ከፍተኛ የሞራል ስንቅ ነው የሆነኝ። እንደምታውቀው ምንም ነገር ሲጀመር በውስጥህ ጥርጣሬ መፍጠሩ የሚታወቅ ነው። ሰው ይወደው ይሆን?፣ አዲስ ነገር አቅርቤ ይሆን?፣ ተመልካችን ይመጥን ይሆን? እያልክ መጨነቅህ የማይቀር ነው። ይህ ሁሉ ከመጠራጠር የሚመነጭ በጭንቀት የታጀበ ጥያቄን የሚመልስልህ የተመልካቹ አስተያየት በመሆኑ በብዙ መወደዱን መረዳቴ እጅግ ከፍተኛ ሞራል ሰጥቶኛል።



ዛብሽ እስጢፋኖስ

**ግዮን፡- ይህ ሞራል ወደ ትልቁ "ሚዛን" ድራማ እንድትደንደሪ ወይም አስፍተሽ እንድታስቢ ገፍቶሻል ማለት ይቻላል?**

ዛብሽ፡- በትክክል።ምክንያቱም የመጀመሪያ ስራ ቀጥሎ ለሚመጡት ፈጠራዎች ሁሉ ወሳኝነት ያለው ነው። በዚያን ጊዜ ስራዬ ባይወደድ ኖሮ ሚዛን ላይወለድ ምናልባትም የመወለጃ ጊዜው ረጅም ወቅት ሊወስድ ይችል ነበር።

**ግዮን፡- አሁን በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እየታየ ያለውን "ሚዛን" ተከታታይ ድራማ የፃፍሽውና ፕሮዲዩስ ያደረግሽው አንቺ ነሽ። ይሁንና ብዙ ጊዜ በእኛ አገር ተከታታይ ድራማን ከማቅረብ በፊት ፊውቸር ፊልም (በሲኒማ ቤት የሚቀርብ) ነው ሲቀድም የምናስተውለው። አንቺ ፊውቸር ፊልም ሳትሰሪ በቀጥታ ወደ ተከታታይ ድራማ እንዴት አተኮርሽ?**

ዛብሽ፡- ባልከው ነገር እኔም እስማማለሁ። የሚገርምህ ነገር መጀመሪያ ድርሰቱን መፃፍ የጀመርኩት ፊውቸር ፊልም እንዲሆን አስቤ ነበር። ነገር ግን ሀሳቡ በጣም ረዘመ። ብዕሬው ብዕሬው የማያልቅ ሲሆንብኝ ነው ተከታታይ ድራማ እንዲሆን ወደ ማሰብ የተሻገርኩት እንጂ የጀመርኩት ፊውቸር ፊልም ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር።

**ግዮን፡- ገንዘቡስ አላሳሰበሽም? ማለቴ ፊልም ሰርቶ በሲኒማ ቤት ማሳየት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ወጪን በቶሎ ለመመለስ ያግዛል። ተከታታይ ድራማ ግን ገንዘብ የመብላት እንጂ የመመለስ ባህሪው ደካማ ወይም አዝጋሚ ነው።**

ዛብሽ፡- በጣም ነበር ያሳሰበኝ። ግን ደግሞ ምን ላድርግ? ታሪኩን ካሳጠርኩት ሊበላሽብኝና ዋናውን መልዕክት ሊጎዳብኝ ሆነ፣ ስለዚህ ያለኝ አማራጭ ተከታታይ ድራማ አድርጎ መታገል ነው። ይህን መንገድ መምረጤ ደግሞ ትክክል ነበር። ምክንያቱም አሁን በተመልካች ዘንድ ያገኘው ተቀባይነትና አድናቆት ለመንገዴ ትክክለኛነት በቂ ማሳያ ነው።

**ግዮን፡- ሚዛን በምን ሀሳብ ላይ ነው የሚያጠነጥነው? መነሻ የሆነሽ ዋነኛ ምክን ያትስ ምንድነው?**

ዛብሽ፡- ሚዛን ድራማ በዋነኛነት የሚያነሳቸው ሀሳቦች አገራዊ ጉዳዮች ናቸው። የዖታ ጥቃት፣ የማንነት ጥያቄ፣ የስነልቦና፣ የባንዲራ ጉዳይ እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየሰፉ ያሉ ማህበራዊ▶

ችግሮቻችን ናቸው፡፡ ለታሪኩ መነሻ የሆነኝን ሀሳብ ያገኘሁት ደግሞ እህቴን ጥየቃ ወደ ሰሜን ወሎ አጣዬ አከባቢ በሄድኩበት አጋጣሚ ነው፡፡ ከተማው ውስጥ ወደሚገኘውና ደስ የሚል መስህብ ወዳለው ሠው ሠራሽ ሐይቅ ሄጄ ንፁህ አየር እየተቀበልኩ፣ በቦታው ውበትም ተመስጬ ሳለሁ ነበር ልጅቷ ወደ እኔ መጥታ ውሃ የጠየቀችኝ፡፡ አካባቢው ቆላማ የአየር ንብረት ያለው በመሆኑ ልጅቷ በላብ ተዘፍቃ በጣም ደክሟታል፡፡ ሁኔታዋ ስላዛነኝ ነይ ብዬ ዛፍ ጥላ ስር እንድታርፍ አደረግኋና ከየት እንደመጣች ጠየኳት፡፡ የመጣችው ከአዲስ አበባ መሆኗን፣ የያዛቻት ህፃን ከፍቅረኛዋ የተረገዘች መሆኗን ነገር ግን በማርገዟ ከቤት ተባርራ ጎና መውደቋን፣ መድረሻ ስታጣ ወደ እናቷ የትውልድ አገር በመምጣት ዘመዶቿ ጋር ለመጠለል በመንገድ ላይ እንዳለች ስትነግረኝ በጣም አዘንኩ፡፡ ይህቺ ልጅ በዚህ ለጋ ዕድሜዋ የገጠማት ችግር በጣም አንጀት የሚበላ በመሆኑ ለብዙ ቀን ስለእሷ አስብ ነበር፡፡ ችግሩ በእሷ ብቻ የተፈጠረ አለመሆኑን ማሰቤ ደግሞ ወደ ድርሰት እንድቀይረው አነሳስቶኛል፡፡

**ግዮን፡- ተከታታይ ድራማን ለመስራት ብዙ የገንዘብ አቅም ይፈልጋል፡፡ ስራውን ስትጀምሪው ገንዘቡ ነበረሽ?**

ዛብሽ፡- ምንም አልነበረኝም፡፡ እኔ ጋር የነበረው ድርሰቱ እና ፍላጎት የሚገፋው የስራ ሞራል ብቻ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን በቤተቦቼ፣ ጓደኞቼና በባለሙያዎች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ድራማው እውን ሊሆን ችሏል፡፡

**ግዮን፡- ስፖንሰር ማፈላለግ ላይ ትኩረት አላደረግሽም?**

ዛብሽ፡- አድርጌአለሁ፡፡ ነገር ግን ድራማው የተጀመረበት ወቅት በራሱ አዲሱ የለውጥ መንግሥት የመጣበትና የመንግሥት መ/ቤቶች ወጪ እንዲያቆሙ የታዘዙበት ጊዜ በመሆኑ ስፖ`ንሰር ማግኘት ፈተናው የበዛ፣ እንደውም የለም የሚባልበት በመሆኑ ስፖ`ንሰር ማግኘት አልቻልንም፡፡

**ግዮን፡- አሁንስ? ስፖንሰር አላገኘሽም?**

ዛብሽ፡- የለም! የያኔው መመሪያ አሁንም አልተለወጠም፡፡ ድራማው የሚተላለፈው የመንግስት ተቋም በሆነው ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ቢሆንም መ/ቤቶች ስፖ`ንሰር ሲጠየቁ አይተባበሩም፡፡ “ተከልክለናል!” የሚል መልስ ብቻ ነው የሚሰጡት፡፡ ይሄ ነገር መቅረት አለበት፡፡ መመሪያው መነሳት አለበት፡፡ ለአገርና ለዜጎች የላቀ ፋይዳ ያላቸው የኪነ ጥበብ ስራዎችን መደገፍ የመንግስት ግዴታና ሃላፊነት በመሆኑ ክልከላው መነሳት አለበት፡፡ በጀት ያላቸው መ/ቤቶች ሊደግፉን ስለሚገባ አሰራሩ መሻሻል ይኖርበታል፡፡

**ግዮን፡- የድራማችሁ አብዛኛው መቼት** በአማራ ክልል በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ነው፡፡ የክልሉን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ድጋፍ አልጠየቃችሁም?

ዛብሽ፡- ጠይቀናል! በተደጋጋሚ ጠይቀናል፤ ግን አዎንታዊ ምላሽ የለም፡፡ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሊሰራው የሚገባውን ስራ እየሰራን መሆኑ በግልፅ የሚታይ ቢሆንም፣ የራሱን ስራ እየሰራንለት ሊደግፈን እንኳ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ኢቢሲ እንደራሱ ስራ ከልብ እየደገፈን ባይሆን ኖሮ እስካሁን መቀጠላችን ከባድ ነበር፡፡ ለዚህ የበቃነው በኢቢሲ ድጋፍ ነው፡፡

**ግዮን፡- በቅርቡ በቤስት ዌስተርን ፕላስ አዲስ ሆቴል አንድ ክብረ በዓል አዘጋጅታችሁ ነበር፡፡ ምንን በማስመልከት ነው?**

ዛብሽ፡- ድራማችን መታየት የጀመረበት አንደኛ ዓመት የልደት በዓልና ምዕራፍ ሶስትን አጠናቀን ወደ ምዕራፍ አራት የተሸጋገርንበት የስኬት ምዕራፍ በአንድ ላይ የተዘከሩበት ፕሮግራም ነበር፡፡ ከተዋንያኑ፣ ከደጋፊዎቻችን፣ ከፕሮዳክሽን ባለሙያዎቹና ከአድናቂዎቻችን ጋር ሆነን ኬክ ቆርሰን፣ ስኬታችንን በጋራ ያከበርንበት ፕሮግራም በመሆኑ በጣም የተደሰትንበት ነው፡፡

**ግዮን፡- የጥበብ አባትሽ ክቡር ዶክተር አርቲስት ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) የክብር እንግዳሽ ነበሩ፡፡ እስቲ ከእሳቸው ጋር ስላለሽ ግንኙነት ንገሪን?**

ዛብሽ፡- እንዳልከው ክቡር ዶ/ር አርቲስት ተስፋዬ አበበ የኪነ ጥበብ ሙያ አባቴ ናቸው፡፡ ስለ ድርሰት እና የፊልም አሰራር ምንም በማላውቅበት፣ ከፍላጎት የዘለለ ምን ማድረግ እንዳለብኝ በውል ባልተረዳሁበት ጊዜ ወደ ማዕከላቸው አስገብተው ለዛሬው የሙያ መንገዴ ወሳኝ የሆኑን ዕውቀቶች የሰጡኝ ጋሽ ተስፋዬ ናቸው፡፡ አሁን ያለችው ዛብሽ የእሳቸው ስሪት እንደሆነች ነው የማምነው፡፡

**ግዮን፡- ከጋሽ ተስፋዬ በኋላ የሲኒማ ጥበብን ተምረሻል አይደል?**

ዛብሽ፡- አዎ! በተለይ የስክሪፕት አፃፃፍ፣ የዳይሬክቲንግ፣ የሲኒማቶግራፊና የትወና ክህሎቴን ይበልጥ ለማዳበር ት/ቤት ገብቼ ተምሬአለሁ፡፡

**ግዮን፡- ሚዛን ድራማ በተለያየ ጊዜ የዳይሬክተር ለውጥ አድርጓል፡፡ ለምንድን ነው?**

ዛብሽ፡- ቀደም ሲል እንደነገርኩህ ባለሙያዎች አብረውኝ ለመስራት የፈቀዱጽ በክፍያ ሳይሆን እኔን ለማገዝና ስራውን እውን ለማድረግ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ የድራማው ክፍሎች ዳይሬክተር የነበረው ሄኖክ አየለ፣ የራሱን ስራ አቁሞ ነው መስመር ለማስያዝ ሲያግዘኝ የነበረው፡፡ ተዋንያኑን ከመምረጥ ጀምሮ ድራማው መልክ እና አቅጣጫ እንዲይዝ ያደረገው ሄኖክ ነው፡፡ ሲጀምረውም መልክ ሊያሲዝልኝ እንጂ አብሮኝ ለመዝለቅ እንደማችል አውቅ ነበር፡፡ የራሱን ስራ አቁሞ ስለነበር እኔም ከዚያ በላይ እንዲዘልቅ አልጠብቅም ነበር፡፡ ያቆመው ማቆም ስላለበት ቢሆንም ያደረገልን ነገር በገንዘብ ሊመለስ የሚችል ባለመሆኑ ሁሌም አመሰግነዋለሁ፡፡

ከእሱ በኋላ ስራውን የተረከበው የሲኒማ ጥበብን በት/ቤት ያስተማረኝ መምህሬ ናኦድ ለማ ነው፡፡ እሱም ያለውን የተጣበበ ጊዜ ተጠቅሞ ሊያግዘን እንጂ ስራውን በዘላቂነት ለመስራት የሚመቸው አልነበረም፡፡ መምህሬ ናኦድ ለማ አሁንም በሀሳብና በገንዘብ ጭምር ከባለቤቱ ጋር እያገዙኝ ነው፡፡ አሁን ድራማውን ዳይሬክት እያደረገው ያለው ዘላለም ይታገሱ ነው፡፡ እሱም በማገዝ መንፈስ እንጂ በክፍያ አይደለም እየሰራልን ያለው፡፡ ዳይሬክተር የተለዋወጠበት ምክንያት በዚህ የተነሳ ነው፡፡

**ግዮን፡- ሚዛን ተከታታይ ድራማ በተዋንያን መረጣ በኩል የተሻለ እንደሆነ ሲነገር ሰምቻለሁ፡፡ እስቲ እነማን እንዳሉበት ንገሪን?**

ዛብሽ፡- ከአንጋፋዎቹ እነ ፍቅርተ ደሳለኝ፣ ወለላ አሰፋ፣ ገነት ንጋቱና ሞገሴ ይጠቀሳሉ፡፡ ከወጣቶቹ ደግሞ ሞዴልና አክተር ሳሙኤል ተስፋዬ፣ ቅድስት ጌታቸውን፣ መቅደስ አለባቸው፣አቤል ጥላሁንን የመሳሰሉ ጎበዝ ልጆች አሉበት፡፡

**ግዮን፡- በመጨረሻም የምታስተላልፊው መልዕክት ካለ ዕድሉን እንስጥሽ?**

ዛብሽ፡- በቅድሚያ የሁሉ ነገር ባለቤት የሆነውን ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠል ሚዛን ድራማን እንደራሱ ንብረት ቆጥሮ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የሚያደርግልንን ኢቢሲን እና የስራ ሀላፊዎቹን፤ በተለይም የኮሚሽኒንግ ዲፓርትመንት ክፍልን እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ የኢቢሲ ድጋፍ ባይኖረን ኖሮ አንድ ዕርምጃም መራመድ አንችልም ነበር፡፡ በዚህ ተቋሙንና መላ ሠራተኞቹን ደጋግሜ አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ ውጪ የሚያግዙን ብዙ ስለሆኑ ሁሉንም መዘርዘር ስለማይቻል፣ ከተዋንያኑ ጀምሮ የፕሮዳክሽን ባለሙያዎቼን ቤተሰቦቼንና ከጎኔ ሆነው ያገዙኝን በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ገና ጀማሪ ብሆንም ስራሽ አመርቂ ነው ብላችሁ ከሕዝብ ጋር ይበልጥ እንድተዋወቅ ዕድል የሰጣችሁኝ የግዮን አዘጋጆችንም አመሰግናለሁ፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

> ...መጀመሪያ ድርሰቱን መፃፍ የጀመርኩት ፊውቸር ፊልም እንዲሆን አስቤ ነበር ነገር ግን ሀሳቡ በጣም ረዘመ ብፅፈው ብፅፈው የማያልቅ ሲሆንብኝ ነው ተከታታይ ድራማ እንዲሆን ወደ ማሰብ የተሻገርኩት እንጂ የጀመርኩት ፊውቸር ፊልም ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር...

## “በኢሕአዴግ . . . *ከገጽ 4 የዞረ*

እያስቸገረን ነበር፡፡ በሁለት መንገድ ነው ተቸግረን የቆየነው፡፡ ግን የሽብር ህጉ ያሉትን ችግሮች ይፈታል ወይ? በነበረው መደበኛ ሕግስ መንግስት ይሄንን ጉዳይ ማስተናገድ አይችልም ወይ? ምን አዲስ ነገር ያመጣል? የሚለውን በተመለከተ አነጋግረናቸዋል፡፡

የዓለም ፕራክቲስን ብንመለከት እነ አሜሪካ፣ እንግሊዝን የመሳሰሉ ትላልቅ አገሮች በዛ አቅጣጫ የሚጓዝ የሽብር ሕግ አላቸው፤ የቸገረን እዛ ላይ ነው፡፡ ሌላው ዓለም እየሰራበት ለእኛ አገር አያስፈልግም ብለን ብንከራከር፣ ዝም ብለን ተቃዋሚ ስለሆንን “በዛ ደረጃ ተከራከሩ” ወደሚለው እንዳንሄድ፡፡ ብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ጉዳይ ቁስል ስላለበት ያንን እንደገና ማምጣቱ ላይጠቅም ይችላል በሚል፡፡

የኢትዮጵያ ደህንነትና መከላከያ ሰራዊቱ፣ ፍ/ቤቱ ሁሉም የሕግ አስፈፃሚ አካል የተዋቀረበት መንገድ ችግር አለው፡፡ ከዚህ ችግር ሳይወጣ በጥንቃቄ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ግን ሽብርተኝነትን በተመለከተ እንደ ድርጅት ሀሳባችንን አቅርበናል፡፡ በሽብርተኝነት ዙሪያ ከዓለም ተሞክሮ ውጪ መሆን ያስቸገራል፤ የኢትዮጵያ መንግስት ፀባይ ደግሞ እንደሚታወቀው በቀላሉ ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ነገር የሚጠቀመው ተቃዋሚ ላይ ስለሆነ ስጋታችንን ገልፀናል፡፡

**ግዮን፡- የሲዳማ ሕዝብ የክልል ጥያቄነትንስ እንዴት ይመለከቱታል? “ጥያቄያችን ምላሽ ካላገኘ ሐምሌ 11 በራሳችን መንገድ እንወስናለን “ የሚልም እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

ፕ/ር መረራ፡- እዚህ ላይ ሁለት ነገር ነው ያለው፡፡ ይሄንን እንቀስቃሴ በበላይነት የሚመራው የሲዳማ ዞን የሚባለው ራሱ የኢህአዴግ ክፍል ነው፡፡ መንግስት ሆኖ አገሪቷን እያስተዳደረ ያለው የኢህአዴግ አንድ ክፍል ካለው ሁኔታ በፈነገጠ ወይም በተለየ መንገድ የራሴን መብት አስከብራለሁ ብሎ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡

ትልቁ ችግር እዛ አካባቢ ላለፉት ብዙ ዓመታት ይሄ ጥያቄ ይጠየቅ ነበር፡፡ ኢህአዴግ ያንን መፍታት ነበረበት፡፡ አቆይቶ በዚህ ደረጃ ፍጥጫውም ግርግሩም እንዲመጣ ያደደረገው የኢህአዴግ መንግስት ነው፡፡ መንግሥት እንደ መንግስት ተደራድሮም ቢሆን የሆነ ነገር ላይ መድረስ አለበት የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ አላስፈላጊ በሆነ መንገድ ወደ እልቂት እንዳይሄድ መንግስትም በቂ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፤ የሲዳማ ወንድሞቻችንም ሁኔታው ከቁጥጥር ውጪ ወጥቶ የሰዎች ሕይወትን የሚያጠፋ ነገር እንዳይከሰት የሚችሉትን ያህል መታገስ አለባቸው፡፡

እኔ እንኳን ሳውቅ ይሄ ጉዳይ አስራ ምናምን ዓመቱ ነው፤ ነገሩ እዚህ ደረጃ ከደረሰ በኋላ የኃይል ዕርምጃ እወስዳለሁ ማለቱ ብዙ ላይጠቅም ይችላል፡፡ መነጋገሩ ጥሩ ነው፡፡ የአካባቢውን ስሜት ከሚያውቁ የአገር ሽማግሌዎች ወጣቶችና አመራሮች ጋር መንግስት መነጋገርና መደራደር ያለበት ይመስለኛል፡፡ ጥፋቱ ለእኔ የመንግስት ነው፤ የመንግስት ብቻ ሳይሆን የኢህአዴግ ነው፡፡ ብዙ ዓመታት ሲጓተት፣ ሲጎተት ቆይቶ እዚህ የደረሰው በራሱ በኢህአዴግ ጥፋት ነው፡፡ ድሮውኑ መቋጨትና መፍታት ይቻል ነበር፡፡

**ግዮን፡- በቤንሻንጉል ክልል ደግሞ ግጭቶች መከሰታቸውንስ እንዴት ተመለከቱት?**

ፕ/ር መረራ፡- በአጠቃላይ አገሪቷ ውስጥ ባለው ሁኔታ ፖለቲካችንን ወደ ብሔራዊ መግባባት አልወሰድንም ብያለሁ፡፡ ሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ወደ መፍጠሩ፤ ወደ መገንባቱ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ደረጃ ወደ ብሔራዊ መግባባቱ መድረሱ ገና ብዙ ይቀረዋል፡፡ ፖለቲካው ገና አልተስተካከለም፤ ችግሩ እሱ ነው፡፡ በዚህ ስታስር በዛ ይፈታል፡፡ በዛ ስታስር በዚህ ያፈሳል፡፡

እነዚህን ነገሮች አስተካክለን ፖለቲካችን እንደ ሀገር አቅጣጫ አላሲያዝነንም፡፡ እዛም እዚም ጫፎች ይዞ ሁሉም እንደ አቅሙ የሚችለውን የፖለቲካ አየሩን እየመረዘ ነው፡፡ ቤኒሻንጉል ብቻ አይደለም ግጭት የተከሰተው፤ ሁሉም አካባቢ እሳት አለ፡፡ እንዲህ ዓይነት ግጭቶች ደግሞ በማይቀሰቀሱበት ሁኔታ ከችግሩ መውጣት የምትችለው አዲስ ስርዓት እንዴት እንገነባለን? ምን ማድረግ እንችላለን? ብለው ኃላፊነት ሊኖራቸው የሚችሉ የፖለቲካ ኃይሎች መደራደርም፣ መነጋርም ሲችሉ ነው፡፡

አሁን እኮ ትልቁ ችግር ኢህአዴግም ከራሱ ሳጥን አለመውጣቱ ነው? ከራሱ አጥር ወጥቶ በሚሆን መንገድ ከሌሎች ኃይሎች ጋር እየሰራ አይደለም፡፡ ብቻውን ደግሞ ችግሮችን መፍታት አልቻለም፡፡ ከአንዱ አንዱን መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ እስካልሆነ ድረስ ግጭቶች ይቀጥላሉ፡፡

**ግዮን፡- መንግስት 2012 ምርጫ ከወዲሁ እየተዘጋጀ ነው፤ ምርጫ ቦርድም የተለያዩ ሕጎችና አሰራሮችን እያሻሻለ ይገኛል፡፡ በትክክል ቀጣዩ ምርጫ በተያዘለት ጊዜ መካሄድ አለበት ብለው ያምናሉ?**

**...በአጠቃላይ አገሪቷ ውስጥ ባለው ሁኔታ ፖለቲካችንን ወደ ብሔራዊ መግባባት አልወሰድንም ብያለሁ ሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ወደ መፍጠሩ፤ ወደ መገንባቱ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ደረጃ ወደ ብሔራዊ መግባባቱ መድረሱ ገና ብዙ ይቀረዋል...**

ፕ/ር መረራ፡- እኛ ያለን አቋም ምርጫው በሰዓቱ መከናውን አለበት የሚል ነው፡፡ ከዚህ የተሻለ ጊዜ አለ፤ ከዚህ የተሻለ መረጋጋት ይመጣል የሚሉት ነገሮች አልተፈቱም፡፡ ስለዚህ በሕጉ መሰረት ምርጫውን ማካሄዱ ጥሩ ነው፡፡ እንደምታውቀው እስካሁን ድረስ የቀበሌና የወረዳ ምርጫዎች መካሄድ ከነበረባቸው ሁለተኛ ዓመታቸውን ይዘዋል፡፡ ሕዝብም ባልመረጣቸው ሰዎች እየተገዛ ነው፡፡ ካድሬና ሕዝቡ ደግሞ አብረው መሄድ አቅቶት እንደምናየው በየቦታው እየተጋጨ ነው፡፡

እስካሁን ያለው ራሱ በአላስፈላጊ መንገድ እየበጠበበጠን ነው፤ ከዚህ በኋላ ሊጎዳ በሚችል ሁኔታ አንድና ሁለት ዓመት ይራዘም የሚል ነገር ከመጣ ህዝቡ ተስፋ ቆርጦ ወደ ሌላ ነገር እንዳይሄድ በጣም ስጋት አለን፡፡ ስለዚህ በኛ በኩል ምንም ይሁን ምን ምርጫው መካሄድ አለበት፡፡ ምርጫ የሚለው ነገር ራሱ የሕዝብን ቀልብ ሊስብ ስለሚችል፣ መልስ ከመስጠት ባሻገር አቅጣጫ ሊያሲዝ ስሚችል መካሄድ ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ 2007 ዓ.ም ላይ ምርጫ ሲካሄድ እኔ እስከማውቀው ድረስ ኦሮሚያ ላይ ድንጋይ ሳይወረወር ነው ያለፈው፤ ሕዝቡ በምርጫው ተስፋ ጥሎ፣ ብዙ ነገር ጠብቆ ስለነበር፡፡

ወደ እዛ መሄዱ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ይልቁኑ ምርጫውን በሰዓቱ ለማከናወን ሊሰሩ የሚገባቸውን ነገሮች በፍጥነት መስራቱ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ባለው ጊዜ የምርጫ መዋቅሩን እስከ ታች ድረስ መዘርጋት፣ መሰራት ያለባቸው ነገሮች በሙሉ በፍጥነት መከናወናቸው ተገቢና ጠቃሚ ነው፡፡ ግን “አልተሰሩም፣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርጫ ማካሄድ አይቻልም” የሚለው ተረት አላስፈላጊ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል የሚል ስጋት አለኝ፡፡

**ግዮን፡- ሰሞኑን በአማራ ክልል የደረሰውን “መፈንቅለ መንግስት” እንደ ፖለቲከኛ እንዴት አዩት?**

ፕ/ር መረራ፡- እሱ ከላይ ከገለፅኩት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በኢህአዴግ ውስጥ በዚህ ለውጥ ላይ ተመሳሳይ አቅጣጫ ተመሳሳይ ፍላጎት በመሀሉ ያለ አይመስልም፡፡ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረው ውጥረት በዛ መንገድ የፈነዳ ይመስላል፡፡ አሁንም ቢሆን የቤ ስራው ኢህአዴግ ጋር ነው ያለው፡፡ ኳሱ በኢህአዴግ ሜዳ ነው፡፡

የኢህአዴግ ድርጅቶች በድሯቸው መንገድ መተግባር አልቻሉም፡፡ ድሮ ከላይ ወደ ታች የሚተላለፈው ትዕዛዝ እስከ ታች ድረስ ሁሉም ተቀብሎ ስራ ላይ ያውለዋል፤ ይተገብራል፡፡ አንዱ ጌታ፣ አንዱ አሽከር ተባብለው ነበር የኖሩት፡፡ አሁን ደግሞ ጌታና አሽከርነት ይቀራል ሲባል ችግር ውስጥ የገቡ ይመስላሉ፡፡

ስለዚህ በባህርዳር የተከሰተው ችግር ዋና የቤት ስራ የኢህአዴግ ነው፡፡ እኛ የምናውቃቸውም፣ የማናውቃቸውም ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ይሄንንም በሚሆን መንገድ ለሕዝብ መንገሩ ጥሩ ነው፤ ግን ዋናው ችግር ኢህአዴግ ራሱ ሲያንከባልለው የኖረው ቦንብ ሲፈነዳ የተከሰተ ይመስለኛል፡፡

**ግዮን፡- እናስመሰግናለን፡፡**

# “በሕዝብና . . .

ከገጽ 4 የዞረ

አካሄድ እንዲከሰት የመቀስቀስ አዝማሚያ ነበረው። የቤኒሻንጉሉን ትንሽ ለየት ሊያደርገው የሚችለው ነገር መተከል አካባቢ ከአማራ ክልል ተቆርሶ የተወሰደ እንደሆነና፣ ሂደቱ የአማራ መገደል ብቻ ሳይሆን ከአማራ ተቆርሶ በተወሰደ መሬት ላይ በሕገመንግስቱ አማካይነት የአማራን ሕዝብ ሉዓላዊነትን ሊጋፋ ወደሚችል አዝማሚያ መሄዱ ነው፡ ፡ ይሄ አካሄድ አክራሪነቱን እየወለደ አሁን የተፈጠረው ዓይነት ኃይል እንዲፈጠር ነበር በዛ አካባቢ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ እንቅስቃሴ ሲካሄድ የቆየው።

**ግዮን፡- የሲዳማ ሕዝብ የክልልነት ጥያቄና ሐምሌ 11 እንወስደዋለን ያሉትን አቋምና ዕርምጃስ እንዴት አገኘኸው?**

ስዩም፡- በመጀመሪያ ደረጃ የክልልነት ጥያቄ በሕገ - መንግስቱ የተፈቀደ ነው። ስለዚህ የብሔረሰቡ ም/ቤት ጥያቄ ያቀርባል፣ ያ ደግሞ ለክልሉ ም/ቤት፣ የክልሉ ም/ቤት ለምርጫ ቦርድ አሳውቆ፤ ምርጫ ቦርድ ደግሞ በጉዳዩ ላይ ሕዝበ ውሳኔ ያካሂዳል። ነገር ግን በዚህ ሕዝበ ውሳኔ እነማን ናቸው ተሳታፊ? የሚሉት በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም። ሕዝበ ውሳኔው እንዴት ይካሄዳል? የሚለውንም ግልፅ አይደለም።

የሲዳማ ሕዝብ ጥያቄ ሕገ-መንግስታዊ መብታቸውን የጠበቀ ነው። ነገር ግን ሲዳማ ክልል የክልልነት ጥያቄ ሲጠይቁ አንደኛ በክልሉ የሚኖሩ የሌላ ብሔር ተወላጆችን መብት በሚገድብና በሚገፍ፣ ሰላምና ደህንነታቸውን በሚነሳ መልኩ መሆን መቻል የለበትም። ሁለተኛ በሲዳማ ብቻ ሳይሆን በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በፌደራል መንግስት በጀትና ድጎማ፣ በፌደራል መንግስት ኢንቨስትመንት፣ እንዲሁም በሌሎች የደቡብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦች በጀት ድጋፍ፣ ሐብት፣ ንብረት፣ ጥሪት የለማቸው ሀዋሳን የመቀራመት አዝማሚያ ያለው መሆን የለበትም። አሁን ያለው ስሜት ያን ይመስላል፡ ፡ይሄ ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው።

ከዛ በተጨማሪ አብዛኛው የአዋሳ ከተማ ነዋሪ የሌላ ብሔር ተወላጅ ነው፣ የሲዳማ ተወላጅ አይደለም። ይህ በራሱ በሕልውናውና ቀጣይ ዕጣ ፈንታው በሚደረገው ውሳኔ ላይ የመወሰን መብት የለውም። በሕገ መንግስቱ መሰረተ ሪፈረንደም ለማድረግ ስልጣን ያለው የብሔረሰቡ ተወላጅ ነው። ሌላው የሲዳማ ተወላጆች የክልሉን ስልጣን በበላይነት እንደያዙ እሙን ነው። እሱ ብቻ ሳይሆን የሃዋሳንም አስተዳደር ጠቅልለው በእጃቸው ያስገቡት እነሱ ናቸው። ወላይታ፣ ሐድያ፣ ጌድኦ የክልልነት ጥያቄ አቅርበዋል። በዞን ደረጃ የቀረበው የክልልነት ጥያቄ ለክልሉ ም/ቤት እስካቀረቡ ድረስ፤ የደቡብ ክልል ም/ቤት ልክ ለሲዳማ እንደደረገው ሁሉ የእነሱንም ጥያቄ ተቀብሎ ወደ ምርጫ ቦርድ መላክ መቻል አለበት። ያንን አላደረጉም። አስር የሚሆኑ ዞኖች ናቸው፣ ክልል እንሁን ያሉት።

የሲዳማ የበላይነትና አፋኝነት በክልሉ ውስጥ እንዳለ የሚያሳየው ይሄ ነው። የራሱን ጥያቄ ወደ ፌደራል ልኮ ሕዝበ ውሳኔ እንዲካሄድ እየጠየቀ፣ የሌሎቹ ጥያቄ ግን እዛው ክልሉ ላይ ታፍኖ እንዲቀር ተደርጓል። ከሲዳማ አባላትና አመራሮች የተለየ ሀሳብና አቋም ያላቸውን የሌላ ብሔር ተወላጆች የክልሉ ም/ቤት ስብሰባ ውስጥ ገብቶ እስከመደብደብና ስብሰባ እስከ ማቋረጥ ደርሰዋል።

በመሰረቱ የሲዳማ ሕዘብ ጥያቄና የሲዳማ ሕዝብ ራስን በራስ የማስተዳደር ስልጣን በየትኛውም ብሔር ተወላጅ ስጋት መሆን የለበትም፡ ፡ አሁን እየሆነ ያለው ግን ያ አይደለም፡ ፡ በተለይ ለአዋሳ ከተማ ነዋሪዎች የመኖር ሕልውናቸው ላይ የተጋረጠ ትልቅ አደጋ ነው፡ ፡ ከዛም አልፈው በቀጣይ ሳምንት በራሳችን ውሳኔ ክልል የመሆን ውሳኔ እናሳልፋለን እስከማለት ደርሰዋል። ይሄ ሕጋዊ ተቀባይነት የለውም። በጥያቄያቸው መሠረት ሕዝበ ውሳኔ የማይካሄድ ከሆነ ጉዳዩን አስመልክቶ ለፌዴሬሽን ም/ቤት አቤቱታ የማቅረብ ስልጣን ብቻ ነው ያላቸው። የፌደሬሽን ም/ቤት ደግሞ በሁለት ዓመታት ውስጥ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ እንደሚሰጥ በሕግ ተደንግጓል። በዚህ መንገድ ለሲዳማ ብቻ ሳይሆኖ ጥያቄ ላቀረቡት አስር ዞኖችም አንድ ላይ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡ ፤ ዛሬ ሲዳማን መልሶ ነገ ሌሎቹን ማየት·ተገቢ አይደለም።

**ግዮን፡- የፀረ ሽብር ሕጉ እየተሻሻለ ተብሎ በሚነገርበት በዚህ ወቅት በርካታ ሰዎች በሽብርተኝነት ተይዘውና ተከሰው ሕጉም የሚተገበርበት ሁኔታ ተፈጥሯል።**

ስዩም፡- በነገራችን ላይ የፀረ ሽብር ሕጉ እየተሻሻለ ነው። ይሄን በማሻሻል ሂደት ውስጥ እኔም በግሌ አስተያየቴን እንድሰጥ ተጠይቄ ቀርቤ ሀሳቤን ሰጥቻለሁ። ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት እንደ ጥሩ ጅምር የሚታይ ነገር ነው። የፀረ ሽብር ሕጉ ፀረ ሽብር ሳይሆን በራሱ አሸባሪ የሆነ ሕግ ነው። በዜጎች ላይ ሽብርና አፈና ለመፈፀም ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡ ፡ ይሄ ህግ መሻሻሉ ምንም ጥያቄ የለውም።

ይሄ ጅምር ባለበት ሁኔታ ያ አሸባሪ ሕግ ተመልሶ ተግባራዊ ሆኖ፣ ያ አስቀያሚ የአፈና ጊዜ አለፈ ባልን በዓመቱ ተመልሶ ያው ሕግ ስራ ላይ መሆኑ፤ እጅግ በጣም አሳዛኝ፣ አሳፋሪና እንደ ክሽፈት የሚታይ ነገር ነው፡

**...ለ27 ዓመት በስርዓት በተቋማት ደረጃ ሲሰራ የነበረ ዘረኝነትና ጥላቻ፣ እንዲሁም በሌላ ክልል የሚኖር የአማራ ሕዝብ አንገቱን ደፍቶ፣ መብቱን እንዳይጠይቅ ሲደረግና እንደስደተኛ ሲቆጠር የነበረበት ሁኔታ ነበር፡፡**

: ለውጡን ወደ ኋላ የመቀልበስ ያህል። ይሄ ለውጥ እንዲመጣ መከራና ስቃይ ላየነው፣ ይሄ የፀረ ሽብር አዋጅ እንዲሰረዝ ስንሟገት ለነበርነው ውርደትና ሞት ነው። በጣም እጅግ በጣም አሳፋሪ ነው።

**ግዮን፡- ምርጫ 2012 በተያዘለት ጊዜ ይካሄዳል እየተባለ ነው፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባልተረጋጋበት ሁኔታ ምርጫው መከናወኑ አግባብ ነው ብለህ ታምናለህ?**

ስዩም፡- በመጀመሪያ ደረጃ ምርጫው በቀጣዩ ዓመት ሊካሄድ ይገባል የሚባልበት መሰረታዊ ምክንያት፤ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ እንደሚካሄድ በሕገ መንግስቱ ስለተደነገገ ነው። በነገራችን ላይ ምርጫ ይካሄዳል ብቻ ሳይሆን የሚለው “ነፃና ገለልተኛ ምርጫ ይከናወናል ነው” የሚለው። ባለፉት ዓመታት የተካሄዱት አምስት ምርጫዎች ከዚህ በፊት ሊካሄድ የነበረውን ምርጫ ለማስቀጠል እንጂ አንዳቸውም ገለልተኛ ምርጫ አልነበሩም። ይሄ ማለት ደግሞ ሕገ መንግስቱ አልተከበረም ማለት ነው። ነፃና ገለልተኛ ምርጫ ተካሂዶ አያውቅም።

ስለዚህ ጊዜውን ጠብቀህ ከዚህ በፊት ሲካሄድ እንደነበረው ዓይነት ምርጫ ለማካሄድ ካልሆነ በስተቀር በቀጣይ ዓመት ልክ ከዚህ በፊት ነፃና ገለልተኛ ምርጫ ሲካሄድ እንደነበረው ታሳቢ ተደርጎ “በቀጣይ ዓመት ምርጫ ካልተደረገ ሞት ሽረት ነው” የሚለው አመለካከት በራሱ ስህተት ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት የነፃ ምርጫ ልምድ የለንምና።

እስከዛሬ ምርጫ ሲያጭበረብርና እስከ ዛሬ የዜጎችን መብት ሲሰርቅ የነበረ፤ ያንን ለመድገም የሚፈልግ አካል ነው “ምርጫ ካልተደረገ ሞቼ እገኛለሁ፣ አገር ትፈርሳለች” የሚለው። እንዲሁም በተመሳሳይ መንገድ አሁን ባለው ግርግር፣ አሁን ባለው የብሔርተኝነት የፖለቲካ ክረት የፖለቲካ ፓርቲዎች አማራጭ ሀሳብና ፕሮግራም ማራመድ በማይችሉበት ሁኔታ፣ ዜጎች ምርጫ እንዲያካሂዱ መወትወትና መጣደፍ በራሱ በብቸኝነት ስልጣን መያዝ እንደሚፈልጉት እንደ ሕወሓት ዓይነት አክራሪ ብሔርተኞች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው።

ነፃና ገለልተኛ ምርጫ እንዲኖር ከተፈለገ በመጀመሪያ ጠንካራ የመዋቅር አሰራር መዘርጋት አለበት። አስፈላጊው የሰው ኃይል መገንባት አለበት። አማራጭ በሌለበት ምርጫ አይካሄድም። የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች በሁሉም የአገሪቱ አካባቢ ሄደው ሀሳብና ፕሮግራማቸውን በነፃነት መግለፅና ማስተዋወቅ ካልቻሉ ሕዝቡ አማራጭ የለውም። “በእኔ ክልል እንዳትመጣብኝ፣ እንዳትደርስብኝ” እየተባለና ሕዝብ አማራጭ በሌለው ሁኔታ ምርጫ እንዴት ይካሄዳል። ልክ ከዚህ በፊት ገለልተኛ ምርጫ ስናካሄድ እንደኖርን ሁሉ በአምስት አመታችን ምርጫ ይካሂድ ማለት አንችልም። በዚህ ምርጫ እናካሂድ እያሉ የሚጣደፉት አክራሪ ብሔርተኞች ሕወሓት፣ ኦነግና አብንን የመሰሉ ድርጅቶች ናቸው፡ ፡ እነዚህ የተሻለ አማራጭ ያላቸው፣ በሀሳብ የሚያሸንፉ ሳይሆኑ በአቋራጭ፣ በድብቅና በግርግር፣ በማጭበርበር ስልጣን ለመያዝ ስለሚሮጡ ነው።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**

# “እስከ ዛሬ ለማንም ያላወጋኋቸው የቴዲ አፍሮ እውነቶች”



በአለምፀሐይ ወዳጆ

በአድናቂዎቹ “የኢትዮጵያ ሙዚቃ አልጋ ወራሽ” የሚል የክብር ስም የተቸረው ወጣቱ የሙዚቃ ፈርጥ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ አትላንታ ከተማ ልዩ የክብር ሽልማት ተበርክቶለታል፡፡ ከእርሱ ጋር በተለያየ የሙያ መስክ ለአገራቸውና ዜጋቸው ጠቃሚ ስራ ለሰሩ ባለሙያዎችም ሽልማት የተበረከተ ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ ደራሲና ገጣሚ በዕውቀቱ ስዩም፣ የዘሐበሻ ሚዲያ መስራችና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ሔኖክ አለማየሁና ሁለገቧ አርቲስት ዓለምጸሀይ ወዳጆ ይገኙበታል፡፡ በዕለቱ የሽልማት ፕሮግራም ከሁሉ ጎልቶ የታየው አርቲስት ዓለምጸሀይ ወዳጆ ስለብላቴናው ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ የሰጠችው ህያው ምስክርነት ነበር፡፡ ተወዳጇና አንጋፋዋ የጥበብ ሰው አለምጸሐይ ወዳጆ “እስከ ዛሬ ለማንም ያላወጋኂዋቸው የቴዲ አፍሮ እውነቶች ናቸው” ብላ የሰጠችው ምስክርነት የሚያስተላልፈው ብርቱ ቁምነገር እንዳለው በማመናችን እኛም እንደሚከተለው አቅርበንላችኂል፡፡

“…ቴዲ አፍሮ ከመወለዱ በፊት እናት እና አባቱን ነው የማውቀው፡፡ ከዛ በኂላ ቴዲን ያየሁት አሜሪካን አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገባ፣ “አለምፀሐይ ቤት ውሰዱኝ” ይልና ለኔ ማንም ሳይነግረኝ ዲጄ መንጌ “ቤትሽ እየመጣሁ ነው፣ አለሽ?” ሲል ጠየቀኝ፡፡ “አለሁ “አልኩት፤ ሲመጡ ከቴዲ ጋር ናቸው፡፡ “ቴዲ እኔ እኮ ትንሽ ሆነህ ነው የማውቅህ፣መወለድህን ብቻ ነው የማወቀው፣ ከዛ በቀር አላውቅህም” አልሁት፡፡

ቴዲ የጥበብ ሰዎችንና ሌሎች ታላላቆቹንም እንዴትእንደሚያከብር ልናገር ስለፈለግሁ ነው ይሄን የማነሳው፡፡ ከዛ “አንቺ ለነሙሉቀን፣ ለቴዎድሮስ ታደሰ ግጥም ስትጽፊ ኖርሽ፤እኔ በእነሱ ዘፈን ነው ያደግሁት፣ አንቺን ሳላመሰግን አሜሪካን መድረክ ላይ አልወጣም ብዬ ነው የመጣሁት” አለኝ፤ ደነቀኝ ፡፡

የእኔ ልጅ እዚህ ተወልዳ በሁለት ዓመቷ እዚሁ ተመልሳ ነው ያደገችው፡፡ ቴዲን ነው የምታውቀው፣ በቴዲ ፍቅር ያበደች ልጅ ነው ያለችኝ፡፡ ቤት መጥቶ እሷ ከት/ቤት ስትመለስ፣ “ቴዲ አፍሮ እኮ ነው እማማዬ” አልኳት ቦርሳዋን ወረወረች፣ ስልኩን ጨበጠች “Guess what “እያለች ለመንደሩ ልጆች በሙሉ “Teddy Afro is in our house” ትጮሃለች፣ ትትጮሃለች ፈጽሞ ቤቱ አልበቃ አላት፡፡ ቴዲ ጠራና አቅፎ ሳማትና “እንዴ የአንቺ እናት እኮ ከኔ በላይ ዕውቅ ናት” ሲላት “No way” አለች፤የማይመስል ነገር አትንገረኝ ማለቷ ነገር ነው፡፡ እሷ ደሞ የእኔን አታውቅም፤ ቴዲ እኔን አክብሮ ነው የመጣው፡፡

ቴዲ “ሰው ገደልክ” ተብሎ አሜሪካን አገር መጥቶ ክሱ ከተመሰረተበት በኂላ አንድ የቤተክርስቲያን ዝማሬ ሰርቶ “አለም አዳምጪልኝ” ብሎኝ ምሳ በልተን መኪና ውስጥ እሱን እያዳመጥን ወደ ኤርፖርት እንሄዳለን፡፡ ወደ አዲስ አበባ ሊመለስ ማለት ነው፡፡

ቅር እንዳይለኝ፣ ሳልነገረው እንዳላልፍ ብዬ “ቴዲ ወያኔ ፋይል ከፍቶብሃል ይሄን ታውቃለህ፤ ወጥተህ የምትቀር ስለመሰላቸው ለቀውሃል ስትመለስ ግን የሚጠብቅህን ነገር ገምተኻል?” አልሁት፡፡ “አዎ! አለም ስንቶቻችን ጠፍተን፣ ተሰደን እንለቅ? መሞት ካለብኝ እኔ ሞቼ ይቺ አገር ነፃ መውጣት አለባት፡፡ እኔ አባቴ ያስተማረኝ ኢትዮጵያን የማውቃት፤ ስለ እሷ እውነቱን እየተናገርኩ መኖር አለብኝ፡፡” ብሎ ተመለሰ፤ አልቀረለትሞ ታሰረ፡፡

ታስሮ ሁሉም አለፈና ለ SEED ሽልማት እዚህ አሜሪካ መጣ፤ እንደገና አገኘሁትና እኔ ቤት ራት እየበላን እጄ ላይ ስልክ ተደወለ፤ ከካናዳ ነው፡፡ የማላውቀው ሰው “ቴዲ interview ሰጥቶ ነበር እንዴ VOA ላይ” ይለኛል፤

“አዎ” አልኩ፡፡ “በዛ VOA ላይ በሰጠው interview ባለሥልጣኖች ቡና ቤት ውስጥ ሆነው “እስቲ እሱ ያላትን ኢትዮጵያ እዚህ መጥቶ ያስረዳናል” ሲሉ ስለሰሙ እባክህ ንገር ብለውኝ ነው እንደው ካገኘሽው” አለኝ፡ ፡ እኔ ቤት ነው ያለው ቴዲ በዛ ሰዓት ላይ፤ መመለሻው በማግስቱ ነበር ደነገጥሁ፡፡

ዝም ብል እንዴት ሰምተሽ ዝም አልሽ? ልባል ነው፣ ብናገር ድጋሚ በዛ ጊዜ የተናገርኩትን ነገር ነው የምናገረው፡፡ እና Kitchen ውስጥ አምለሰትን ጠራሁዋት “አምለሰት አንድ ሰው ደወለልኝ እና እንዲህ እያለኝ ነው፤ ምን ታስቢያለሽ?” አልኳት “ንገሪው” አለችኝ፡፡ ጠራነው፡፡

“ቴዲ” አልኩት “የማላውቀው ሰው ከካናዳ ደወለ VOA ላይ የሰጠኸውን interview የወደዱልህ አልመሰለኝም፡፡ የሆኑ ባለሥልጣናት ሲፎክሩብህ ነበር መጠጥ ቤት ሆነው፡፡ ይሄን የሰማ ሰው ነው ንገሪው የሚለው” አልኩት፡፡

“ውይ አለም እንኳን እኔ ልጠፋ የአንቺ መምጫ እኮ ደረሰ” አለኝ፡፡

አገሬ ስገባ ከሁለት ቀን በኂላ ደወለ “ቴዲ ነኝ አለም እንኳን ደህና ገባሽ ልልሽ ነው” አለኝ፡፡ “ቴዲ አሁን ማን ያምነኛል? እኔ ጥፋ ስልህ አንቺ መምጫሽ ደርሷል ያልከኝን ሰው ያምነኛል ብናገር?” ስለው “እኔ እኮ አይደለሁም እግዚአብሔር ስለፈቀደ ነው፡፡” አለኝ፡፡”

*አለምፀሐይ ወዳጆ በአሜሪካን ሀገር ለቴዎድሮስ ካሳሁን የእውቅና ሽልማት ሲበረከት ከተናገረችው የተወሰደ፡፡*

**…ቴዲ “ሰው ገደልክ” ተብሎ አሜሪካን አገር መጥቶ ክሱ ከተመሰረተበት በኋላ አንድ የቤተክርስቲያን ዝማሬ ሰርቶ “አለም አዳምጪልኝ” ብሎኝ ምሳ በልተን መኪና ውስጥ እሱን እያዳመጥን ወደ ኤርፖርት እንሄዳለን፤ ወደ አዲስ አበባ ሊመለስ ማለት ነው…**

## “ይህ ወቅት ለአማራ ሕዝብ በተለየ ሁኔታ ፈታኝ ነው”

“ ...በሰኔ 15ቱ ድርጊት ወንድሞቻችንን አጥተናል። መሪዎቻችንን አጥተናል። ተጎድተናል። አዝነናል። ከዶ/ር አምባቸዉ፣ምግባሩ፣ እዘዝና ብ/ጀ አሳምነዉ በተጨማሪ በጸጥታ ሥራ ላይ የተሠማሩ ፖሊሶችን አጥተናል፡ ፡ በተፈጠረዉ አሳዛኝና ቅስም የሚሰብር ክስተት በአማራ ሕዝብ ላይ መቼም የማይረሳዉ የታሪክ ጠባሳ አሳርፎብናል። ይህ ወቅት ለአማራ ሕዝብ በተለዬ ሁኔታ ፈታኝ ነዉ። ይህን የፈተና ወቅት ለመዉጣት የአማራ ሕዝብ አንድነት ከመቼዉም ጊዜ በላይ አስፈላጊ ነዉ። አንድ ከመሆን ያነሰ ማናቸዉም አካሄድ ለአማራ ሕዝብ የከፋ ጉዳትን ያስከትላሉ። እንግዲህ ያለፈዉ አልፏል። በታሪካችን ጥቁር ነጥብ ሆኖ ይመዘገባል። እንደ ሕዝብ ከእዚህ የከፉ ወቅቶችንም አሳልፈናል። ብዙ ዋጋ አስከፍለዉንም ቢሆን በብቃትም ተወጥተናቸዋል፡ ፡ ከመቼመዉም ጊዜ በላይ የሚያስፈልጉንን ወንድሞቻችንን፣መሪዎቻችንን አጥተናል። አሁን የሚያስፈልገዉ ከእዚህ የፈተና ወቅት በአፋጣኝ የምንወጣበትን አካሄድ መከተል ነው...” **ውብሸት ሙላት**

## ከህዝብ ራስ ላይ ውረድ!

አሁን ደግሞ “ባለተራ” የምትባል አዲስ የመጣች ፋሽን አለች። ከአራተኛ ክፍል ለሽንት ብሎ ወጥቶ ያልተመለሰ ሁሉ የፖለቲካ ተንታኝ ተብሎ አይኑን አፍጥጦ በየሚዲያው ባለተራ ምናምን እያለ ይቀባጥራል። መቼስ ዘንድሮ ሰው ሁሉ ኦሮሚኛ በሰማ ቁጥር መደንገጥ ጀምሯል መቼስ እኔን ታውቀኛለህ እስከዛሬ ለአማራውም ለሌላውም ስጮህ ነው የከረምኩት። አሁንም ይሄን የምፅፍልህ አትላንቲክ ውቅያኖስ የሚያክለው አፍህን እንድትከፍትብኝ ሳይሆን እንዲገባህ ነው! እስከማውቀው ድረስ ኦሮሞ አይደለም ሌላ ቦታ ኦሮሚያ ውስጥ እንኳ ከሌላው የተለየ ፌቨር እንዲሰራለት አይፈልግም። ኦሮሞ ጥያቄው የእኩልነት ነው። ትግሉ እኩል ልሁን እንጂ የበላይ ልሁን የሚል አይደለም። ስለዲሞክራሲና እኩልነት ደግሞ እነአሜሪካና ካናዳም ሊያስተምሩት አይችሉም። ኦሮሞ እነፕሮፌሰር አስመሮም አይናቸው እስኪደክም ያጠኑትን ከሶስት ሺ አመት በላይ ሳይቆራረጥ የቀጠለ እንኳን ለሰው ልጅ ለእንስሳ እንኳ መብት የሚሰጠውን የ“ገዳ” ስርአት የገነባ ድንቅ ማህበረሰብ ነው። አሜሪካ ጥቁርን እንደሰው በማትቆጥርበት ወቅት በሞጋሳ የተጠጋውን ሁሉ የሚያቅፍ ስርአት ገንብቷል። ዛሬ አለም adoption ብላ የሰውን ልጅ ማሳደግ የስልጣኔ መለኪያ አድርጋ ከመቀበሏ አስቀድሞ ኦሮሞ «በጉዲፈቻ» የሰውን ልጅ ከራሱ ልጅ በላይ አቀማጥሎ የሚያሳድግበት ከተራራ የገዘፈ የሞራል ልእልና የነበረው ህዝብ ነው። ማንም እየመጣ “ተረኛ” ገለመሌ እያለ አፉን ሲከፍትበት ሳይ የሚገርመኝ ለዚህ ነው!!

አብይንም ሆነ የትኛውንም ፖለቲከኛ መንቀፍ ይቻላል። በአብይ አሳቦ የኢትዮጵያን ግማሽ ህዝብ ተረኛ ማለት ግን ፍቃድ የወጣለት ብልግና ነው! ኦሮሞ ዘመዴ ነገሰ ብሎ ሌላውን የሚጨቁን ህዝብ አይደለም። እንደዛ ቢሆንማ ሃይለስላሴና መንግስቱ ሃይለማርያምስ ኦሮሞ አልነበሩንዴ? ዛሬ አብይ ተነስቶ ኦሮሞን የበላይ ላድርግ ቢል እንኳ መጀመሪያ የሚነሳበት እራሱ ኦሮሞው ነው!! ኦሮሞ ሲጨቆን እንጂ ሲጨቁን ታይቶ አያውቅም። ወደፊትም አይታይም። ምክኒያቱም እኩልነት ተፈጥሯዊ ባህሪው ነው። ዲሞክራሲ ባህላዊ ስፖርቱ ነው። አቃፊነትና ደግነት ለሺህ ዘመናት ያዳበረው ማህበራዊ እሴቱ ነው!! ስለዚህ ማንም በፖለቲካው መድረክ ያጣውን ድል ህዝብን በመስደብ ሊያካክሰው መሞከርየለበትም!!

ባሻዬ ...ከፖለቲከኛህ ጋር ብትፈልግ መስቀል አደባባይ ተቀጣጥረህ ሹሌ ተጫወት። ከህዝብ ራስ ላይ ግን ውረድ!!

**ዘውድአለም ታደሠ**

## “በሙዚቃዬ የማቀነቅነው ስለ ሀቅ፣ መብትና ሰላም ነው”

“ ...ንፁህ ሆኖ ለሀቅና ለትክክል የሚሠራ ሰው እግዚአብሔርም ከላይ ሆኖ ያየናል፤ ምድርም ጭንቅላት ያለውን ሰው ይረዳል። እኔ በሙዚቃዬ አቀነቅን የነበረው ስለ ሀቅ፣ መብትና ሰላም ነው። አንዳንዱ በኦሮምኛ ስለዘፈንኩኝ እንዴት በሶማሊኛ አልዘፈነም? ብሎ ሶማሌውን እኔ ላይ የሚያነሳሳ ሊኖር ይችላል። አማርኛ፣ እንግሊዝኛና ሌሎችም ቋንቋዎች ለምን አልዘፈንክብ ብለው የሚጠይቁ [አሉ]. . . ቋንቋው ኦሮምኛ ይሁን እንጂ መልዕክቱ ዓለም አቀፍ ነው። በሰው ልጅ ላይ የሚደርስ ግፍ፣ ጭቆና፣ ሞት በየትኛውም አገር አለ። በኦሮምኛ ቋንቋ ስለተዘፈነ ወደ ኦሮምኛ ብቻ ጥግ የሚያስይዙኝ አሉ። ግን እኔ የማውቀውና የማስበው የሰውን ልጅ መብት መጋፋት እግዚአብሔር አላደረገውም፤ የሰው ልጅ ነው የሚያደርገው። አካሄዴ፣ መነሻና መድረሻዬ በዛ ላይ የተመሰረተ ነው። ሙዚቃው ከሌላ ሙዚቃ የተሻለ ተብሎ አይደለም። ‘ሪዲንግ ቢትዊን ዘ ላይን’ የሚሉት አለ አይደል? [ግጥሞቹ በመሀል የማይታዩና የማይነበቡ መልዕክቶች አሉት]። እናም ቀና የሆኑ ሰዎች ሙዚቃዬን ይሰሙታል ቀና ያልሆኑ ሰዎች አንድ ጥግ ሊወስዱኝ ይችላሉ እንደ ማለት ነው። ሁሉም ሰው ሙዚቃዬን እንዲወድልኝ እወዳለሁ። ይሆናል ብየም ሳይሆን፤ ስለ መሬት አራሹ፣ ስለ መብት፣ ስለ አካባቢም ከዘፈንኩ ከልቤ ነው፤ ለበጎም ነው። እናም በጎ አስተሳሰብ ያለው ሰው እየሰማ ያደንቅልኛል። ሌላውም እንዳልኩት በሆነ መንገድ ጥግ ሊወስዱኝ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። ለኔ የፈጣሪ ፀጋ ነው ሙዚቃዎቼ እንዲወደዱ ያደረገልኝ። ዋናው መልዕክቱ ነው።...”

**ክቡር ዶክተር አርቲስት አሊ ቢራ BBC**

